# የክርስትና መሰረታዊ እውነቶች

## የደቀ መዝሙር ጠንካራ መሰረቶች

### የመልመሻ መጽሐፍ

“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። (ማቴዎስ 28:19–20)

FDM .WORLD

Craig Caster

*Christian Foundational Truths* in Amharic

ሌሎች  መንፈሳዊ  የስራ መጽሐፍት   በFDM.world

ጋብቻ አገልግሎት ነው ተከታታይ ትምህርት በክሬግ ካስተር

ወላጅነት አገልግሎት ነው ተከታታይ ትምህርት በክሬግ ካስተር
ወጣቶችን መረዳት ተከታታይ ትምህርት በክሬግ ካስተር

ሁሉም የFDM.world የስራ መጽሐፍት ለግል ጥናት፣ ለትናንሽ ቡድኖች፣ እንደ ደቀመዝሙርነት መሳሪያዎች እና ለምክር አገልግሎት ይመከራሉ

# የክርስቲያን መሰረታዊ እውነቶች

## ለደቀመዝሙር የሚሆን ጠንካራ መሠረት

ክሬግ ካስተር

*እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። ኣሜን። ( ማቴዎስ 28:19–20 )*

FAMILY DISCIPLESHIP MINISTRIES
ስልክ: (619) 590-1901
ኢሜል ፡ info@FDM.world
ድር ገፅ፡ www.FDM.world፣ www.discipleshipworkbooks.com

*የክርስቲያን መሰረታዊ እውነቶች፡ ጠንካራ መሰረት ለደቀመዝሙርበክሬግ ካስተር*
ISBN 978-1-7331045-5-5
የህትመት እና የኤሌክትሮኒክስ ስራት የቅጂ መብት © 2021 በክሬግ ካስተር። ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው።
10062021 ክለሳ

በዚህ የመፅሃፍ ፕሮጀክት ላይ ከእኔ ጋር ስለሰራ ለልጄ ጆስቲን ልዩ ምስጋና።

በተጨማሪ ካልተገለጸ በቀር፣ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ ኪንግ ጀምስ ትርጉም® ነው። የቅጂ መብት © 1982 በቶማስ ኔልሰን። በፍቃድ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው።

በKJV ምልክት የተደረገባቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች የተወሰዱት ከኪንግ ጀምስ ትርጉም፣ 1987 ሕትመት ነው። የህዝብ ጎራ።

NASB ምልክት የተደረገባቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የቅጂ መብት © 1960፣ 1962፣ 1963፣ 1968፣ 1971፣ 1972፣ 1973፣ 1975፣ 1977፣ 1995 በሎክማን ፋውንዴሽን ነው። በፍቃድ ጥቅም ላይ የዋለ.

ከላይ የተጠቀሱትን የቅጂ መብት መብቶች ሳይገድብ፣ የዚህ ህትመት ምንም ክፍል–በታተመ ወይም በኤሌክትሮኒክ መጽሐፍ ቅርጸት፣ ወይም በማንኛውም ሌላ የታተመ ተዋጽኦ–ያለቅድመ የጽሑፍ ፈቃድ በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም ዘዴ (በኤሌክትሮኒክ፣ በሜካኒካል፣ በፎቶ ኮፒ፣ በድምጽ ቀረጻ ወይም በሌላ) ሊባዛ፣ ሊከማች ወይም ወደ መልሶ ማግኛ ሥርዓት ሊገባ ወይም ሊተላለፍ አይችልም።

# ይዘቶች

ከደራሲው የተላከ ደብዳቤ.......................................................v

ምዕራፍ 1፡ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ.......................................1

ምዕራፍ 2፡ የእግዚአብሔር አባትነት.....................................22

ምዕራፍ 3፡ መንፈስ ቅዱስ ...................................................40

ምዕራፍ 4፡ መንፈሳዊ እድገት እና ብስለት............................56

ምዕራፍ 5፡ ይቅርታ እና እርቅ..............................................79

ምዕራፍ 6፡ መንፈሳዊ ጦርነት .............................................104

ምዕራፍ 7፡ ሞትና የመጨረሻው ዘመን ...............................141

አባሪ ሀ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ዕለታዊ ቅርርብን ማዳበር........186

አባሪ ለ፡ የሚመከሩ መጽሐፍት፡፡ ........................................188

አባሪ ሐ፡ መዝገበ ቃላት.....................................................190

ለደቀ መዝሙሩ የተላከ ደብዳቤ............................................196

ስለ ደራሲው .....................................................................197

ስለ ቤተሰብ ደቀመዝሙርነት አገልግሎት ...................................198

## ከደራሲው የተላከ ደብዳቤ

ውድ ደቀመዝሙር፣የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ከጀመርኩ በሁለት ዓመታት ጊዜዬ ራሴን እስኪደንቀኝ ድረስ ባማከርኩዋቸው ብዛት ያላቸው ክርስቲያኖች ተገርሜያለሁ ። እነዚህ ክርስቲያኖች ሆነው ነገርግን የክርስቶስ ሕልው የሌለውን የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚመሩና ስለ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ያላቸው መረዳት ጥበብ የጎደለው መሆኑ ነው ። ከስራ ጓደኞቼ ጋር የማደርገውን የጠዋት ፀሎት ስብሰባን ተከትሎ ስለ ጉዳዩ ጭንቀቴን ለሰራተኞቼ ካካፈልኩ በኋላ፣ ፀሀፊዬ፣ “ለምን የሚረዳቸውን የአምልኮ ጽሑፍ አትጽፍም?” ብላ ጠየቀችኝ።

ጭንቅላቴ በጥርጣሬ ጥያቄዎች ተጥለቀለቀ፡ ጊዜ የት አገኛለው? ማን ያነበዋል? የሃይማኖታዊ ጽሑፍ የመጻፍ ብቃት አለኝ? የሃይማኖት ትምህርት ቤት ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ገብቼ አላውቅም ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንኳን የተመረቅኩት በደካማ ውጤት ነው።

መመሪያ ለማግኘት መጸለይ ስጀምር፣ ጌታ እሱን እንዳውቅ እና እንድተማመንበት መንፈሳዊ መሰረት የጣሉብኝን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች እንዳካፍል በልቤ አኖረ። በእነዚህ እውነቶች ላይ ያለን ግንዛቤ እና እምነት ማነስ ሰይጣን እኛን ለማታለል፣ ለማዘናጋት እና ለመፈተን ወደ አእምሯችን የሚያስገባውን ቀጥተኛ መንገድ ያገኛል በዚህም የእግዚአብሔርን ማንነትን እና የእኛን የእግዚአብሔር ልጅነት እንድንጠራጠርና ፍርሐት እንዲያድርብን ያደርጋል።

ይህንን አቅጣጫ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከሰራተኞቼ ከሚሰጠኝ ተከታታይ ማበረታቻ እና ድጋፍን በማጣመር ፣ ጠንክሬ ይህን ራስን ማስተማር የሚቻልበትን መፅሃፍ ወለድኩ። እና አሁን ከሃያ ዓመታት በኋላ፣ እግዚአብሔር ይህን የአምልኮ መጽሐፍ በመጠቀም በአለም ዙሪያ በሺዎች የሚቆጠሩ ሕይወቶች ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ሳውቅ ተገርሜአለሁ።

ይህ ራስን ማስተማር የሚቻልበትን የአምልኮ መፅሃፍ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ ጥልቅ ግንኙነት እንዲመራችሁ እና ለእምነታችሁ ጠንካራ መንፈሳዊ መሰረት እንዲመሰርትላችሁ፣ ወደ እርሱ እንድትቀርቡ እና በፅድቁ እንድትመላለሱ ዘንድ እንዲረዳችሁ ጸሎቴ ነው። ይህንን መጽሐፍ ስትጨርስ፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ተልእኮ ማለትም "ሂዱና ደቀመዝሙርቴ አርጎአቸው" የሚለውን ለመፈጸም እንደ መሳሪያ በመጠቀም ና ጌታን በመጠየቅ በህይወታችሁ ውስጥ ካሉት ሰዎች መካከል ደቀ መዛሙርት ማድረግ የምትችሉትን እንዲሁም አብሮአችሁ የምትጓዙት ሰው እንደሚገልጥላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ።

በተጨማሪም *ጋብቻ አገልግሎት ነው፣ ወላጅነት አገልግሎት ነው* እና *ወጣቶችን ማስተዋል/መረዳት* የሚሉትን ሦስት መፅሄቶች እንድታነቡ አበረታታችኋለሁ። በድረ-ገጻችን www.FDM.world ላይ ልታገኟቸው ትችላለህ።

በየቀኑ ወደ ኢየሱስ በመቅረብ እና እሱ የጠራህ እና የቀባህ ደቀ መዝሙር እንድትሆን ያርግህ ። አሜን!

በክርስቶስ፣

ፓስተር ክሬግ ካስተር

## ምዕራፍ 1

## ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ

ያደግኩት በካቶሊክ ወላጆች ሲሆን እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ የካቶሊክ ትምህርት ቤት ተምሬያለሁ። በልጅነቴ የሃይማኖት ፍላጎት አልነበረኝም፣ ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መሠረታዊ ግንዛቤ ነበረኝ   እሱ የአለም ፈጣሪ እንደሆነ እና ኢየሱስ የሚባል ልጅ እንዳለው አምን ነበር። ነገር ግን ስለ ኢየሱስ አመጣጥ በተወሰነ ደረጃ ጨለማ ውስጥ ነበርኩ። *አምላክ ነው የፈጠረው? ህይወቱ በድንግል ማርያም ነው የተጀመረው ?ጥያቄዎች ነበሩኝ*

ከስድስተኛ ክፍል በኋላ ለሃይማኖታዊ ተጽእኖዎች ብዙም ትኩረት አልሰጠሁም ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ኢየሱስ ማሰብ አልፈለኩም ምክንያቱም እነሱ እንደማይወዱኝ ስለተሰማኝ ነው። በስጋዬ መነሳሳት እየኖርኩ እና ደስተኛ ለመሆን በጣም እየሞከርኩ ዝም ብዬ የመኖር ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ። የህይወቴ የጨለማ ጊዜ ነበር። ነገር ግን  የሃያ አንድ አመት ልጅ ሳለሁ ኢየሱስ እራሱን ገለጠልኝ እና እንደ ጌታዬ እና አዳኜ አድርጌ ተቀበልኩት። ከበርካታ አመታት በኋላ፣ ቃሉን ማጥናት ጀመርኩ እና በበሰሉ ክርስቲያን አማኞች ደቀ መዝሙር ሆንኩ። ስለ ክርስቶስ እና ለምን ወደዚህ ምድር እንደመጣ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችንና እውነቶችን እንዳውቅ ረድተውኛል።

### ትምህርት 1–ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው?

በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። አንዳንዶች እርሱ ታላቅ ነቢይ ወይም አስተማሪ እንደሆነ ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ከረጅም ጊዜ በፊት የኖረ በጎ ኢድራጊ ሆኖ የሞተ ሰው እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል። ኢየሱስ በማቴዎስ 16 ላይ ለደቀ መዛሙርቱ የጠየቃቸውን ተመሳሳይ ጥያቄ ቢጠይቃችሁስ? "እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላለህ?" (ቁጥር 15) ምን ምላሽ ትሰጣለህ?

______________________________________________________________________

________________________________________________________

______________________________________________________________________

_________________________

የክርስትና እምነት መሰረቱ በኢየሱስ ማንነት ላይ ብቻ ነው ያለው፣ ቅዱሳት መጻህፍትም  ማንነቱ የተገለጹበት ብቸኛ ቦታ ነው። ሙሉ ህይወታችሁ ሊቀረፅ የሚችለው እሱን ማን እንደሆነ በማመናችሁ ላይ ነው።

### ኢየሱስ ፈጣሪያችን ነው።

በዘፍጥረት 1፡1 ላይ እንደተገለጸው በፍጥረት የሚያምኑ አብዛኞቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያያይዙታል ብሎ መናገሩ ደህና ይመስለኛል። ኢየሱስ ግን ለጽንፈ ዓለሙ /Universe / መፈጠር አስተዋጽኦ እንዳደረገ ብነግራችሁስ?  ያስገርማችሁዋል?

በቆላስይስ 1፡16-17 ስለ ኢየሱስ የተማርከውን በአጭሩ ጻፍ።

______________________________________________________________________

_________________________

____________________________________________________________

____________________

____________________________________________________________

________

ዕብራውያን 1:10

____________________________________________________________

_______

____________________________________________________________

____________________

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፣ ኢየሱስ በፍጥረት ውስጥ ጉልህ ሚና እንደተጫወተ እንማራለን። ከመጀመሪያው ጀምሮ እርሱ የቅዱስ ሥላሴ አኩል አካል ነው። ኢየሱስ ሁሉንም ነገር የፈጠረው በራሱ እና በሱ በኩል ነው።

በመቀጠል፣ እሱ ፍጥረቱን በመፍጠር ብቻ እንዳላቆመ እናያለን። ሁሉም ነገር የእርሱን ተከታታይ ድጋፍ ይፈልጋል።

**ኢየሱስ ረዳታችን ነው።**

በዕብራውያን 1:3 መሠረት ኢየሱስ ሁሉን ነገር አንድ ላይ የሚደግፈው እንዴት ነው?

____________________________________________________________

________

____________________________________________________________

__

ክርስቶስ የሁሉም ነገር ጥበበኛ እና ኃያል ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን ፍጥረቱን በታማኝነት በህይወት እንዲቀጥሉ ያደርጋል ። እሱ በምድር ላይ ከነበረበት ጊዜ በፊት፣ በነበረበት ጊዜ እና በኋላ ሁሉ ከመጀመሪያው ጀምሮ ፍጥረቱን ሲደግፍ ቆይቷል።እርሱ በዚህ ደቂቃ እንኳን በሰማይ በአብ ቀኝ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አጽናፈ ሰማይን እየደገፈ ነው።

**ማስቀጠል**- መደገፍን ማስጠት፣ አቅፎ መያዝ ፣ እንደነበረ ሳይበላሽ ሳይጎዳ ማቆየት

**ቤዛ መሆን**-በክፍያ ይዞታን መልሶ ለማግኘት; ከምርኮ ወይም ከባርነት ነፃ ለማውጣት ወይም ለማዳን; ለማገ ምወይምለማድረስ.

የነገሮች ፈጣሪ እና ደጋፊ መሆን ብቻም በቂ ሳይሆን ኢየሱስ የመጨረሻውን ዋጋ ከፍሎ የአለም ቤዛ እና አዳኝ ሆኗል።

**ኢየሱስ ቤዛችን ነው።**

ቲቶ 2:14 እና ቆላስይስ 1:13—14 ስለ መቤዠታችን ምን ይላሉ?

____________________________________________________________

____________________

ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት፣ ኢየሱስ በፈቃዱ ሰማያዊውን ዙፋኑን ትቶ በፍጥረቱ መካከል የኖረው ለእኛ ዋጋ ያለው  መስዋዕትነት ለመክፈል  ነው ።ይህንን ያደረገው የሰውን ልጅ ለመዋጀት እና እኛን ወደ ከመጀመሪያው አላማችን ጋር ለማስታረቅ ነው።

**ትምህርት 2–ቤዛ የሚሆን ለምን ያስፈልገናል ?**

በሰው ልጅ ስነፍጥረት ላይ በደመ ነፍስም ቢሆን የሆነ ስህተት እንዳለ ማስረጃ ለማግኘት ሩቅ መመልከት አያስፈልግም:: የራሴን ልብ በማየት በቂ ማስረጃ አገኛለሁ:: የአንተን ስትመለከት ምን ታያለህ? የችግሩን ምንጭ ለማግኘት ወደ መጀመሪያው እንመለስ::

ይህ ሁሉ የጀመረው በኤደን የአትክልት ስፍራ ማለትም የሰው ልጆችና ተፈጥሮ ፍጹም ተስማምተው እንዲኖሩባት በተፈጠረች ገነት ውስጥ ነው:: ፈጣሪ ከፍጥረቱ ጋር ፍጹም በሆነ ኅብረት የተራመደበትም ጊዜ ነበር:: እንደ አለመታደል ሆኖ ይህንን የመሰለ ምናልመውንና ፍጹም የሆነ ቦታ ያጣነው መጥፎ ስህተት ተፈጥሮ ስለነበረ ብቻ ነው::

ዘፍጥረት 1:26ን አንብብ:: የመጀመሪያው ሰው የማንን ምስል ይዞ ተፈጠረ ?

____________________________________________________________________________________________________________________

***በመልካችን*** እንደ ***ምሳሌያችን*** የሚሉትን ቃላት አስተውል ይህ የሚያመለክተው በመጀመሪያው ሰው ፍጥረት ላይ(ቦሃላም አዳም የተባለው)እግዚአብሔር ከኢየሱስ ጋር መስራቱን የሚገልፁ ናቸው ::

ዘፍጥረት 2:15—17ን አንብብ:: እግዚአብሔር አዳምን የከለከለው አንድ ነገር ምንድ ነው ? ትዕዛዙንስ ባይታዘዝ ምን ይሆናል?

____________________________________________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________________________________________

ዘፍጥረት 2:18—22ን አንብብ:: አምላክ ለአዳም ይህን ትእዛዝ ከሰጠው በኂላ ጓደኛ ሰጠው ቦሃላም ሔዋን የተባለችውን :: አሁን ዘፍጥረት 1:28ን አንብብና የእግዚአብሔርን በሱ አምሳያ ለተፈጠሩት የሰጠውን መመሪያዎችን ጻፍ::

____________________________________________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________________________________________

እግዚአብሔር ሔዋንን ለአዳም ሚስት እንድትሆን አደረጋት::አዳምንም ፍጥረታቱን ሁሉ በታማኝነት እንዲንከባከብ አዘዘው:: ሁሉም ነገር ፍጹም ነበር ነገር ግን ሰይጣን በዘፍጥረት 3 ላይ እንደተገለጸው በእባብ ተመስሎ ወደ ስፍራው ገባ:: እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ያሰበውን ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋም እንደ ሌባ መጣ (ዮሐ. 10፡10):: የሰይጣን የመጀመሪያ ዘዴ ሔዋን የአምላክን መልካምነት እንድትጠራጠር ለመፈተን ነበር::

በዘፍጥረት 3፡1 ላይ ሰይጣን ሄዋንን ምን ጠየቃት?

____________________________________________________________________________________________________________________

በዘፍጥረት 3፡2-3 ሔዋን ምን ምላሽ ሰጠች?

ማስተዋል ያለባችሁ ሔዋን እግዚአብሔር እሷን ከመፍጠሩ በፊት ለአዳም የሰጠውን ትእዛዝ ታውቃለች። አዳም የእግዚአብሔርን ሕግ ና አዋጅ እንዲሁም ማስጠንቀቂያ አስፈላጊነት በመረዳት ለትዳር ጓደኛው በታማኝነት አካፍሏታል /ነግሯታል ።

በዘፍጥረት 3፡4 ላይ ሰይጣን ለሔዋን የነገራት ውሸት ምንድነው ?

በዘፍጥረት 3፡5 ላይ ሰይጣን ሔዋንን ከፍሬው ብትበላ ምን እንደሚሆን ተናገራት?

በዘፍጥረት 3፡6 ላይ ሔዋን ስለ ፍሬው ምን ማራኪ ነገር አገኘች?

ምን ለማድረግ ወሰነች?

ሔዋን ለአዳም ፍሬውን ስታቀርብለት ምን አለ ና ምን አደረገ?

የመጀመሪያዋ ሴት የውሸት ልዑልን አምና የፈጣሪዋን መልካምነት ተጠራጠረች ነገር ግን የመጀመሪያው ሰው አዳም ምንም ሳይል አለመታዘዝዋን ተከተለ።

አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝን እንዲጠብቅና እና በታመኝነት ሚስቱን እንዲንከባከብ የተሰጠውን መመሪያ አልጠበቀም ። የእግዚአብሄር ፈቃድ መፈጸሙን ለማረጋገጥ እሷን መጠበቅ እና አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ነበረበት። አዳምና ሔዋን የሰይጣንን ውሸቶች አምነው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠሩ፣ ያስጠነቀቃቸውን መዘዝም በመጠራጠር የተቀረውን የሰው ልጅ ክፉኛ ጎዳው ከነዚህም ጉዳቶች የሚከተሉትን ተመልከት ፦

- በእግዚአብሔርና የሱን አምሳያ በተሸከሙት መካከል የነበረው ኅብረት ፈረሰ (ዘፍጥረት 3፡8-10)።
- እግዚአብሔር የሰውን ዘር ከኤደን ገነት አስወጣ (ዘፍጥረት 3፡23-24)።
- ያለመታዘዝ ፍርድ ሞት ነው (ዘፍ 5፡5)።
- የአዳም ኃጢአት በሰው ዘር ሁሉ ተስፋፋ (ሮሜ 5፡17-19)።
- የሰው ልጅ ተስፋ አጣ በራሱም ለማገገም በምንም አልቻለም (ኤፌሶን 2፡12)።

የተፈጠርነው በእግዚአብሔር መልክ ነው፤ ማለትም የተሰጠን አዕምሮ ማመዛዘን እና ምክንያታዊ አስተሳሰብን ማሰብ የሚችል ኢንዲሁም ልባችን ስሜቶች እና ፍቅር የሚሰማው ነው። እግዚአብሔር የመምረጥ ነፃነት ሰጠን ግን በሚያሳዝን ሁኔታ የነፃነታችንን ስጦታ ፈጣሪያችንን ለመቃወም ተጠቅመንበታል። ከገነቱ ክስተት በኋላ ጊዜ እየጨመረ/እየገፋ ሲሄድ ነገሮች እየተሻሉ አልሄዱም ።

አምላክ የሰውን ልጆች ሲመለከት ያየውን በአጭሩ አብራራ።

ኦሪት ዘፍጥረት 6፡5

ዘጸአት 32፡22

_

መዝሙረ ዳዊት 53፡1-3

የሰው ልጅ ያለ ተስፋ በኃጢአት ጠፍቷል። ከመጀመሪያውኑ ከፈጣሪያችን ሸሽተን ከእርሱም በመራቅና በራሳችን መኖርንን ፈለግን—የሥጋችንን ምኞት በትዕቢት ፈጸምን። ዛሬም ምንም የተለወጠ ነገር የለም። ለእግዚአብሔር አለመታዘዛችን ህመምን ፣ ስቃይን እና መከራን ሁሉ እያመጣብን ነው ።

**ኃጢአት ምንድን ነው?**

**የእግዚአብሔርን ህግጋትን መጣስ።**

**ራስን ከፈጣሪ በላይ ከፍ ማድረግ።**

**የእግዚአብሔርን ትእዛዛት አለማክበር።**

**በእግዚአብሔር ፈንታ ራስን በግል ህይወት ላይ የመጨረሻ ስልጣን ያለው ማድረግ።**

የራስዎን ህይወት እና በዙሪያዎ ያለውን ዓለም ሲመለከቱ እግዚአብሔር ስለ ሰው ልጅ በሚሰጠው ግምገማ እንዲሁም የእኛ ብቸኛ የመቤዠት ተስፋ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ብቻ መሆኑን ይስማማሉ ?

ማኅረታዊ እውነት

ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ፈጣሪ እና ጠባቂ ነው። ወደ ምድር የማጣውየ ሰውን ልጅ ለማቤዠት ነው።

**ትምህርት 3– እኛ መቤዠትን/መዳንን ያገኘነው  እንዴት ነው?**

**የክርስቶስ መስቀል**

ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘር  ካለበት ኃጢአታዊ  ሁኔታ ነፃ እንዲወጣ  መቤዥትን  እንዴት አቅርቦ ነበር?

ኤፌሶን 1:7

________________________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________________________

1ኛ ጴጥሮስ 1:18-19

________________________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________________________

ሮማውያን በመስቀል ላይ ሞት የተባለውን ቅጣት ፈለሰፉ፣ ይህም ለመጥፎ ወንጀለኞች በጣም የተለመደው የማሰቃያ ዘዴ ነበር:: አሳፋሪና በህመም የተሞላ ቀስተኛ ግድያ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው፣ የኢየሱስ ብዙ አይሁዳውያን ወገኖች እርሱን አልተቀበሉትም፣ ጓደኞቹም ትተውት ሄዱ፣ የሃይማኖትና የመንግስት መሪዎችም ፈረዱበት:: ተሳለቁበትና ተገረፈ - ጀርባው ላይ ባዶ ቆዳው ላይ ብረት የተገጠመበት የቆዳ ጅራፍ ተመታ:: የሮማውያን ወታደሮች ጢሙን ነጭለው በፊቱ ላይ ተፉበት:: ከዚያም እርቃኑን አድርገው ልብሱን ተደራረቡበት::

ኢየሱስ፣ ፈጣሪያችን፣ በሕይወት እያለ በመስቀል ላይ ተቸነከረ፣ እዚያም ለስድስት የሚያሠቃዩ ሰዓታት ተሰቅሎ ሞተ:: በመስቀል ላይ በነበረባቸው የመጀመሪያዎቹ ሦስት ሰዓታት፣ ብዙ የሚያልፉ ሰዎች ይሳለቁበት ነበር፣ ሌሎች ደግሞ በደረሰው አስፈሪ ነገር ያለቅሱ ነበር:: በመጨረሻዎቹ ሦስት ሰዓታት ውስጥ፣ የዓለም ኃጢአቶች በእርሱ ላይ ስለተጫኑ ሰማዩ ጨለመ:: በዚያ ቀን፣ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት፣ ኃጢአታችን በእርሱ ሞት ውስጥ ገባ (ማቴዎስ 26:3—27:56)::

ኢሳይያስ 53:3—6ን አንብብ:: ነቢዩ ኢሳይያስ አስቀድሞ ስለተነገረው መሲሕ የተናገረውን ጠቅለል አድርገህ ጻፍ::

________________________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________________________

ኢሳይያስ እነዚህን ቃላት ከኢየሱስ በመስቀል ላይ ለኃጢአታችን ከመሞቱ ከስድስት መቶ ዓመታት በላይ በፊት እንደተናገራቸው ታምናለህ? የኢየሱስ ሞት የዚህ ትንቢት ፍጻሜ ነበር፣ እርሱ እውነተኛ አዳኝ መሆኑን

ያመለክታል።

> ማስረታዊ እውነት
> በኃጢአታችን ምክንያት ማክፈል የማንችለውን ዕዳ ከእግዚአብሔር ተበደርን። ኢየሱስ በማስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስ ዕዳችንን ከፍሎነፃ አወጣን ።

ዮሐንስ 19:30ን አንብብ። ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት የተናገረው የመጨረሻ ቃል ምን ነበር?

*ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የማዳን ስራውን ጨረሰ ። ከሞተ በኋላ የአርማትያሱ ዮሴፍ የእየሱስን ሰውነት መቃብር ውስጥ አኖረው በዚያም ለሦስት ቀናት ቆየ ። ሞት ግን በኢየሱስ ላይ ስልጣን አልነበረውም ።*

**የኢየሱስ ትንሳኤ**

*በዮሐንስ* 20 *መሠረት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ተነስቷል!* 1 *ቆሮንቶስ* 15:17*ን አንብብ። የእሱ ትንሣኤ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?*

______________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________
__________

*ሐዋርያው ጳውሎስ ቆሮንቶስያውያንን የክርስቶስ ትንሳኤ ባይኖር ኖሮ የኃጢአት ይቅርታ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ሕይወት ተስፋ ሊኖር እንደማይችል እንዲረዱ አሳስቧቸዋል።*

*ሮሜ* 4:25 *ኣንብብ። ኢየሱስ ከሞት የተነሣው ለምንድን ነው?*

______________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________
__________

ኢየሱስ በሞቱ ጊዜ ኃጢአታችንን በራሱ ላይ ተሸከመ። ትንሳኤው ጽድቁንና ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ሕይወት ስጦታን ገለጠ። ኢየሱስ ሞትን ድል በማድረግ፣ የሚገባ መሥዋዕት እንደነበረና እግዚአብሔር ሕይወቱን እንደ ምትካችን አድርጎ እንደተቀበለው አረጋገጠ።

> ***ማፅደቅ :-*** *ከጥፋተኝነት ወይም ከተጠያቂነት ነፃ ማሆንን ማታወጅ፣ ማፍታት፣ እንደ ጻድቅ አድርጎ ማያዝ; ከኃጢአት ቅጣት ነፃ ማሆን ።*

> ማስረታዊ እውነት
> የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ለክርስትና እምነት በጣም አስፈላጊ ነውምክንያቱም ያለዚያ ኢየሱስ እንደ ተራ ሰው ሞቶ ይሆን ነበር። ለልጆቹ የዘላለምሕይወት ተስፋውምባዶ ይሆን ነበር ፣ እናምእሱ አምላክ አይሆንም ነበር ።

ኢየሱስ ለምን ወደ መስቀል ሄደ?

ይህ ቀላል ጥያቄ ነው። እረኛው ዳዊት በአንዱ መዝሙሩ ውስጥ ለእግዚአብሔር ተመሳሳይ ነገር ጠይቋል። የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ኃይል እንዲሁም የፈጠረውን ሁሉ ካሰበ በኋላ ዳዊት “ሰው ምንድነውና ታስበዋለህ?” ሲል ጠየቀ (መዝሙር 8፡3–4)።

ኢየሱስ በፈቃዱ ወደ መስቀል የሄደው ለምንድን ነው?

ሮሜ 5፡7-8

___________________________________________________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________________________________

ዮሐንስ 3፡16

___________________________________________________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________

እንደዚህ ቀላል ሊሆን ይችላል? በርግጥ ነው። ምንም እንኳን የእርሱን ፍቅር ጥልቀትና በእኛ ላይ ያኖረውን ዋጋ ሙሉ በሙሉ ባንረዳም፣ ለእኛ የሚሰጠን የእግዚአብሔር ወሰን የሌለው ጸጋና ምሕረት ተጨባጭና ዘላለማዊ ማስረጃ ነው።

## ትምህርት 4–በጸጋው የዳንን

**እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ኃጢአት ላይ የጽድቅ ፍርዱን ለመፍረድ ሁሉንም አይነት መብት አለው፣ ነገር ግን በምትኩ፣ ምሕረትንና ጸጋን ዘረጋ። ኤፌሶን 2፡1—9ን አንብብ እና የተማራችሁትን አጠቃልና ፃፍ ።**

___

___

___

___

የእግዚአብሔር ጸጋ እና ምሕረት በኢየሱስ ሕይወት፣ ሞት እና ትንሳኤ ብቻ የተገለጡ ናቸው እንጂ ለማንም የማይገኙ ና የማይገቡ ነበሩ። ጸጋ እና ምሕረቱ በየማለዳው አዲስ ነው የማይጠፋው ፍቅሩ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ማስረጃ መሆኑን ያሳያል። እርሱን የበለጠ እንዲወደን ማድረግ የምንችለው ምንም ነገር የለም እና እንዲቀንስም እንዲሁ። ምሕረቱ ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ መለያየትን ይከለክልልናል። ጸጋው በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ አማካኝነት ነጻ የሆነ የድኅነት ስጦታን ይሰጣል።

ጸጋ የማይገባን ስጦታ ነው፣ ምሕረት ደግሞ የሚገባንን ፍርድ እንዳያገኘን ያደርጋል።ከጽድቅ ፍርዱ ይልቅ፣ እግዚአብሔር ለሁሉም ድነትን ይሰጣል።

> ***ምህረት-*** *በቅጣት ጉዳት ከማድረስ ትዕግስት; ርኅራኄን ወይም ይቅርታን የማጠቀም ዝንባሌ፣ ለመማር ወይም ለሚረዳት ፈቃደኛነት፣ እንደ ርህራሄ ወይም ምስ የሚቆጠር በረከት።*
>
> ***ጸጋ-*** *የማይገባ መለኮታዊ ምስ፣ ለሰው ልጅ ለዳግም ልደት ወይም ለመቀደስ የተሰጠ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ፣ ነፃ የእግዚአብሔር ስጦታ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ መዳን፣ መለኮታዊ ፍቅር፣ ንስሐ ለገባ ኃጢአተኛ ይቅርታ ማስጠት ።*

***መዳን ምንድን ነው?***

**ከኃጢአት ኃይል እና ውጤቶቹ ነፃ መውጣት.**

**ከጨለማ እና ከውሸት ነፃ መውጣት።**

**ከመለኮታዊ ፍርድ መለኮታዊ ድነትን ማግኘት።**

**ከሞት እና ከዘላለማዊ መከራ መጠበቅ.**

በሮሜ 6፡23 *መዳን እንዴት ይገለጻል?*

___

___

በሮሜ 10፡11-13 *መሰረት የዳኑ እነማን ናቸው?*

1 ዮሐንስ 2:2ን አንብብ፡፡ ኢየሱስ የሞተው ለማን ኃጢአት ነው?

1 ጢሞቴዎስ 2:4—6ን አንብብ፡፡እግዚአብሔር ማንን ማዳን ይፈልጋል?

**ኢየሱስ ክርስቶስ ለመላው የሰው ዘር ኃጢአት ነው የሞተው ፡፡** እርሱ ሁላችንም ወደርሱ እንድንጠራው እና ከፍርድ እና ከሞት የሚያድን ምህረትን እንድንቀበል ይፈልጋል፡፡

**ትምህርት 5– የዳንነው እንዴት ነው?**

አንድ ሰው መዳንን እንዴት እንደሚቀበል ማወቅ አለበት። ሁሉም የሐሰት ሃይማኖቶች የሚያስተምሩት የትኛውም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ሊያገኝና ከእርሱ ጋር የዘላለም ሕይወት ማግኘት የሚችለው በሥራ ብቻ እንደሆነ ነው ። ጥሩ ህይወት በመኖር፣ ሌሎችን በመውደድ እና ቤተ ክርስቲያን አዘውትሮ በመገኘት አይደለም እግዚአብሔር የሚቀበለን።ከሚከተሉት ቅዱሳት መጻሕፍት የተማርከውን ጻፍ።

ዮሐንስ 14:6

የሐዋርያት ሥራ 4:12

1ኛ ዮሐንስ 5:12

**ማሰረታዊ እውነት**

በእግዚአብሔር ጸጋና በኢየሱስ ማስዋዕት ካልሆነ በቀር የሰው ልጅ ከኃጢአት ቅጣት የሚድንበት ሌላ መንገድ የለም።
የክርስቶስን ማስቀል አለመቀበል ብቸኛውን የመዳን መንገድ አለመቀበል ነው። በኢየሱስ አለማመን ተስፋ በሌለው ሙሉ ጠፍቶ በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ሆኖ መቆየት ማለት ነው።

ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት መመስረተ እድሉ ለዓለም ሁሉ የተሰጠና የተዘረጋ ነው፣ ነገር ግን በእሱ መመሪያ ብቻ ነው የሚሆነው።እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንድንመሰርት የፈቀደው ብቸኛ መንገድ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም እና በኢየሱስ በማመን ብቻ ነው።

**የመዳንን ስጦታ እንዴት እንቀበላለን?**

አስደናቂውን የእግዚአብሔርን የማዳን ስጦታ ስለ መቀበል ከእነዚህ ጥቅሶች የተማርከውን ጻፍ።

ማርቆስ 1:15

እስከዚህ ነጥብ ድረስ፣ አይሁድ በሕግና በሥራ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ሕይወት ማግኘት እንደሚችሉ ያስተምሩ ነበር። ከዚያም ኢየሱስ *ንስሐ ግቡ* የሚለውን ቃል ተጠቀመ። ከመዳን በፊት በወንጌል ጥቅም ላይ ሲውል *ንስሐ መግባት* ማለት በሕጉ ከመኖር ወይም በጎ ሰው ከመሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በመስቀል በኩል ወደ መዳን መለወጥ ማለት ነው። ለአማኞች ከድኅነት በኋላ *ንስሐ መግባት* ማለት ለሠሩት ኃጢአት ይቅርታ መጠየቅ ማለት ነው። ኢየሱስ ያስተማረውን ወንጌል ማመን ማለት በመልካሙ ዜና ማመን፣በኢየሱስ ክርስቶስ የመዳንን የምስራች እና በሰራው ስራ ማመን ማለት ነው።

***ንስሐ ግቡ*** - *(በግሪክ)አዕምሮን/አስተሳሰብን ማወጥማት ነው።*

**የሐዋርያት *ሥራ*** 16:30-

***የወንጌል ምሥራች በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው።በእኛ ሥራ አልዳንም፣ ስንት ኃጢአቶችን እናስታውሳለን ? ለኃጢአታችንስ ምን ያህል ከልባችን ንስሐ ገባን ? ወይም አራቱን መንፈሳዊ ሕጎች የመረዳት ችሎታችንስ ? ማንም ሰው ኃጢአታአቱን ሁሉ ማስታወስ ና ንስሐ ለመግባት ወይም በመስቀል ላይ ለተከፈለው የኃጢያት ዋጋ የሐዘናቸውን/የፀፀታቸውን ደረጃ ማሳየት አይችሉም ። ደቀ መዛሙርት ስንሆን እና የእግዚአብሔርን ቃል ስናጠ፣ ሁሉም ኃጢአትን እንደሠሩ እና በክርስቶስ መስቀል መዳን እንደሚያስፈልጋቸው እንማራለን፣ እናም ሁሉም በመንፈሳዊነት እንዴት ማደግ እና ወደ እርሱ አምሳል መለወጥ እንደሚችሉ መማር አለባቸው።***

ኢየሱስ እኛን እንድንበትና ከእርሱ ጋር የዘላለም ሕይወት ስጦታን እንድንቀበል ሁሉንም ሥራ ሰርቷል። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታ እና አዳኝ ማመንን ማሳነስ ወይም መናቅ የለበትም፣ ምክንያቱም የመፈጠራችን አላማ እና የተቤዠንበት መንገድ ነው። በኢየሱስ ማመን ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለጸው ኢየሱስ ማመን ማለት ነው እንጂ አንድን ሰው አያጠቃልልም። ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ሲያምኑ የክርስትና እምነትን ጥልቅ የሥነ መለኮት መርሆዎች አልተረዱም ነበር፣ ነገር ግን በዚያ ቅጽበት በድኅነታቸው እርግጠኞች ሆኑ። ጥልቅ ትምህርት ከእምነት በኋላ ኢየሱስን እንደ ጌታና አዳኝ ካመኑ በኋላ ይመጣል፣ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ የሚኖረው ከድኅነት በኋላ ብቻ ስለሆነ፣ እነዚህን መርሆዎች መረዳትና በሕይወታቸው ውስጥ መሥራት የሚችሉት በዚያን ጊዜ ነው።

ማሰረታዊ እውነት
የእግዚአብሔር የማዳን ስጦታ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ነፃ ነው።

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ( ዮሐንስ 3:16 )
አዳኝህን ለመቀበል ቀላል የእምነት ጸሎት ጸልይ፡-

*ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ አምናለሁ። ኃጢአቴን ይቅር በለኝ. በመስቀል ላይ ስለሞትክልኝ አመሰግናለሁ። አዳኝ እና ጌታዬ ሁን። ስለ ጸጋህ እና ምህረትህ እና*

*የዘላለም ህይወት ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሕይወቴን ተቆጣጠር እና እንድሆን የምትፈልገው ሰው እና ደቀመዝሙር አድርገኝ። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ። ኣሜን።*

| |
|---|
| ማስረታዊ እውነት<br>በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን<br>የዘላለምሕይወት እናገኛለን! |

በፈጣሪህ የተወደድክ እና የተፈቀርክህ ነህ። በእርሱ ስታምኑ ካለፈው ኃጢአት ታጥባችኋል እና ከክርስቶስ ጋር በአዲስ ሕይወት ትጸድቃላችሁ።

*በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፤በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል። ( ዮሐንስ 3:18 )*

| |
|---|
| ***የተወገዘ፡*** *-(በግሪክኛ፣ ክሪኖ)ጉዳያቸው እንዲመረመር ና እንዲፈረድባቸው ለፍርድ* |

በኢየሱስ ክርስቶስ በማያምኑ ሰዎች ላይ የሚከተለውን መዘዝ የሚገልጸው የትኛው ቃል ነው?

____________________________________________________________

መልካሙ ዜና በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሰዎች አይፈረድባቸውም።

**ትምህርት 6–ለአማኞች ምን ማለት ነው?**

**አማኞች ይጸድቃሉ**

ከሚከተሉት ቅዱሳን ጽሑፎች የተማርከውን ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

ሮሜ 3፡23-26

________________________________________

---

የሐዋርያት ሥራ 13፡38-39

________________________________________

________________________________________

ቆላስይስ 2፡13—14ን አንብብ። እግዚአብሔር የእኛን  የኃጢአት ዕዳ ምን አደረገ?

________________________________________

________________________________________

በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21 መሰረት ኃጢአተኞች ለክርስቶስ ሲገዙ ምን ይሆናሉ?

________________________________________

________________________________________

**በመስቀል ላይ ምን ሆነ?**

**ኃጢአታችን ሁሉ በክርስቶስ ላይ ሆነ ።**

**በተለወጥን ጊዜ፣ ጽድቁ በእኛ ላይ ሆነ ።**

**ንፁህ ሰው ለእኛ ቅጣቱን ከፈለልን።**

**ጥፋተኞች ነፃ ወጡ !**

ማኅረታዊ እውነት
ህይወታችንን ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈን ስንሰጥ፣ ኃጢአታችን ይሰረይልናል እናምበክርስቶስ ጻድቅ እንድንሆን ታውጀልናል ።

**አማኞች እንደገና ተወልደዋል**

ዮሐንስ 3:1-8ን አንብብ። ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው?

ኤፌሶን 2:1-5ን አንብብ:: ዳግም በተወለደ አማኝ ላይ ምን ለውጦች ተደርጎላቸዋል?

**አማኞች የዘላለም ሕይወት ስጦታ ተሰጥቷቸዋል::**

በዮሐንስ 3፡16 እና በዮሐንስ 11፡25-26 ካሉት አስደናቂ ተስፋዎች ምን ተማራችሁ?

> ***ዳግመኛ መወለድ-*** ፣ መንፈሳዊ ሕይወትን በመቀበል እንደገና መፈጠር፣ መታደስ ።
>
> ***ዘላለማዊ;*** መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሌለው; ጊዜ የማይሽረው; ማብቂያ የሌለው ቆይታ።

1 ዮሐንስ 5፡11-13ን አንብብና ቁጥር 12ን በራስህ ቃል ጻፍ::

ሁሉም ሰው በሥጋ ሞት ስለሚሞት የዘላለምን ሕይወት ስጦታ ለመረዳት አዳጋች ነው:: ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን ሥጋዊ አካላችን በህመም፣ በእርጅና ወይም በአደጋ ቢሞትም መንፈሳችን ግን ዘላለም ፈጽሞም ለዘላለም የማይሞት ነው ። እንዲያውም ከሞት ተነስተን ለበሽታ፣

ለእርጅና ወይም ለሞት የማይዳርግ አዲስ ሰማያዊ አካል ይሰጠናል !

ከ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡35-58 ስለ ዘለአለማዊ ህይወት ምን እውነቶችን ተማራችሁ?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

*እግዚአብሄር ለህይወታችን ያለው እቅድ ለዘለአለም የሚዘልቅ ስለሆነ በዚህ አለም ላሉ ጊዜአዊ ነገሮች ሙሉ በሙሉ ካልተሟላልን ብለን መታገላችንን ማቆም አለብን። እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ሕይወታችንን ሊባርክ ይፈልጋል፣ ነገር ግን በሰማያዊው አባታችን እና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ወደ ዘላለማዊ መድረሻችን እስክንደርስ ድረስ ፍጹም ደስታ እና እርካታ ላይ አይደረስም።*

> ማጠቃለያ እውነት
> ህይወታችንን ለክርስቶስ አሳልፈን ስንሰጥ፣ ውድ የሆነውን የዘላለምህይወት ስጦታ ይሰጠናል።

**ከእግዚአብሔር ጋር የተመለሰ ኅብረት**

ዮሐንስ 17፡20–23ን አንብብ እና የኢየሱስን ጸሎት ለሁሉም አማኞች ጠቅለል አርገው ።

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

*የተፈጠርነው ከቅዱስ ፈጣሪያችን ጋር በኅብረት እንድንኖር ነው። ሕጉን በመጣሳችን በእርሱ ፊት ለመሆን የማንበቃ ሆንን በዚህም ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንድንለይ ሞት ተፈርዶብናል። በፍቅሩ የተነሳ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለኃጢአታችን ዋጋ ከፍሏል። እርሱ የሞተው እኛ እንድንኖር ነው። ከሞትም የተነሳው በእርሱ ጽድቅ አዲስ ሕይወትን እንድንቀበል ነው ። አሁን እኛ ዋጋ ያለን ክርስቶስ ዋጋ ከፍሎ ነው። ከፈጣሪያችን ጋር ያለን ኅብረት እንደገና የተመለሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በቂ ስለሆነ ነው።*

*ጥቂት ጊዜ በመውሰድ በዚህ ምዕራፍ ክርስቶስ ለአንተ ስላለው ፍቅር፣ ለኃጢያትህ ስለከፈለው መስዋዕትነት እና ካንተ ጋር ግላዊ ግንኙነት እንዲኖረው ስላለው ፍላጎት የተማርከው አሰላስልና አንፀባርቅ። በእምነትህ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረው የትኛው ትምህርት ነው? አብራራ።*

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

ከትምህርቶቹ  የመጀመሪያውን ምዕራፍ ጨርሰሃል እና እንደ ደቀመዝሙር የእምነታችን የማዕዘን ድንጋይ ስለሆነው  የኢየሱስ ክርስቶስን  መንፈሳዊ ትምህርትና እውነቶችን ተምረሃል። እንድትቀጥሉ አበረታታችዋለው! በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ ከሰማያዊ አባትህ  እግዚአብሔር ጋር እንዴት ግንኙነት መመስርትና መኖርም  ምን ማለት እንደሆነ ትማራለህ።

**ምዕራፍ 2**

## የእግዚአብሔር አባትነት

አባት የሚለውን ቃል ስትሰሙ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው ምንድን ነው? በዚህ ምድር ላይ ያለ እያንዳንዱ ሰው ተፈጥሮአዊ አባት አለው የእያንዳንዱም አባት ልዩ ነው ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ከየአባቱ ጋር ያለው አስተዳደግ/ቅርበት/ልምምድ ይለያያል ። አንዳንድ ሰዎች ልጆቻቸውን በጥሩ ሁኔታ ለማሳደግ የተቻላቸውን ሁሉ የሚያደርጉ ጥሩ አባቶች አሏቸው።አንዳንድ አባቶች ደግሞ ጨካኝ ና አረመኔ እንዲሁም ልጆቻቸውን እግዚአብሄር እንዳቀደው ወላጅ ለመሆን የማይፈልጉና የማይችሉ ናቸው።

***ሌሎች ሰዎች የሚያውቋቸው አባቶች ደግሞ ደካማና ቸልተኛ የሆኑ የእግዚአብሄር ቃል የሚያዛቸው ለልጆቻቸው የሚጠበቀባቸውን ስልጠና/ትምህርት መስጠት እንዲሁም በፍቅር የመምራትን ትእዛዝ የማያከብሩ ናቸው ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ አባቶቻቸውን በጭራሽ አያውቁም ምክንያቱም አባቶቻቸው ኃላፊነታቸውን ሙሉ በሙሉ በመተው ቤተሰባቸውን ጥለው ጠፍተዋልና። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ እውነተኛ አባትነት ምን እንደሆነ እንማራለን።***

## ትምህርት 1–የሰማዩ አባታችን

***ከምድራዊ አባትህ ጋር ምንም አይነት ልምድ ቢኖርህ ክርስቶስን አምነንና የመቤዠት ስራውን አንዴ ከተቀበልን እግዚአብሔር ልጁ አርጎ እንደተቀበልን እና እርሱ አባታችን እንደሚሆን መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሰማዩ አባታችን ፍጹም ወላጅ፣ በፍቅሩ እና በእንክብካቤው ታማኝ፣ ለማሰልጠን ብቃት ያለው፣ ለመምራት ጥበበኛ፣ ሁል ጊዜ የሚገኝ እና እርስዎን ወደ ብስለት ለማሳደግ ቁርጠኛ እንደሆነ ይማራሉ።***

### በጉዲፈቻ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ

*ጉዲፈቻ - እንደራስ አድርጎ መውሰድ ወይምመቀበል; ለመጽደቅ; ለመቀበል; እንደ ልጅ፣ ወራሽ፣ ጓደኛ፣ ወይም ዜጋ በምርጫ ወደ ግንኙነት ለመውሰድ።*

ብዙ ጊዜ በሃይማኖታዊ አስተምህሮቶች ውስጥ ሁሉም የሰው ዘር የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ተብለው ነው የሚገለፁት።የተለያዩ ፓስተሮች ወይም ሌላ የሃይማኖት መሪዎች “ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን” ሲሉ መስማትህን ታስታውሳለህ።
ይሁን እንጂ መፅሀፍ ቅዱስ ሁላችንም የእግዚአብሔር ፍጥረታት መሆናችንን ቢያስተምርም የእግዚአብሔር አባትነት ግን ለሁሉም /ዓለም አቀፋዊ እንዳልሆነ በግልጽ ያስተምራል። እግዚአብሔርን “አባት” ብሎ የመጥራት መብት ያለው ማን ነው?

**ዮሐንስ** 1፡12

______________________________________________________________________________________________

_______________________________

______________________________________________________________________________________________

_______________________________

**ገላ** 3፡26

______________________________________________________________________________________________

_______________________________

______________________________________________________________________________________________

_______________________________

**ኤፌሶን** 2፡18-19

ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ልብ ልክ ሉቃስ ወንገል ላይ እንዳለ የአባካኙ ልጅ አባት ታሪከ አይነት መሆኑን በግልፅ ያሳያሉ:: ሉቃስ 15:11-24 ኣንብብ::

ልጁ በደምብ ማሰብ ሲጀምር  ስለ አባቱ ምን ትዝ አለው (ቁጥር 17)?

ልጁ ወደ አባቱ ለመቅረብ ያቀደው እንዴት ነው (ቁጥር 18-19)?

አባቱ እንዴት ተቀበለው (ቁጥር 20-24)?

የሰማይ አባት ለእኛ ያለው ጥልቅ ፍቅር ሊመረመር አይችልም:: እንደ ጉዲፈቻ ቤተሰብ አባልነታችን  ማለቂያ የሌለው ፍቅሩን፣ ትዕግሥቱን እና ደግነቱን ተቀባዮች ነን::

> ማሳረታዊ እውነት
>
> እግዚአብሔርን እንደ አባታቸው በትክክል መጥራት የሚቻሉት ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የሰጡ ብቻ ናቸው። እግዚአብሔር ልጁን የላከውእኛን እንዲቤዠን፣ ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን እና እንደ ራሱ ልጆች አድርጎ በጉዲፈቻ ወደ ቤተሰቡ ሊቀላቅለን  ነው።

## የሚያውቀን አባት

የሰማዩ አባታችን ፈጣሪያችን ስለሆነ፣ እያንዳንዳችንን በግል እና በልዩ ሁኔታ ያውቀናልና ይረዳናል። ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ጥልቅ እውቀት

ብዙ መዝሙሮችን ጽፏል። ከዚህ በታች ያሉትን ምንባቦች ጠቅለል አድርጉ። እግዚአብሔር ምን ያህል ያውቃችኋል?

መዝሙረ ዳዊት 71:6

*መዝሙረ ዳዊት* 103:13-14

*መዝሙረ ዳዊት* 139:1-6

*መዝሙረ ዳዊት* 139:7-12

*መዝሙረ ዳዊት* 139:13-18

እግዚአብሔር ከመወለድህ በፊት አውቆሃል እና በእናትህ ማኅፀን ውስጥ በተለየ ሁኔታ ፈጠረህ። እሱ ወላጆችህን መረጠ እና በህይወታችሁ ውስጥ ያሉትንም ሁኔታዎች ደስተኛም ሆነ አስቸጋሪ እንዲሆኑ ዘንድ አዘዘ ። ባታውቁትም ወይም ባትገነዘብትም ፣ እርሱ እናንተን እየጠበቀ ወደ እራሱ ስቧችኋል ። እርሱ ፈጣሪያችሁ ነው ሳታውቀው በፊት ያወቀህ እና እራስህን ከምታውቀው በላይ የሚያውቅህ ነው።

### *የሚያሠለጥን አባት*

*እንደ አፍቃሪ አባት፣ እግዚአብሔር ልጆቹ ወደ ጠንካራ፣ ጤናማ፣ የበሰሉ ጎልማሶች እንዲያድጉ ይፈልጋል። ለጥንካሬ እና ምሪት በእሱ ላይ ተመስርተን ባህሪውን እንድናንጸባርቅ ይፈልጋል። ወደ ክርስቶስ ከመምጣታችን በፊት፣ ከእግዚአብሔር የራቅን፣ በራስ ወዳድነት እና በኃጢአተኛ ባህሪ የመመላለስ ልማድ ያለን መንፈሳዊ ወላጅ አልባ ልጆች ነበርን። ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበልን በኋላ፣ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ተቀላቅለናል እና በእርሱ በኩል አዲስ ሕይወት ተሰጥቶናል። ነገር ግን አዲስ የተወለዱ ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን በራሳችን ኃይል በመታመን ነገሮችን በራሳችን መንገድ ማድረግን ለምደናል። እኛ ምን ያህል ገለልተኛ፣ ኃጢአተኛ እና አላዋቂ እንደሆንን አናውቅም። ነገር ግን እግዚአብሔር በማያልቀው ጥበቡ እነዚህን ነገሮች በእያንዳንዳችን ህይወት እንዴት እንደሚገልጥ ያውቃል።*

*እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን በቅርበት ያውቃል። ታላቅ ደስታ የሚሰጠን እና ጥልቅ ሀዘን የሚያመጣብንን ያውቃል። የእያንዳንዳችንን ልዩ ባህሪ ማለትም የስብዕናችን የሆኑ ድክመቶች፣ ጥንካሬዎች እና ውስንነቶች ያውቃል። የሚያታልሉንንም ፈተናዎች ያውቃል። እንደ ጥበበኛ አባት፣ እግዚአብሔር በግለሰብ ሕይወታችን ውስጥ ፈቃዱን ሲፈጽም ሁሉንም ነገር ግምት ውስጥ ያስገባል፣ እያንዳንዳችንን በመንፈሳዊ የበሰልን እንድንሆን ያሠለጥናል።*

*እግዚአብሔር እንደ እኛነታችን ይወደናል፣ ነገር ግን እሱ እኛ ባለንበት መንገድ የማይተወን ስለወደደን ነው።* 2ኛ ቆሮንቶስ 3፡18 *እኛ ምን እንመስላለን ይላል?*

እግዚአብሔር በማደጎ ልጆቹ ላይ አዲስ ሥራ ይጀምራል ይህም የማሰልጠን፣ የማስተማር እና እንደ ቤተሰብን እንዲመሳሰሉ ማስተማር ነው ። ልጆቹን ቅድስናውን እያካፈለ በልጁ አምሳል እንዲለወጡ ይናፍቃል።

> ***መቀይር-*** *ቅርጹን ማዛወጥ; ባህሪን/ተፈጥሮን፣ ዝንባሌን፣ ልብን ወይም የማሰሉትን ማዛወጥ፣ ለማዛወጥ*

## ትምህርት 2-የእግዚአብሔር የለውጥ መሳሪያዎች

**ሸክላ ሠሪ እጆቹን እና ልዩ ልዩ መሳሪያዎቹን በመጠቀም ሸክላውን ቅርፅ በማውጣት ወደ ውብ ዕቃ እንደሚስራው/ እንደሚቀይረው ሁሉ እግዚአብሔርም ሕይወታችንን ለመቅረጽ እና ለመቀየር በእጆቹ እና በመሳሪያዎቹ ይጠቀማል።እኛ ለእርሱ የዋህና የፀና ዳሰሳ ራሳችንን አሳልፈን ከሰጠን ውስጣዊ ኃይልና ውበት ያላቸው ሰዎች እንድንሆን ይቀርጸናል።እግዚአብሔር በመለወጥ ሂደት ውስጥ ሶስት ዋና ዋና መሳሪያዎችን ይጠቀማል፦ መጽሐፍ ቅዱስን፣ ፈተናዎችን እና ችግሮችን ፣ እንዲሁም ሌሎች ሰዎችን ነው።**

### መጽሐፍ ቅዱስ

የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ በማንበብ የእምነታችንን መሰረታዊ እውነቶች በመማር በጥበብ፣ በእውቀት እና በእምነት እናድጋለን ።

መዝሙረ ዳዊት 119:105 የእግዚአብሔር ቃል ______________________________ ነው።

ዕብራውያን 4፡12 የእግዚአብሔር ቃል ___________________________________ ነው።

ኤርምያስ 23:29 የእግዚአብሔር ቃል እንደ _______________________________ ነው።

ኢዮብ 23፡12 የእግዚአብሔር ቃል ከ_____________________________________በላይ ሊከበር ይገባዋል።

ኤፌሶን 5፡26 የእግዚአብሔር ቃል ይቀድሳል እና ______________________________.

1ኛ ጴጥሮስ 2፡2 የእግዚአብሔር ቃል ___________________________________ ነው።

ዮሐንስ 5:38-40ን አንብብ። ኢየሱስ ሃይማኖተኛ የሆኑትን አይሁዶች የገሰጸው ለምንድን ነው?

_________________________________________________________________

> *በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትፈልጉትን ለምኑ ይሆንላችሁማል። ብዙ ፍሬ ብታፈሩ በዚህ አባቴ ይከበራል፣እናንተ ደቀ መዛሙርቴ ትሆናላችሁ። ( ዮሐንስ 15:7–8 )*

> *መዛት/መኖር ፦ማንቀጠል; ማነጠት; ሳንለወጥ መቋቋም መቀጠል የተረጋጋ ወይምቋሚ ሆኖ ለመቆየት.*

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በእርሱ እና በቃሉ እንዲኖሩ/እንዲገዙ አዟቸዋል—በትምህርቱ ውስጥ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ኢንዲያስገቡ ዘንድ ። ቃሉን የምናነበው ዝም ብለን ማንበብን በማሰብ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስን እውቀት ለማግኘት አይደለም። ግባችን ኢየሱስን እና ለእኛ ያለውን ፈቃድ በቅርበት ለማወቅ ና መመሪያዎቹን ለመከተል በመፈለግ መሆን አለበት። በእርሱ ቃል ውስጥ ስንኖር፣ ፍላጎቶቻችን የእርሱን ፍላጎት እንዲመስሉ ይጀምራሉ፤ ይህም ምን ልንጠይቅ እንዳለብን ያሳየናል፤ በዚህም ሕይወታችን ሰማያዊ አባታችንን ያስደስታል።

> ማሰረታዊ እውነት
> የእግዚአብሔር ቃል ሕይወታችንን ለማለወጥየሚጠቀምበት ኃይለኛ መሣሪያ ነው።

## ፈተናዎች እና ችግሮች

የአምላክ ቃል ስለሚያጋጥመን ፈተናዎችና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ምን ይላል?
ያዕቆብ 1፡2-4

1ኛ ጴጥሮስ 1፡6-7

መዝሙረ ዳዊት 66:10-12

**በሰማይ የሚኖረው አባታችን ችግሮችንን የሚጠቀመው፦ በራሳችን የምንመራ መሆናችንን ለማሳየት፣ ዓመፃችንን ለማጋለጥ፣ ትምህርት ለማስተማር፣ እምነታችንን እንዲበስልና መንፈሳዊ በረከቶች ወደ ተትረፈረፈበት ቦታ ለማድረስ ነው ። በፈተናዎቻችን ወቅት፣ በጸጋው፣ በፍቅሩ፣ እና በርኅራኄው ማረፍ አለብን። የእግዚአብሄርን አመለካከት ካልተከተልን የእሱን ተግሳጽ አንቀበልም፤ እንዲሁም በህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙን ችግሮች እንዲያሰናክሉን እንፈቅዳለን።**

**እርስዎን ወደ እርሱ ለማቅረብ አሁንም ሆነ በቀድሞ ህይወታችሁ የተጠቀመበት አስቸጋሪ ወይም ህመም የሚያስከትሉ ሁኔታዎችን አስታውስ።**

| መሰረታዊ እውነት |
| --- |
| ፍቃደኛ ከሆንን እግዚአብሔር በፈተናዎቻችን ተጠቅሞየ ልጁን ሜልክ እንድንማስል ይቀይረናል። |

### ሌሎች ሰዎች

እግዚአብሔር ሰዎች እንዲመክሩን እና እንዲያበረታቱን በሕይወታችን ያስቀምጣል። በእርሱ ላይ ብቻ መተማመናችንን አንድናስቀምጥ ዘንድ ጌታ መጥፎ ሰዎችንም አንድንማርባቸው ዘንድ ያስቀምጣል። በሚቀጥሉት ጥቅሶች ውስጥ ስለ ሌሎች ሰዎች ምን ይማራሉ?

ምሳሌ 27፡17

ሮሜ 1፡11-12

መዝሙረ ዳዊት 41:9-12

2 ጢሞቴዎስ 4:16-17

በእምነትህ እንድትበረታ እግዚአብሔር በህይወታችሁ ውስጥ ያስቀመጠው ሰው ማን ነው?

በህይወታችሁ ውስጥ ታጋሽ እና አፍቃሪ እንድትሆኑ የሚሞግትዎ ማነው?

_______________________________________________________________________________

_________________________________

_______________________________________________________________________________

_________________________________

_______________________________________________________________________________

_________________________________

## ትምህርት 3- የእግዚአብሔር ተግሣጽ

***ተግሣጽ የሚለውን ቃል ስታስቡ ምን ትዝ ይላችኋል? ብዙውን ጊዜ ከፍቅር እና ከእንክብካቤ ጋር የተያያዘ ሞቅ ያለ ስሜት የሚቀሰቅስ ቃል አይደለም። አብዛኞቹ የተግሣጽ ልምዶቻችን የተበሳጨ ወይም የተናደደ ወላጅ ምስሎች ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ተግሣጽ ከባድ፣ የማይመች እና አንዳንድ ጊዜም የሚያሠቃይ ነው። በክፍት እጆች ለመቀበል የምንዘጋጅበት ነገር አይደለም። ሆኖም፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሚገሥጸን ይነግረናል።***

*__ተግሣጽ/ቅጣት__ -ማስተማር; ራስን መግዛትን ወይም ለተሰጡት መሟያዎች/ሁኔታዎች መታዘዝን ማሰልጠን; በማስተማር እና በልምምድ ማደግ።*

እግዚአብሔር ስለሚሰጠው ተግሣጽ መስበክ በተለይ ተወዳጅ አይደለም። አብዛኛው ሰው በእግዚአብሔር ፍቅርና ይቅርታ ላይ ማተኮር ይመርጣል—እነዚያም መልካም ስሜት እንዲሰማን የሚያደርጉን የእግዚአብሔር ባህሪያት ናቸው። ነገር ግን አፍቃሪ የሆነው የሰማይ አባታችን ሁልጊዜ መልካም ስሜት እንዲሰማን ለማድረግ ፍላጎት የለውም። እርሱ እንደርሱ፣ መልካም እንድንሆን ይፈልጋል።

ዕብራውያን 12:5-11ን አንብብ።
ጌታ የሚቀጣው ማንን ነው (ቁጥር 6)?

_______________________________________________

ይህ ቅጣት ምን ያረጋግጣል (ቁጥር 8)?

_______________________________________________

ለምን ይቀጣናል (ቁጥር 10)?

_______________________________________________

ቅጣት ምን ውጤት ያስገኛል (ቁጥር 11)?

_______________________________________________

እግዚአብሔር በትዕግሥትና ያለማቋረጥ  እርሱን ደስ የማያሰኙትን አስተሳሰቦች፣ አመለካከቶች እና ድርጊቶች ያጠራል፣ "በሰላማዊ የጽድቅ ፍሬ" ይተካቸዋል።
ገላትያ 5፡22–23ን አንብብ እና እግዚአብሔር በህይወታችን ሊያፈራ የሚፈልገውን ፍሬ ዘርዝር።

_______________________________________________
_______________________

_______________________________________________
_______________________

ፊልጵስዩስ 1:6ን ጠቅለል አድርገህ አስቀምጥ ።

እግዚአብሔር መልካም ፍሬን እንድናፈራ ህይወታችንን እንደሚለውጥ ማረጋገጫ አላችሁ። አንተን ወደ እርሱ አምሳል ለመቅረጽ በንቃት እየሰራ ነው። ነገር ግን እርሱ ሥራውን ሲሰራ እኛ በቸልተኝነት መቆም እንደማንችል መረዳት አለብን። እንዲለውጠን በንቃት የመቀበል እና ለሱ ተግሣጽ የመገዛት ሃላፊነት አለብን ።

የእግዚአብሔር የመለወጫ መሳሪያዎች—መጽሐፍ ቅዱስ፣ ፈተናዎች እና ችግሮች፣ እና ሌሎች ሰዎች ሲሆኑ — እኛጋ አብሮን በሀይል የሚኖር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ክርስቶስን ለመምሰል ገና መሆናችንን ና ፈቃዱን አለማወቃችን እና ከእሱ መራቃችንን ያሳያሉ። የአምላክን ፍቅራዊ ባሕርይ በማያንጸባርቅ መንገድ የሆንክበትን ጊዜ ታስታውሳለህ? መጽሐፍ ቅዱስን ስታነብ ወይም ስብከት ስትሰማ ሲወቅስህ ተሰምቶህ ያውቃል ? ለመከራ ወይም ለአንድ ሰው ኃጢአትን በተሞላ መንገድ ምላሽ ስትስጥ መንፈስ ቅዱስ ሲወቅስህ ተሰምቶህ ያውቃል? እግዚአብሔር እርስዎን በሚገባ ያውቃል በህይወቶ ውስጥ ገና ለውጦ ያልጨረሰውን ቦታውንም እንዲሁ። ነገር ግን ለውጥን ለማግኘት የእርሱን የለውጥ ዘዴዎች መቀበል አለብህ። የኃጢአት ተፈጥሮህን ለመለወጥ መሳሪያዎቹን እርሱ ሲገልጥ፣ ኃጢአትህን ለእርሱ መናዘዝ፣ ይቅርታውን መጠየቅ እና ኃጢአት ከሰራህባቸው ሰዎች ይቅርታን መጠየቅ አለብህ። ከእግዚአብሔር ተግሣጽ ጋር መተባበር ማለት ይህ ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለውጥ እና መንፈሳዊ እድገት የምትለማመዱበት ብቸኛው መንገድ በዚህ ንቁ ተሳትፎ ነው።

ከ1ኛ ዮሐንስ 2፡6 እና ኤፌሶን 5፡1–7 ምን ተማራችሁ?

ክርስቶስን የማይመስሉ የሕይወቶ ክፍሎች (ሀሳቦች፣ ቃላት፣ ወይም ድርጊቶች) አሉ ? የክርስቶስን መምሰል አለመቻልህ በእግዚአብሔር የመለወጥ መሳሪያዎች ሲጋለጥ ወዲያው፣ በንስሃ፣ በጸሎት፣ ቃሉን በማጥናት እና ተጠያቂነትን በመሻት ማጥፋት አለብህ።
ከሮሜ 12፡1–2 እና ኤፌሶን 5፡17 ምን ትማራለህ?

በሁሉም የሕይወትህ ዘርፎች (ከእሱ ጋር ያለህ ግንኙነት፣ በትዳር ጓደኛህ፣ በልጆችህ፣ በቤተሰብህ እና በጓደኞችህ፣ በገንዘብህ እና በሌሎች ላይ ባለህ ግንኙነት) የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? አለማወቅህ ሲገለጥ፣ በሁሉም የህይወታችሁ ዘርፍ በንስሀ፣ በጸሎት፣ ቃሉን በማጥናት እና የሚረዳህን ደቀ መዝሙር በማግኘት የእርሱን የመልካምነት እና ፍፁምነት ፈቃዱን እውቀት በንቃት መፈለግ አለብህ።

ከሮሜ 6፡1–4፣ ያዕቆብ 1፡22–25 እና 1 ጴጥሮስ 1፡13–16 ምን ትማራለህ?

ለእግዚአብሔር ለሰጠው ሥልጣን በትህትና እየተገዛችሁ ነው ወይስ ኃጢአተኛ የሆነውን ባህሪና አለመታዘዝን እያጸደቃችሁ ነው? ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ የራሳችሁን ቅድመ ሁኔታ አስቀምጣችኋል? እግዚአብሔር በለውጥ መሣሪያዎቹ ሲገለጥ፣ በንስሐ ለእርሱ ሥልጣን በንቃት መገዛትና የመታዘዝ ሕይወት ለመኖር ትሕትናና ኃይልን መጠየቅ አለባችሁ። ተጠያቂነትን መፈለግም ይረዳል ።

***መግረፍ-*** *በከፍተኛ ሁኔታ ለመቅጣት ወይም በመጥፎ ሁነታ ሙዳት; ለሚሪም ዓላማ ኃጢአትን ወይም ጥፋቶችን ለመቅጣት.*

የእርሶ ለውጥ ጊዜ ይወስዳል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ጥሩ፣ ታጋሽና ታማኝ አባት ነው። በእናንተ ውስጥ የጀመረውን ሥራ እንደሚጨርስ ቃል ገብቷል። ሆኖም፣ ለእግዚአብሔር ተግሣጽ ለመገዛት እምቢ ካላችሁ፣ የእርሱን መግረፍ እየጠየቃችሁ ነው።
ዕብራውያን 12:6ን አንብብ። እግዚአብሔር ልጆቹን የሚገስፀው እና የሚገርፈው ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ይወዳችኋል እናም ከመጠን በላይ ሊባርክህ ይፈልጋል። ነገር ግን የእሱን ተግሣጽ ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆናችሁ፣ ሊሰጣችሁ የሚፈልገውን ደስታና ሰላም አታገኙም። በምትኩ፣ ድብርት፣ ፍርሃት፣ ብስጭት፣ ጉድለቶች እና ጥርጣሬ ያጋጥምዎታል። ህይወታችሁ የመንፈስ ፍሬ ይጎድለዋል እናም የስጋ ፍሬዎችን ማፍራ ት ይጀምራል።
ገላትያ 5፡19-21ን አንብብና ለአንተ ከሚታዩ የሥጋ ፍሬዎች መካከል ጥቂቶቹን ዘርዝር።

__________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________

የእግዚአብሔርን ሲቀጣን፣ ለሥቃዩ ሌሎች ሰዎችን ወይም አስቸጋሪ ሁኔታዎቻችን መወንጀል/መውቀስ ተፈጥሯዊ ነው። *ይህ ውሸት ከሰይጣን ወይም ከራሳችን የሚመጣ ነው፣ ለእግዚአብሔር ትምህርት ለመታዘዝ ያለን አመጽ ና የግል ተጠያቂነት ላለመውሰድ የምናምነው ነው።*ልጆቹን መግረፍ ለእግዚአብሔር ደስታን አያመጣም ነገር ግን እውነተኞች ከሆንን አንዳንድ ጊዜ እሺ እንድንል ለማነሳሳት መጠነኛ ስቃይ እንደሚያስፈልገን መቀበል አለብን ። ትኩረታችሁን ለመሳብ እና በእናንተ ውስጥ የጀመረውን ሥራ ለመጨረስ የሰማዩ አባታችሁ ስለሚወዳችሁ ተፅናኑ ።

## ትምህርት 4—የእግዚአብሔር የርህራሄ እንክብካቤ ተስፋዎች

የሰማዩ አባታችን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ለተሰጠ ህይወት ሙሉ ሀላፊነት ለመውሰድ ዝግጁ ነው። በእርሱ ጥንቃቄ በተሞላበት እንክብካቤ ተከበናል።

መዝሙረ ዳዊት 91:4 ከእኛ በላይ የእርሱ ______________________________ ናቸው።

ዘዳግም 33፡27። ከእኛ በታች የእርሱ ______________________________ ናቸው።

መዝሙረ ዳዊት 34:7 በ______________________________ ______________________________ተከበናል።

ፊልጵስዩስ 4፡6-7 ልባችን እና አእምሯችን የሚጠበቁት በ____ ______________________________ ነው።

ከሰማዩ አባታችን የምንቀበለው ፍቅር እና እንክብካቤ በእርግጥ በሰጠን ተስፋዎቹ ማለተም በእርሱ ህልውና፣ እርዳታ እና ጥበቃውን ውስጥ በግልጽ ይታያል።

**የእግዚአብሔር የመገኘት ተስፋ**

ስለ እግዚአብሔር ያልተቋረጠ ቅርብነት የተማርከውን በአጭሩ ጻፍ።
መዝሙረ ዳዊት 23:4

______________________________________________________________________
______________________________
______________________________________________________________________
______________________________
______________________________________________________________________
______________________________

መዝሙረ ዳዊት 121:1-5

______________________________________________________________________
______________________________
______________________________________________________________________
______________________________

መዝሙረ ዳዊት 139:7-10

______________________________________________________________________
______________________________
______________________________________________________________________
______________________________

ዕብራውያን 13፡5-6

**እንደ እግዚአብሔር ልጆች፣ መቼም ብቻችንን አይደለንም። አባታችን ሁል ጊዜ ንቁ እና ቅርብ ነው ።**

| |
|---|
| መሰረታዊ እውነት<br>በእርሱ ርኅራኄ የተሞላ እንክብካቤ፣ የሰማዩ አባታችን ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ነው። |

**የእግዚአብሔር እርዳታ ተስፋዎች**

የሚከተሉት ጥቅሶች የእግዚአብሔርን ለጋሽነት/ሰጪነት መታመን በተመለከተ ምን ያስተምሩዎታል?

ማቴዎስ 6፡25-26

ሮሜ 8፡32

ፊልጵስዩስ 4፡19

ማቴዎስ 7:7-11ን አንብብ። በቁጥር 11 መሰረት አብ ለሚጠይቁት ምን አይነት ስጦታዎችን ይሰጣል?

እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚሰጠው መልካም ስጦታዎችን ብቻ ነው። ከፍቅሩ እና ከጥበቡ የተነሣ፣ የምንለምነውን ብዙ ጊዜ ይከለክላል እና ይልቁንም የሚያውቀውን ለኛ የተሻለውን ይሰጠናል። መንገዱን ባንረዳም እንኳን እነዚህ በቸርነቱ እና በጥበቡ የምንታመንባቸው እድሎች ናቸው።

ማቴዎስ 6:24—34ን አንብብ። እግዚአብሔር የሰማይ ወፎችን እና የሜዳውን ሣር የሚንከባከብ ከሆነ በእርግጥ የሚወዳቸውን ልጆቹን እንደሚንከባከብ ማመን አለብን። ስለ እነዚህ ለጊዜያዊ ነገሮች እንዳንጨነቅ ታዝዘናል። በቁጥር 32 ላይ፣እንደዚህ አይነት ጭንቀቶች  እግዚአብሔርን የማያውቁት ወይም  የአሕዛብ ጭንቀት እንደሆኑ እንማራለን።

በአሁኑ ጊዜ ያሉብህ ጭንቀቶች፣ ስጋቶች ወይም እንክብካቤዎች ምንድናቸው ?

በማቴዎስ 6፡33 መሠረት ለጭንቀት  መድኃኒቱ ምንድን ነው?

እግዚአብሔርን የግድ መፈለግ አለብን ከእርሱ ጋር ያለንን ግላዊ ግንኙነትን ቀዳሚ ተግባራችን ማድረግ አለብን። ሁሉን ነገር ለእርሱ የመስጠት እና በነገር ሁሉ በእርሱ የመታመንን ልማድ ስናዳብር፣ እሱም ጭንቀት የሚፈጥርብንን  ይህን ሃጢአታዊ ልማድ እንድናሸንፍ ያስችለናል።

| |
|---|
| መሰረታዊ እውነት |
| በእርሱ ርኅራኄ የተሞላ እንክብካቤ፣ የሰማዩ አባታችን ሁሉን ምፍላጎታችንን ያሟላልናል። |

**እግዚአብሔር እንደሚጠብቀን የገባው ቃል**

መጽሐፍ ቅዱስ "አትፍሩ" የሚሉ 365 ትዕዛዞችን ይዟል። ሻቭኃይል ያለው የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን በእርሱ ውስጥ በሰላም

*ማረፍ እንችላለን። ከሚከተሉት ጥቅሶች ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ ምን ትማራላችሁ?*

*ኢሳይያስ* 54:17

*መዝሙረ ዳዊት* 91:1-12

*መዝሙረ ዳዊት* 121:5-8

> ማስረታዊ እውነት
> በእርሱ ርኅራኄ የተሞላ እንክብካቤ፣ የሰማዩ አባታችን ይጠብቀናልና ይንከባከበናል።

የሰማዩ አባታችን ተግሣጹን፣ ጥበቃውን እና እርዳታውን ሊያረጋግጥልን በቃሉ ብዙ ርቀት ሄዷል። ህይወታችንን እና ጭንቀታችንን ሁሉ በእርሱ ጥበቃ ላይ አደራ በመስጠት በእምነት ምላሽ መስጠት አለብን። የእግዚአብሔር ክብር፣ ኃይሉ እና ሉዓላዊነቱ ፍጥረቱን ሲፈጥር የተገለጠ ሲሆን፣ የመለኮታዊ ባህሪው ጥልቀት ደግሞ በአባትነቱ ተገልጧል። የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ትዕግስት፣ ደግነት፣ምህረት እና ቸርነት ከእኛ ከልጆቹ ጋር ባለው ግንኙነት ተገልጧል።

ከሚከተሉት ጥቅሶች ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ምን ይማራሉ?
**1ኛ ዮሐንስ** 3:1

2ኛ ጴጥሮስ 3:9

ኤፌሶን 1:3-6

2ኛ ቆሮንቶስ 1:3-4

እንደ  እግዚአብሔር የማደጎ ልጆች እንደመሆናችን  መጠን እርሱ ያለውን ሁሉ ወራሾች እንሆናለን። የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ርስታችን ሀብት ምን ይላሉ?

መዝሙረ ዳዊት 50:10-12

ሐጌ 2፡8

1 ጴጥሮስ 1:3—4ን አንብብ። ርስታችን የት ነው?

አንተ የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ መሆንህ ለራስህ ባለህ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው?

ይህ ምእራፍ ስለ እግዚአብሔር የሰማዩ አባት ያለዎትን ግንዛቤ እንዲጨምር እንደረዳው ተስፋ አደርጋለሁ። የሚቀጥለው ምዕራፍ የሚያተኩረው በሌላ የእግዚአብሔር ስጦታ መንፈስ ቅዱስ ላይ ነው፣ በተለይ ንስሃ ለገቡ እና ክርስቶስ ኢየሱስን የግል አዳኝ አርገው ለተቀበሉ ነው ።

## *ምዕራፍ 3*

## *መንፈስ ቅዱስ*

*በካቶሊክ ቅዳሴ ላይ ተቀምጬ ቄሱ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲጠቅሱ መስማቴን አስታውሳለሁ:: ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር ግን "እሱ" በሆነ መንገድ አስፈላጊ እንደሆነ አውቃለሁ:: በመንፈሱ ዙሪያ ያለው ምስጢር ለቀጣዮቹ አስራ አምስት ዓመታት በህይወቱ ቆየ :: ክርስቶስን እንደ ጌታ በተቀበልኩበት ጊዜ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በሀይል ቢያገኘኝም፣ነገር ግን በወቅቱ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም :: እንደ አለመታደል ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጉዳይ ብዙ ግራ መጋባት አለ:: ብዙዎች "እሱ" ከእግዚአብሔር የሚመነጨው ተጽዕኖ የሚፈጥር ወይም እግዚአብሔር ለክርስቲያኑ የሚያካፍለው/የሚሰጠው ኃይል ነው(ክርስቲያን የሆነ ከእግዚአብሔር የሚቀዳው ሀይል ) ብለው ያምናሉ :: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ የሚያስተምረውን መማር ስጀምር ብዙም ሳይቆይ ማን እንደሆነ ተገነዘብኩ::*

### *ትምህርት 1– መንፈስ ቅዱስ ማን ነው ?*

*መንፈስ ቅዱስ እንደ ኢየሱስ ሁሉ የእግዚአብሔር አካል ነው፣በኃይልና በክብር እኩል ነው፣ የሥላሴ አንዱ አካል ነው ፣የሚንቀሳቀሱትም እንደ አንድ ነው :: እግዚአብሔር ራሱን ከልጆቹ የሚያገናኘው እንዲሁም ጥልቅ የሰውን ልብ ኃጢአት በመግለጥ ለልጆቹ የሚናገናገርበት መንፈስ ነው :: ልክ እንደ አብ እና ወልድ መንፈስ ቅዱስም ዘላለማዊ በሁሉም ቦታ በአንድ ጊዜ መገኘት የሚችል (በሁሉም ቦታ፣ በማንኛውም ጊዜ)፣ ያልተገደበ ሀይልና ስልጣን ያለው (ሁሉም ስልጣን ያለው) እና ገደብ የሌለው እውቀት ያለው (ወሰን የሌለው አዋቂነት ፣ጠልቆ መረዳተ ያለው)ነው ::*

የሚከተሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን ይላሉ ?
ዕብራውያን 9፡14 መንፈስ ቅዱስ ________________________________ ነው።
መዝሙረ ዳዊት 139:7-10 መንፈስ ቅዱስ ________________________________ ነው።
ሉቃስ 1፡35። መንፈስ ቅዱስ ________________________________ ነው።
1ኛ ቆሮንቶስ 2፡10-11 መንፈስ ቅዱስ ________________________________ ነው።

በተጨማሪም በሚከተለው ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተገለጡ የባህርይ መገለጫዎች አሉት።
እሱ የራሱ ፈቃድ አለው (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡11) ።

ይወዳል (ሮሜ 15፡30)

ያዝናል (ኤፌሶን 4፡30)።

ሊዋሹት ይችላሉ (ሐዋ. 5፡3)።

አብዝቶ በቅናት እኛን ይፈልገናል (ያዕቆብ 4፡5)።

ሊያረካን ወይም ልንጫነው እንችላለን (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡19)።

የሰው ልጅ አዳኙን ባለመቀበሉ ያዝናል (ዕብ 10፡29)።

ይናገራል (1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1)

| ማስረታዊ እውነት |
|---|
| መንፈስ ቅዱስ ግልጽ ያልሆነ የጠፈር ኃይል ወይምተራ ተጽዕኖ አድራጊ አይደለም። እርሱ ማኅኮታዊ አካል ነው። እርሱ እግዚአብሔር ነው። |

እርሱ እውነት ነው (1ኛ ዮሐንስ 5፡6)።

ትምህርት 2—የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

## መንፈስ ቅዱስ አዲስ ውልደትን ይሰጣል

መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት የምናገኝበትን መንገድ ያቀርባል። ኢየሱስ ተከታዮቹ የመንፈስን ዳግም አፈጣጠር ሥራ እንዲረዱት ፈልጎ ነበር። ዮሐንስ 3፡1-8ን ያንብቡ።

ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

ኢየሱስ እያንዳንዱ ወንድና ሴት ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ሁለት ልደቶችን ሊያገኙ እንደሚገባ አስተምሯል። አንደኛው ሥጋዊ ውልደት (ከውሃ) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መንፈሳዊ ውልደት (ከመንፈስ) ነው ። ኒቆዲሞስ መንፈስ ቅዱስን እንዲረዳ ዘንድ፣ ኢየሱስ እርሱንና ስራውን በቁጥር 8 ከነፋስ ጋር አመሳስሎታል።

- ነፋሱ ወደ ፈለገበት ይነፍሳል፣ እንዲሁም መንፈሱ ሉዓላዊ እና ነጻ ነው፣ እና ማንም አይቆጣጠረውም። እንደሻው ይሰራል።
- ነፋሱ የማይታይ ቢሆንም ኃይለኛ ነው። ነፋሱን ማየት አይችሉም፣ነገር ግን ውጤቶቹ ይታያሉ፣ እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ የማይታይ ነው፣ ነገር ግን የኃይሉ ማስረጃ በግለሰብ ሕይወት እና ሁኔታ ውስጥ ይታያል።
- በመጨረሻም፣ አየር ሕይወትን የሚሰጥ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም ሕይወትን ይሰጣል።

በሕይወታችን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራን በተመለከተ ከሚከተሉት ጥቅሶች ምን ይማራሉ?
የዮሐንስ ወንጌል 6፡63

____________________________________________________________________________
______________________________

____________________________________________________________________________
______________________________

____________________________________________________________________________
______________________________

ቲቶ 3፡5

____________________________________________________________________________
______________________________

____________________________________________________________________________
______________________________

____________________________________________________________________________
______________________________

## መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን ይቀይራል

መንፈስ ቅዱስ የማይታይ ነው፣ነገር ግን ኃይለኛ ነው፣ በሁሉም አማኞች ልብ ውስጥ ለመኖር ና አዲስ ህይወትን

ሊያካፍል የሚመጣ ነው። እሱን ማየት አንችልም፣ ነገር ግን የእሱ መገኘት የሚያስከትላቸው ውጤቶች በህይወታችን ውስጥ ይታያሉ። እያንዳንዱን አማኝ ወደ ክርስቶስ አምሳል የመቀየር ስራ የእርሱ ነው። ከሚከተሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈስ ምን ተማራችሁ?

2ኛ ጴጥሮስ 1፡3-4

______________________________________________________________________________
________________________________

______________________________________________________________________________
________________________________

______________________________________________________________________________
________________________________

ሕዝቅኤል 36:26-27

______________________________________________________________________________
________________________________

______________________________________________________________________________
________________________________

______________________________________________________________________________
________________________________

1ኛ ቆሮንቶስ 2፡12-16

______________________________________________________________________________
______________________________________________________________________________
_____________________________

በክርስትና እምነት ውስጥ ያለው አንዱ ጥሩ ነገር አምላክ ራሳችንን እንድንለውጥ ወይም ራሳችንን እንድናሻሽል እየጠየቀን አይደለም። አኛ ውስጠ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እኛን ከውስጥ ወደ ውጭ ይለውጠናል! በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ በየቀኑ ከእርሱ ጋር መቀራረብን በመፈለግ እና በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ከእሱ ተግሣጽ ጋር በመተባበር እንሳተፋለን። በግላዊ አምልኮ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ፣ ልቡን፣ አእምሮውን እና ተፈጥሮውን ይሰጠናል። በየቀኑ የግድ ለእርሱ እጅ መስጠት፣ መገዛት እና መተባበር አለብን።

***ተገዛ***- *ለሌላው ስልጣን ወይም ይዞታ መገዛት; ለመልቀቅ; ሙሉ በሙሉ መተው*

***ማስጠት***- *የሌላውን ውሳኔ ወይም ፍርድ ሚፈጸም; ከስር መቀመጥ ወይም ማስቀመጥ;*

***ተባበሩ***- *ከሌላ ጋር በጋራ ማስራት ወይም ማከናወን።*

መሰረታዊ እውነት

መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ
አማኝ ውስጥ ለመኖር የሚመጣው፣
አዲስ ሕይወትን ሊያካፍል እና
እኛን ወደ ክርስቶስ አምሳል
ሊቀይር ነው።

**ትምህርት 3–መንፈስ ቅዱስ ረዳታችን ነው።**

ኢየሱስ ከመታሰሩ ከሰዓታት በፊት፣ ደቀ መዛሙርቱን የመጨረሻውን እራት እንዲበሉ ወደ ላይኛው ክፍል ወሰዳቸው። ዮሐንስ 13—17 ክርስቶስ ከስቅለቱ በፊት አብረው ባደረጉት የመጨረሻ እራት ወቅት ያስተማራቸውን ሁሉ ይገልፃል። ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ስለሚልክው ስለ መንፈስ ቅዱስ ለተከታዮቹ ነገራቸው። ከሚከተሉት ምንባቦች ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን ተማራችሁ?

ዮሐንስ 14፡16-27

______________________________________________________________________

______________________

______________________________________________________________________

______________________

______________________________________________________________________

______________________

ዮሐንስ 15፡26

______________________________________________________________________

______________________

______________________________________________________________________

______________________

ዮሐንስ 16፡7-15

______________________________________________________________________

______________________

______________________________________________________________________

______________________

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር እና በእነርሱ ውስጥ የሚሆን ሌላ ረዳት እንደሚሆን ነገራቸው።

መንፈስ ቅዱስ እንዴት ይረዳናል?

መንፈስ ቅዱስ ይረዳናል __________________________________ (ሮሜ 8፡26-27)።

መንፈስ ቅዱስ የእኛ ____________________________________ (ሮሜ 8፡14፤ ዮሐንስ 16፡13)።

መንፈስ ቅዱስ የእኛ ____________________________________(1ኛ ዮሐንስ 2፡27፤ ዮሐንስ 14፡26)።

መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል ________________________________________________

(ሉቃስ 12፡11-12)።

**ትምህርት 4 የመንፈስ ሙላት**

ለመንፈስ ቅዱስ ስንገዛ እርሱ ይሞላናል፡፡ በኤፌሶን 5፡18 ላይ ይህ “መሙላት” ከመስከር ጋር ተነጻጽሯል፡፡ አንድ ግለሰብ የወይን ጠጅ ሲወስድ ከራሱ ባልሆን በአልኮሉ ተጽእኖ ውስጥ ይወድቃል፣ በተመሳሳይ መልኩ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ስንገዛ እርሱ በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል እንዲሁም ይነካናል፡፡ እሱ ሀሳቦቻችንን፣ውስጣዊ ግፊቶችን እና ምኞቶቻችንን ያጠራል፣ ይህም የባህሪያችንን ለውጥ ያመጣል፡፡

ዮሐንስ 7:37—39ን አንብብ፡፡ በቁጥር 37 ላይ፣ ኢየሱስ በመንፈስ የተጠሙትን ምን ሁለት ነገሮች እንዲያደርጉ ጠየቃቸው?

__________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________

ቀጥሎ ከነሱ ሕይወት ምን ይፈሳል ይላል (ቁጥር 38)?

__________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________

በኢየሱስ አምነን መጠማታችንን እውቅና ስንሰጥ እንዲሁም ከሱ ስንቀበል/ስንጠጣ በመትረፍረፍ ይሞላናል ፡፡

በኤርምያስ 2:13 መሠረት እስራኤላውያን ምን ሁለት ክፉ ነገር ሠሩ?

__________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________

የእስራኤል ልጆች እግዚአብሄር ፍላጎታቸውን እንደሚያሟላላቸው ከመመካትይልቅ እርሱን ትተው ሌሎች ምንጮችን እንዲያረኩዋቸውና አንዲያትረፈርፉዋቸው ፈለጉ፡፡

አንተ የፈጠርካቸው ከክርስቶስ ውጪ ያሉህን ጉድጓዶችን ታውቃለህ ? ከክርስቶስ ውጭ እርካታን ለማግኘት እንዴት እንደምትሞክር ግለጽ፡፡

__________________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________________
___________________________

________________________________________________________________________________________
___________________________

________________________________________________________________________________________
___________________________

________________________________________________________________________________________
___________________________

**የመንፈስ ፍሬ**

መንፈስ ቅዱስ የእኛን መስጠት በቅናት ይፈልጋል። እሱ ክብር ያለው ነው ፍቃዳችንን አይጋፋም ወይም እንድንታዘዘው አያስገድደንም ። ኢየሱስ በፈቃዱ ራሱን ስለ ኃጢአታችን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። በምላሹ፣ ንስሐ የገቡ፣ ይቅርታ የተደረገላቸው ኃጢአተኞች በፈቃደኝነት ለእርሱ በመገዛት ምላሽ መስጠት አለባቸው። በየቀኑ ለመንፈስ ስንገዛ፣ እርሱ የሚትረፈረፈውን ይሞላናል። የእሱ የሕይወት ውሃ ከውስጥ ይፈልቃል እና በህይወታችን ፍሬ ያፈራል ።

ይህ ፍሬ በገላትያ 5:22-23 ተገልጧል። ፍሬውን ከዚህ በታች ይዘርዝሩ.

________________________________________________________________________________________
___________________________

________________________________________________________________________________________
___________________________

በሕይወታችሁ ውስጥ ምን የተለየ የመንፈስ ፍሬ ይጎድላል ?

________________________________________________________________________________________
___________________________

በህይወታችን ውስጥ ያለው የመንፈስ ፍሬ መለኪያ በእርሱ ላይ ካለን መተማመን ደረጃ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። የፍራፍሬ ዛፍ ፍሬ ለማፍራት ፀሀይ፣ ውሃ እና ጤናማ አፈር እንደሚፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅም ፍሬውን ለማፍራት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍ አለበት። እግዚአብሄርን አሁን መጠየቀ ያለብን የህይወታቸን ሁሉም ዘርፎች የእርሱን መንገድ እንዲይዝ እና ልባችን በመንፈስ ፍሬዎች እንዲሞሉ ነው ።

**የመንፈስ ስጦታዎች**

መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ የመንፈስን ፍሬ ማፍራት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ስጦታዎችንም ይሰጠናል። የመንፈስ ስጦታዎች እንዲሁ ሊገኙ አይችሉም እንዲሁም ስለታማኝ አገልግሎት አይሰጥም። ከተፈጥሯዊ ችሎታዎቻችን፣ ስብዕናዎቻችን ወይም የባህርይ ችሎታ ጋር የተገናኙ አይደሉም። እነዚህ ስጦታዎች ለክርስቶስ አካል ለሆኑ ብቻ የተሰጡት በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው። ሦስት የአዲስ ኪዳን ምዕራፎች ለመንፈሳዊ ስጦታዎች ትምህርት ብቻ የተሰጡ ናቸው።

1ኛ ቆሮንቶስ 12—14ን አንብብ።

***በ1 ቆሮንቶስ 12:7 እና 11 መሠረት መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚሰጠው ለየትኞቹ የክርስቶስ አካሎች ነው?***

***መንፈሳዊ ስጦታዎችን የምንጠቀምበት ዋና ዓላማ ምን መሆን አለበት? ( 1 ቆሮንቶስ 14:12, 26 ተመልከት።)***

***የመንፈስ ስጦታዎች በትዕቢት እና በራስ ወዳድነት ወይም ለወንድሞች ፍቅር በሌለው ሁኔታ ስንጠቀም ውጤቱ ምንድ ነው? ( 1 ቆሮንቶስ 13:1—2 ተመልከት።)***

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በመጠቀም ጊዜ ሊደርስ ስለሚችል አላግባብ የሆነ አጠቃቀም ምክንያት ብዙ የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ይርቃሉ። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡1 ላይ ስለ ስጦታዎች ምን የማስጠንቀቂያ ቃላት ሰጥቷል?

***መታነፅ*** *፦ሥነ ምግባራዊ፣ አእምሯዊ ወይምመንፈሳዊ መሻሻል፣ ማንባት፣ መሚያ.*

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10, 28 የሚገኙት የመንፈስ ስጦታዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፣ ለእያንዳንዳቸውም ተጨማሪ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅስ አብሮ አለ፦

የጥበብ ቃል (የሐዋርያት ሥራ 6:10)

የእውቀት ቃላት (1ኛ ቆሮንቶስ 1:5፤ ሮሜ 15:14)

ልዩ እምነት (የሐዋርያት ሥራ 3፡1-16)

የፈውስ ስጦታዎች (ማርቆስ 6:13፤ ያዕቆብ 5:14–16)

ተአምራትን ማድረግ (የሐዋርያት ሥራ 5:12-15፤ ዕብራውያን 2:4)

ትንቢት ( ዘጸአት 7:1, 2፣ ኤርምያስ 1:9፣ 1 ቈረንቶስ 14:1-5, 24, 25, 39 )

መንፈስን መለየት (የሐዋርያት ሥራ 13:9–11፤ ዕብራውያን 5:14)

ልሳናት (1 ቆሮንቶስ 14:1–5፤ ሥራ 2:3–11፤ ሮሜ 8:26, 27)

የልሳናት ትርጓሜ (1 ቆሮንቶስ 14:13, 27, 28)

እርዳታዎች (የሐዋርያት ሥራ 20:35)

ያስተዳድራል (1 ጢሞቴዎስ 5:17)

የመንፈስ ስጦታዎች ለእያንዳንዱ የክርስቶስ አካሎች ይከፋፈላሉ። የምታውቅ ከሆነ የአንተ መንፈሳዊ ስጦታዎችህ ምንድን ናቸው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ማሳረታዊ እውነት

ለመንፈስ ቅዱስ ስንገዛ እርሱ በውስጣችን መንፈሳዊ ፍሬ ያፈራል፣ እናምለእኛ የተሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይገለጣሉ።

**ትምህርት 5–በመንፈስ ቅዱስ ሃይል መሞላት**

1ኛ ቆሮንቶስ 6:17-20 አጠቃል::

ኢየሱስን ጌታ አድርገን ስንቀበል መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ስለሚኖር ከእርሱ ጋር በመንፈስ አንድ እንሆናለን! መንፈሳችን በአሳባችን፣ በቃላችንና በሥራችን እግዚአብሔርን ለማክበር ኃይልን ስለሚሰጠን ሰውነታችን የመንፈስ ማደሪያ ወይም ቤተ መቅደስ ይሆናል:: ይህ በመንፈስ መሞላት ወይም በልወጣ ጊዜ መንፈስን መቀበል በመባል ይታወቃል::

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፣ በግልፅ በተለወጠን ጊዜ መንፈስ ቅዱስን በመቀበል እና በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ መካከል ያለውን ግልጽ ልዩነት እንመለከታለን:: ሁለቱም ከአንድ ምንጭ፣ ከራሱ ከመንፈስ ቅዱስ የመጡ ናቸው፣ ግን ሁለት የተለያዩ ዓላማ አላቸው::

ሉቃስ 1:15 ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን ይላል?

ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ በሙላት ነበር ልክ እኛም በተለወጠንበት ጊዜ እንደምንሞላው :: በሉቃስ 3:16 ዮሐንስ ኢየሱስ ሲመጣ ምን ያደርጋል አለ?

በሐዋርያት ሥራ 1፡4-8 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት ወይም ጥምቀትን በተመለከተ ምን አስተማራቸው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ኢየሱስ የተናገረው በሐዋሥራ 2፡3-47 መሠረት ስለተፈጸመው የጴንጤቆስጤ ቀን ነው።

የሚከተሉትን ክስተቶች ይግለጹ.

የሐዋርያት ሥራ 2፡3-13

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

የሐዋርያት ሥራ 2፡14-36

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

የሐዋርያት ሥራ 2፡37-41

______________________________________________

______________________________________________

የሐዋርያት ሥራ 2፡42-47

ሐዋርያው ጴጥሮስ በቂሳርያ በአሕዛብ/አይሁድ ባልሆኑ ላይ የመንፈስ ጥምቀት የተደረገበትን ሌላ ጊዜ ዘግቧል። በሐዋርያት ሥራ 11፡15-16 ጴጥሮስ ስለ መንፈስ ምን አለ?

ማስተዋል ያለብን መንፈስ በአህዛብ ላይ የወረደበት እና በጴንጤቆስጤ ቀን የወረደው የመንፈስ ጥምቀት መካከል ጴጥሮስ ምንም ልዩነት እንዳልገለፀ ነው ። አንድ እና ራሱ ነው።. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በተአምራዊ መንገድ የመንፈስ ኃይል መፍሰስ ነው። ምንም እንኳን ከተለመደው ውጭ እንደሆነ ሊታይ ቢችልም ነገር ግን የሚያስፈራ ነገር አይደለም.። የተለመደም መሆን የእግዚአብሔር ባሕርይ አይደለም።

የመንፈስ ጥምቀትም በግድታ የሚኖርብን ጉዳይ አይደለም። ኢየሱስን ልናመልከው እና ልናከብረው ይገባናል እንጂ ኃይሉ እንዲገለጥ በመፈለግ አደለም ። በሌላ አነጋገር ሰጪውን መውደድ ያለብን ነው እንጂ ስጦታዎቹን አደለም ። ጴጥሮስ በቂሳርያ ባሉ አሕዛብ ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ አላሰበም ወይም አልጠየቀም። ያ የእግዚአብሔር ለዓላማውና ለክብሩ ያቀደው ነበር። ሁል ጊዜ የልብዎን ተነሳሽነት ያረጋግጡ።

**ትምህርት 6–የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት**

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድራዊ አገልግሎቱ ወቅት የደቀ መዛሙርቱን ፍላጎት እንዳሟላ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ለእያንዳንዱ ለተሰጠ አማኝ በተግባራዊ መንገድ ያገለግላል:: ይህ ትምህርት የሚያተኩረው በሕይወታችን ውስጥ ባለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው ማለትም  አጽናኝነት፣ አጋርነት፣ ከሳሽነት እና መካሪነት ላይ ማለት ነው ::

**አጽናኝ**

ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል::( ዮሐንስ 14:16 )

መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ማጽናኛ ሁለት ክፍሎች አሉት:: ስንጎዳ ወይም ስንቸገር  በማያልቅ የእናትነት ርህራሄን ይሰጠናል፣ነገር ግን የህይወት ፈተናዎችን እና ብስጭቶችንም ደግሞ እንድንቋቋም ብርታትን  ይሰጠናል:: መጽናኛ የሚለው ቃል የመጣው ፎርቲስ ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን ጠላት እንዳያጠቃ ምሽግ መስራት /ማጠናከር  የሚለውን ትርጉም ይይዛል ::

ስለመንፈስ ቅዱስ ርኅራኄ ወይም የሚያበረታ ማጽናኛነት ክምታወቀውን የግል ተሞክሮህ  ጻፍ::

____________________________________________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________________________________________

**አጋር  /አብሮ የሚሆን ጓደኛ /**

እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ:: ( ማቴዎስ 28:20 )

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን ለዘላለም ብቻችንን በፍፁም አይደለንም:: በሕይወታችን ውስጥ የምንጋፈጣቸው ሁኔታዎች ብዙ ጊዜ ከባድ እና አስቸጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ :: በእንደዚህ አይነት ጊዜያት ላይ ብቸኝነት ወይም ተስፋ መቁረጥ ስሜት ሊደርስብን ይችላል:: በእነዚህ ጊዜያት ለጠላት ጥቃቶችም በጣም ተጋላጭ ነን::ወደ እግዚአብሔር በጣም በመቅረብ  እርሱ የገባልንን ፍቅር፣ የመገኘቱን እንክብካቤ ፣ወደ ቃሉ በመመለስ ና አጋርነቱን  በመፈለግ የእኛን ፍላጎት ኣንዲያሟላልን መፍቀድ አለብን ::

ያዕቆብ 4:7-10 አንብብ:: ለወደፊት የብቸኝነት፣ የመንፈስ ጭንቀት ወይም የጠላት ጥቃት ሲደርስብህ እንዴት መልስ መስጠት ትችላለህ?

____________________________________________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________________________________________

**ወቃሽነት /ክሳሽነት/**

እርሱም ሲመጣ ስለ ኃጢአት ዓለምን ይወቅሳል:: (የዮሐንስ ወንጌል 16:8)

መንፈስ ቅዱስ ነውና ቅድስናውን በእኛ ውስጥ ያባዛዋል :: ቅድስና ማለት ለእግዚአብሔር የተለየ ማለት ነው:: በሕይወታችን ውስጥ ቅዱስ ያልሆኑ ማንኛውም ሃሳብ ወይም ድርጊት በእኛ ውስጥ የሚኖረውን መንፈስ ቅዱስን ያሳዝነዋል:: ምስጋና ይድረሰውና ስላልተቀደስን ጥሎን አይሄድም ፣ ይልቁንም ህሊናችንን ይወቅሰናል፣ ይናገረናል::

ህሊናችን የውስጣችን ፈራጅ ነው፣ማንኛውንም ሀጥያት ለመስራት ስናስብ ወይም ስንሰራ ያስጠነቅቀናል እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ሰለማዘኑ እንዲሰማን ያደጋል :: መጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ ሕሊና እንድንይዝ ያሳስበናል:: ለመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ ወዲያው በመታዘዝና ንስሀ በመግባት ምላሽ ብንሰጥ እሱ ከሀጥያት ይጠብቀናል ::

መንፈስ ቅዱስ የወቀሰህን ጊዜ ግለጥ :: ለመንፈስ ቅዱስስ ተገዝተሃል ?

**መካሪ**

ስሙም ድንቅ መካር ይባላል:: (ትንቢተ ኢሳይያስ 9:6)

እግዚአብሔር በቃሉ፣ በመንፈሳዊ ሰዎች እና በመንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ምሪት ይመክረናል:: በእግዚአብሔር ፊት ስንፀልይ ፣ ድምፁን ለመስማት እና ፈቃዱን ለማወቅ እንችላለን :: ብዙ ክርስቲያኖች በዕለት ተዕለት አምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር መቀራረብን ቸል ይላሉ እናም በሕይወታቸው መሰናከላቸውን ይቀጥላሉ በዚህም የመንፈስ ቅዱስን መመሪያ እና ምክር አያገኙም :: ይህንን ተግሣጽ ለመጀመር ለሚመከሩ መጻሕፍት አባሪ ለ ይመልከቱ::

የእግዚአብሔርን ጥበብ የምትፈልገው ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ ስላለህ ነው ?

በያዕቆብ 1፡5-6 ላይ እግዚአብሔር ምን ተስፋ ሰጥቷል?

**መሰረታዊ እውነት**

መንፈስ ቅዱስ በችግሮቻችን ውስጥ አጽናኛችን፣ ሁሌም አብሮን ያለ አጋር፣ ስንፈተን ወቃሻችን፣ እና መምሪያ እና ጥበብ በምንፈልግበት ጊዜ ደግሞ መካሪያችን ነው።

አሁን ስለ እግዚአብሔር ሦስቱ አካላት ማለትም እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተሻለ ግንዛቤ አለህ። እነዚህ በአንድነት ቅድስት ሥላሴን ይመሰርታሉ አንድ አምላክ በሦስት አካላት ሆነው ሶስቱም እኩል ኃይልና ግርማ አላቸው። በሚቀጥለው ምዕራፍ የክርስቶስ የመቀደስ ሥራ በሕይወታችሁ ውስጥ ሲተገበር ወደ ጎልማሳ ክርስቲያን ማደግ ምን ማለት እንደሆነ ትማራላችሁ።

# ምዕራፍ 4
# መንፈሳዊ እድገት እና ብስለት

የአስራ ሶስት አመት ልጅ ሳለሁ አንድ ጓደኛዬ የቤዝቦል ቡድንን እንድቀላቀል አሳመነኝ፣ በየትኛውም የተደራጀ ስፖርት ውስጥ ተሳትፌ ባላውቅም ያለኝ ብቸኛ የቤዝቦል ልምዴ በትምህርት ቤቱ ሜዳ ውስጥ ስጫወት የሚያጋጥሙኝ አንዳንድ ግጭቶች ነበሩ። በመጀመርያው የልምምድ ቀን ሁለት ነገሮችን ተምሬአለሁ አንደኛው በቤዝቦል በጣም ደካማ እንደሆንኩ እና ሁለተኛው ደግሞ ቡድኑ ውስጥ የነበሩት ሁሉም ሰዎች በርግጥ ጥሩ እንደነበሩ ነው።

በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት በነበረው ልምምድ ወቅት ማድረግ ፈልጌ የነበረው ነገር ቢኖር ማቆምን ነበር። የአካል ብቃት ነበረኝ ግን ለጨዋታው ምንም አይነት የዳበረ ችሎታ አልነበረኝም። እኔ ያለማቋረጥ ይሰማኝ የነበረው ራሴን ብቁ እንዳልሆንኩ ነበር፣ ነገር ግን ጓደኛዬ እንድቆይ አበረታታኝ። ከጊዜ በኋላ ኳሱን በቀላሉ መያዝ፣ መጫወት እና መምታት ጀመርኩ። ሌላው ቀርቶ በውድድር ዘመኑ መጨረሻ "በጣም የተሻሻለ"ተጫዋች በሚል ዋንጫ ተቀብያለሁ እና በቡድኑ ውስጥ ጥሩ አነጣጥሮ መቺ ከነበሩት የተሻልኩ ነበርኩኝ።

በመንፈሳዊ ህይወታችን ማደግ እና እግዚአብሔርን እየታዘዙ መኖር እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ የምንማራቸው መመሪያዎች/ተግፃፆች ናቸው። አንድ ክርስቲያን በመንፈሳዊነት እንዴት እንደሚያድግ ሳያውቅ ወይም ሂደቱን ችላ በማለት እግዚአብሔር ለኛ እንዲኖረን የሚፈልገውን ለውጥ እና ዓላማ በሙሉ አያገኝም ።

## ትምህርት 1—የጳውሎስ ምሳሌ

መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ አማኝ በክርስቶስ ሕፃን እንደሆነ ይገልፃል። ጤናማ የሆነ ሕፃን ወደ ጉልምስና ከመድረሱ በፊት የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን እንደሚያሳልፍ ሁሉ ሕፃኑ ክርስቲያንም ወደ መንፈሳዊ ጉልምስና በሚወስደው መንገድ ላይ ያለማቋረጥ መሻሻል ይኖርበታል። አንድ ሕፃን ማደግ ተስኖት ጤናማና በሳል ጎልማሳ ሳይሆን ሲቀር አሳዛኝ ነው። በተመሳሳይም አንድ ክርስቲያን መንፈሳዊ ምሉእነት እና ብስለት ማጣቱ ሲያቆም በጣም ያሳዝናል። የሰማዩ አባታችን ሁሉም ልጆቹ በእምነት የበሰሉ ወንዶች እና ሴቶች እንዲሆኑ ይፈልጋል።
ወደ መንፈሳዊ ጉልምስና ለማደግ የሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት ግሩም ምሳሌ ይሆነናል።

**የጳውሎስ መዳን**

ጳውሎስ ከወጣትነቱ ጀምሮ ሃይማኖተኛ ሰው ነበር፣ ነገር ግን በክርስቶስ አላመነም ነበር በሃላ ቆይቶ ቢያምንም ። ከሚከተሉት ቅዱሳን ጽሑፎች ስለ ጳውሎስ ሕይወት ምን ተማራችሁ?
የሐዋርያት ሥራ 22:3

______________________________________________________________
_________________________

______________________________________________________________
_________________________

______________________________________________________________
_________________________

የሐዋርያት ሥራ 23፡6

______________________________________________________________
_________________________

______________________________________________________________
_________________________

የሐዋርያት ሥራ 26:4-5

ገላትያ 1፡14

ፊልጵስዩስ 3፡4-6

ጳውሎስ ለአይሁድ ሃይማኖቱና ህጎቹ ያለው ቅንዓት ቤተክርስቲያንን በማሳደድ በግልጽ ታይቷል። የክርስቶስ ተከታዮችን ማሳደድ ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንደሆነም ያምን ነበር፣ ስለዚህ ይህንንም ያደረገው ምንም የጥፋተኝነት ስሜት ሳይሰማው ነበር። በሚቀጥሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ጳውሎስ ለአማኞች ያደረገውን ነገር ጠቅለል አድርገህ ጻፍ። (ማስታወሻ፡ ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ሳውል ተብሎ ይጠራ ነበር።)
የሐዋርያት ሥራ 7፡54–60; 8፡1–3፤ ገላ 1፡13

**የሐዋርያት ሥራ** 22:4; 22:19; 26፡9—11

ጳውሎስ የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ከተሞከረው ሙከራ በስተጀርባ ያለ መሪ እና ለክርስቲያኖች ስደት ምክንያት  የሆነ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ወደ ክርስትና መመለሱ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከታዩት ታላላቅ ክስተቶች መካከል አንዱ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በሐዋርያት ሥራ 9፡1-22 ያለውን ዘገባ አንብብና ታሪኩን ባጭሩ በራስህ አባባል ጻፍ፡፡

ጳውሎስ በመጀመሪያ ለጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጨቋኝ ሆኖ ነው የኖረው ፣ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተገለጠለት ቦሃላ ሙሉ በሙሉ ኢየሱስ ለውጦታል፡፡ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡12—16 ያለውን ምስክርነቱን አንብብ እና አንዳንድ ቁልፍ ነጥቦቹን ጻፍ፡፡

______________________________________________________________________________

____________________________

**የጳውሎስ ጥምቀት**

***የሐዋርያት ሥራ 9:18 እንደሚለው ጳውሎስ ከአይነስውርነቱ ወጥቶ ማየት እንደቻለ ነው የተጠመቀው ። የክርስትና ጥምቀት ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን ከደነገገው ሦስቱ ሥርዓቶች አንዱ ነው። ማቴዎስ 28:19-20ን አንብብና ኢየሱስ የሰጣቸውን ሦስት ትእዛዛት ጻፍ።***

1. ____________________________________________________________

2. ______________________________________________________________

3. ______________________________________________________________

***እነዚህ መመሪያዎች ታላቁ ተልእኮ በመባል ይታወቃሉ እናም የእያንዳንዱ የክርስቶስ አካል ሀላፊነት ናቸው። ደቀ መዝሙሩ አናንያ የጌታን መመሪያ በታማኝነት ተቀብሏል እናም ጳውሎስን ደቀ መዝሙር በማድረግ፣ በማጥመቅ እና በእምነቱ እንዲበስል እና እንዲያድግ በማስተማር ይህንን ተልእኮ ተወጥታል።***

| |
|---|
| መሰረታዊ እውነት<br>ጥምቀት በአካል፣ በአደባባይ የሚለጽ ወይምበልብውስጥ የታወጀውን የሚልጽ መግለጫ ነው። በራሳችን በጎነት እግዚአብሔር እኛን እንደ ልጆቹ አድርጎ ወደ ቤተሰቡ ሊያስገባን አይምሮ ጥም። የተሟጥነ ው በእርሱ ጸጋ ብቻ ነው። |

ጥምቀት በልብ ውስጥ የተከናወነውን ነገር በአካላዊና በአደባባይ በግልጽ ሁኔታ መግለጫ ነው። በውሃ ውስጥ መዘፈቅ ከክርስቶስ ውጭ የነበረው አሮጌ ህይወትን መሞት ያመለክታል፣ ከውሃው መውጣት ደግሞ መታጠብን፣ በክርስቶስ አዲስ ህይወት መወለድን ያመለክታል። አንድ ክርስቲያን ለክርስቶስ ቃል በመታዘዝ ለመጠመቅ ሲመርጥ፣ ኢየሱስ ለኃጢአቱ እንደሞተ፣ በመቃብር እንደተቀበረ እና ከሙታን እንደተነሳ ማመንን በአደባባይ መግለጫ ነው። ጥምቀት ለመዳን ግዴታ የሆነ ተግባር እንዳልሆነ፣ ነገር ግን አስቀድሞ ለተፈጸመው መዳን ምላሽ ይሆን ዘንድ መታዘዝን በተግባር ማሳያ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። ጥምቀት አስፈላጊ የሆነው ኢየሱስ ስላዘዘው ነው።

**የጳውሎስ አገልግሎት**

| |
|---|
| ***ሐዋርያ-*** *መልእክተኛ; ለተልእኮ የተላከ፣ ሥልጣኑን ከላኪው የሚያገኝ።* |

ጳውሎስ ሐዋርያ ሆነ ። ለእግዚአብሔርም ስራ ና ክብር መገልገያ መሣሪያ ሆነ። እርሱ በብዙ ቦታ ተላክ ፣በክፍተኛ ወኔ አገለገለ ፣ ታላቅ ነገርን እንዲያከናውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይልም ተሰጠው። ካገለገለውም መካክል

- ወንጌላዊ ና ቤተ ክርስቲያን መሥራች—ጌታ ጳውሎስን ቀደም ሲል ወንጌል ባልተሰበከባቸው ቦታዎች ሦስት የወንጌል ጉዞዎች እንዲያደርግ ላከው። ክርስቶስን መድኃኒት አድርጎ በመስበክ በእነዚህ አካባቢዎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አቋቋመ። የጳውሎስ የሚስዮናውያን ጉዞዎች በሐዋርያት ሥራ 13-21 ተመዝግበው ይገኛሉ።
- ሰባኪ እና አስተማሪ—በትንቢት እንደተነገረው፣ ጳውሎስ ክርስቶስን ለአሕዛብ፣ ለነገሥታት እና ለእስራኤል ልጆች ሰብኳል። ብዙዎች በክርስቶስ ሲያምኑ ሌሎች ደግሞ ያፌዙበት እና ያሳድዱበት ነበር። የጳውሎስ ስብከት ምሳሌዎች በሐዋርያት ሥራ 13:16–41 እና በሐዋርያት ሥራ 17:22–34

ተመዝግበዋል።

- ጸሃፊ—አዲስ ኪዳንን ከመሰረቱት ሀያ ሰባቱ መጻህፍት፣ ጳውሎስ የአስራ ሶስት፣ ምናልባትም የአስራ አራቱ ጸሃፊ ነው። እነዚህ መጻሕፍት በወንጌላዊ ጉዞው ላቋቋማቸው አብያተ ክርስቲያናት የተጻፉ መልእክቶች በመባል የሚታወቁ ናቸው።

ትዕቢተኛ ከሆነው የሃይማኖት መሪ እና ከክርስቲያኖችን አሳዳጅ እስከ ትሑት የልዑል አምላክ አገልጋይ ድረስ የጳውሎስ ሕይወት ለአማኞች ሁሉ ምሳሌ ነው። ጥቂት ሰዎች እንደዚህ አይነት ትጋትን ቢከተሉም ሁሉም ክርስቲያኖች ልክ እንደ ጳውሎስ ከጨለማ ወደ ብርሃን ተሸጋግረዋል።የእግዚአብሔርን እውነት በትዕቢት ከመቃወም ወደ ድነት ስጦታው በትህትናና በጸጋ እስከ መቀበል ደርሰዋል።

**በኤፌሶን 2፡10 ላይ እግዚአብሔር ለአማኞች ሁሉ ምን አስደናቂ ተስፋ ሰጥቷል?**

__________________________________________________________________________________________________________________________________________________

እግዚአብሔር ለህይወትህ እቅድ እና አላማ እንዳለው ታምናለህ ?

| |
|---|
| መሰረታዊ እውነት |
| ያለፉት ስህተቶቻችን ቢኖርም፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ያለው ዓላማ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ፈጥረውና ሌሎችን በማገልገል እርሱን እንዲያገለግሉ ነው። |

# ትምህርት 2-መቀደስ

በመጽሐፍ ቅዱስ መቀደስን ክርስቲያናዊ የመብሰል ሂደት ይለዋል። ይህ ቃል ቅዱስ የመሆን ሂደት ተብሎ ሊገለጽም ይችላል። ቅድስና ስሜት ወይም ልምድ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ ባሕርይ የዳበረበትና በአማኙ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚኖረው የአኗኗር ዘይቤ ነው።

***መቀደስ-*** *መጥራት; የሰዎች ስሜት ከኃጢአት የራቀበት እና ከፍ ከፍ ወዳለ ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ጽድቅ ፍቅር የሚሸጋገርበት የእግዚአብሔር የጸጋ ሂደት።*

1ኛ ጴጥሮስ 1፡14–16 አንብብና ጥቅሶቹን ከታች ጻፍ።

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

*የመቀደስ ሂደት ሶስት የተለዩ ገጽታዎች አሉት፡ የመጀመሪያ፣ እያደገ ያለ እና የመጨረሻ መቀደስ ናቸው ፡፡*

***የመጀመሪያ ደረጃ መቀደስ***

*የመጀመርያው መቀደስ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ የሰጠው ቦታ ነው፡፡ ይህ አቋም ከባህሪ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ሁሉም አማኞች ክርስቶስን እንደተቀበሉና እንደተለወጡ በክርስቶስ ደም ተዋጅተዋል፣ ይነጻሉ፣ ይቅርታ ይደረግላቸዋል፣ በዚህም ጻድቅ ሆነዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖችን ቅዱሳን ብሎ የሚጠራቸው ነቀፋ የሌለባቸው ወይም ኃጢያተኞች ስለሆኑ ሳይሆን ኢየሱስ በመስቀል ላይ በደላቸውን በራሱ ላይ በማድረጉ በእግዚአብሔር ፊት ያለ ነቀፋ እንዲሆኑ ስላደረጋቸው ነው፡፡*

*ክርስቶስን እንደ አዳኛችሁ ከተቀበላችሁት ተቀድሳችኋል፡፡*

***እያደገ ያለ የመቀደስ ደረጃ***

*በቅድስና ውስጥ ማደግ ማለት አማኙ ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ ለመኖር እና ኃይሉን ለመቀበል በሚያደርገው ዕለታዊ ውሳኔ ላይ ነው የተመሰረተው ፡፡ ይህ ቀጣይነት ያለው ሂደት የክርስቲያኑን የማያቋርጥ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ በፈቃዳቸው ለእግዚአብሔር መገዛት አለባቸው፣ ፈቃዱን ለሕይወታቸው መመኘት እና ለእርሱ ማሰልጠኛ/ማስተማሪያ ዘዴዎች መተባበር አለባቸው፡፡*

*ራሳችንን በየጊዜው ለእግዚአብሔር ባቀረብን ወይም በሰጠን ቁጥር ና እምሯችንን ከላይ ባሉት ነገሮች ላይ ስናደርግ እና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስንመላለስ ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንለያለን፣ ስለዚህም ለመቀደስ እድገት እያደረግን ነው ማለት ነው፡፡ በተለይም ራሳችን ረዳት አልባ እንደሆንን እና የእግዚአብሔርን ፍፁም ኃይል በሕይወታችን ውስጥ እንዳለ ስናቅ ይህ በእያንዳንዱ ቅጽበት የሚገኘው ድል እየጨመረ መምጣት ይገባዋል ፡፡*

**የመጨረሻው መቀደስ ደረጃ**

ይህ ፍፁም እና የመጨረሻው መቀደስ የሚሆነው አማኞች በዳግም ምጽአቱ የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ ሙሉ በሙሉ በሚመስሉበት ጊዜ ነው። ክርስቲያኖች በምድራዊ አካል ውስጥ እስካሉ ድረስ ለኃጢአት የተጋለጠ ና የወደቀን ተፈጥሮ ይዘዋል። ነገር ግን፣ ከዚህ ህይወት ሲወጡ እና በፊቱ ሲገለጡ የክርስቶስን መልክ ሙሉ በሙሉ ይመስላሉ።

**የመቀደስ ምሳሌ**

አንድ የጥሩ ነሃስ ኤክስፐርት በከተማው ዳርቻ ላይ ከተከማቸ የቆሻሻ ክምር ውስጥ አንድ ነገር ለማግኘት እየፈለገ ሳለ በድንገት አንድ አሮጌ የተደበደበ የናስ ድስት ተመለከተ። የቆሸሸ፣ የጠቋቆረ እና የተደበደበ ነበር፣ ነገር ግን አይኑ ዋጋ ያለው ነገር እንዳገኘ አውቆአል ። ክቆሻሻ መጣያ ውስጥ አሮጌውን ድስት አውጥቶ ለብቻው አስቀመጠው። በዚህም ዕቃውን ቀደሰው ማለት ነው ። ይህ አተገባበር የመጀመሪያ ደረጃ መቀደስ ማለት ነው። እርግጥ ነው አሮጌውን ማሰሮ በማጽዳት፣ በመቅረጽ እና በማሳመር ብዙ ሰአታት ማሳለፍ አለበት። በዚህም ለጠረጴዛው የሚያምር ማስጌጫ ይሆንለታል ማለት ነው።ይህ ተግባርና ሂደት ሁለተኛውን መቀደስ ያሳያል ።

የቅድስና ማብራሪያ በራስዎ ቃላት ይጻፉ።

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዱ ሕይወት ዋጋ እንዳለው ነው የሚያየው፣ ሰውን ሁሉ ከጥፋት ለማዳን የመጨረሻውን ዋጋ እንደከፈለለትም ነው ። ለእርሱ መስዋዕትነት ና አዳኝነት በእምነት ምላሽ የሚሰጡ ለእሱ ከዚህ አለም ተለይተዋል ማለት ነው። እሱም እያንዳንዳቸውን በማንጻት በመቅረጽ እና በማሳመር ለክብሩ የተዋቡ ያረጋቸዋል።

ኢየሱስ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ የጀመረውን ሥራ ለማጠናቀቅ ታማኝ ነው። የእኛ ድርሻ በየቀኑ ለእርሱ መገዛት ነው። በእርሱ እና በቃሉ ስንኖር እና ለፈቃዱ በታማኝነት ስንገዛ፣የእርሱን የሚቀደሱ እጆችን በህይወታችን ላይ እናያለን እናም እሱ ለእኛ ያለውን ሁሉ እንለማመዳለን።

> ማሳረታዊ እውነት
> ክርስቶስን እንደ አዳኝ እና ጌታ በተቀበልን ጊዜ እግዚአብሔር ቀደሰን። ከእርሱ ጋር በፍቅር እና በሙታዘዝ ስንሄድ እኛን ሙቀደሱን ይቀጥላል። አንድ ቀን፣ ወደ እርሱ ሲጋብዘን ና ሲቀበለን በዚያ ቅጽበት፣ ሙቀደሳችን ሙሉ ይሆናል።

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው ደብዳቤ ጌታ እኛን ለመቀደስ ያለውን ታማኝነት በማያጠራጥር መልኩ ገልጿል።

ፊልጵስዩስ 1፡6 አንብብና ጥቅሱን እንደገና ጻፍ።

__________________________________________

**ትምህርት 3-የጳውሎስ መቀደስ**

**ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ድኖ ለአገልግሎት ተለየ ። የልቡ ፍላጎት ከአዳኙ ጋር ህብረት ማድረግ ና በመንፈሳዊነት ማደግ  እንዲሁም በየጊዜው የበለጠ ወደ ኢየሱስ መምሰልን  መቅረብ ነበር ። ፊልጵስዩስ 3ን አንብብ።**

**ለምን ጳውሎስ በፈቃዱ ሁሉንም ነገር በማጣት ተሰቃየ** (**ቁጥር** 7-8)?

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

**የጳውሎስ ልብ ምኞት ምን ነበር** (**ቁጥር** 10)?

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

ጳውሎስ ስለ አምላክ ማወቅ ብቻ አልነበረም ፍላጎቱ ። እርሱን በቅርበት ክልብ ሊያውቀው ፈለገ።

***የጠበቀ/የቀረበ*** - *በግል ግንኙነት ወይም ማህበር ውስጥ ቅርብ; የተለመደ፣ በቅርበት አንድነት; ከውስጣዊ ማንነት ጋር በተያያዘ።*

ሰውን በቅርበት የምናውቀው እንዴት ነው?

____________________________________________________

____________________________________________________

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

በዘፀአት 33:13 **ሙሴ እግዚአብሔርን ምን ጠየቀው**?

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

**የሙሴም ልብ እንደ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር እና ስለ መንገዶቹ ጥልቅ እውቀት ለማግኘት**

**ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔርን በቅርበት ማወቅ የምትችለው እንዴት ይመስልሃል?**

**በፊልጵስዩስ 3:12-14፣ ጳውሎስ ገና ሙሉ በሙሉ እንዳልበሰለ ተናግሯል። ራሱን ውድድር ውስጥ እንዳለ ራጭ አትሌት ጋር አነጻጽሯል። መንፈሳዊ እድገት ለማምጣት የሚያደርገውን ጥረት ለማስረዳት ሦስት ገላጭ ሐረጎችን ተጠቀመ:-**

- **"ተጠንቅቆ መቀጠል" (ቁርጠኝነት)**
- **"የያዙትን እውነት አጥብቆ መያዝ " (ጽናት)**
- **ወደፊት መገስገስ / ለውጥ (የግል ጥረት)**

ጳውሎስ ክርስቲያንን ከአንድ አትሌት ጋር ሲያወዳድር መንፈሳዊ ብስለት የቁርጠኝነትና የተግሣጽ ውጤት መሆኑን ያሳያል። ንስሐ ለሚገቡ እና ክርስቶስን ለሚቀበሉ ሁሉ መዳን ነጻ ነው፣ነገር ግን ብስለት፣ ጥረት እና መስዋዕትነትን የሚጠይቅ የዕለት ተዕለት ምርጫ ነው። ተራ አትሌቶች በስፖርት ጎልተው መውጣት እንደማይችሉ ሁሉ ተራ ክርስቲያኖችም አነስተኛ እድገትና ለውጥ ይኖራቸዋል።

ማስረታዊ እውነት

መንፈሳዊ እድገት እና ብስለት ቁርጠኝነትን፣ ጽናትን እና የግል ጥረትን ይጠይቃል።

***ተጠንቅቆ መቀጠል*** *- ጥረትን ማጠቀም; ማጣር; መንገዱን ወደፊት በሃይል/ገፍቶ መሄድ።*

***ማያዝ /ሜጨበጥ*** *- ሚረዳት ፣ ማያዝ ፣ አጥብቆ ማያዝ።*

***ወደፊት ማዝ/ማስገስ*** *- ከአንድ ነገር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፣ ጥረት*

*ሯጮች ውድድራቸውን በብርቱነት እንዲጨርሱ የሚሮጡብትን መስመር ምንም ነገር እንዲረበሽባቸው መፍቀድ የለባቸውም። ወደኋላ ፣ ወይም ሌሎች ሯጮች ላይ ወይም ራሳቸው ላይ ጭምር ማተኮር የመጨረሻውን ግባቸው ላይ እንዳይደርሱ እንቅፋት ይሆናቸዋል ።*

በፊልጵስዩስ 3 ላይ፣ ጳውሎስ *መንፈሳዊ እድገትን የሚከለክሉ/የሚያደናቅፉ ሦስት አደጋዎችን ተናግሯል።*

| |
|---|
| ***ማከልከል*** - *ወደ ኋላ/ከኋላ ማድረግ ; እንዳይጀምር ወይም ወደ ፊት እንዳይሄድ የ ማከላከል.* |

## ወደ ኋላ ማየት

በፊልጵስዩስ 3:13 *መሠረት ጳውሎስ ምን ሁለት ነገሮች አድርጓል?*

___________________________________________

___________________________________________

በዚህ ምዕራፍ ስለ ጳውሎስ በተማርከው ነገር ላይ በመመሥረት ጳውሎስ በሕይወቱ ውስጥ የትኞቹን ነገሮች መርሳት ያስፈልገው ይመስልሃል?

___________________________________________

___________________________________________

እዚህ ላይ የተጠቀሰው መርሳት ማለት ማስታወስ ማቆም ማለት ሳይሆን ታሪኩን ወደ ኋላ ማስቀመጥን መምረጥ ማለት ነው። ያለፉ ኃጢአቶች ወይም ጎጂ ትዝታዎች የአሁን ያለንበትን ጊዜ እንዲቆጣጠሩ እና የወደፊት ሕይወታችንን እንዲያበላሹ መፍቀድ የለብንም። እነርሱን ከኋላችን ትተን በእግዚአብሔር ጸጋ፣ ይቅርታ እና ኃይል ወደፊት መራመድ አለብን።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡9-10፣ ጳውሎስ እራሱን እና ክርስቶስ ለእርሱ ያደረገውን እንዴት ገልጿል?

___________________________________________

___________________________________________

ጳውሎስ ያሳለፈው ውድቀቶቹ ን እና ኃጢአቶቹን ከእግዚአብሔር ፀጋ ይበልጥ ቢያተኮርበት ለጌታ ያለው አገልግሎት ላይ ምን አይነት ተፅእኖ ለያሳድርበት ይችል እንደነበር ታስባለህ ?

___________________________________________

___________________________________________

______________________________________________________________________

________________________

በቀደመው ህይወቱ ቢያፍርም፣ ጳውሎስ ከዛ ህይወቱ ነጻ የወጣው በክርስቶስ የመስቀል ስራ፣ በእግዚአብሔር ፊት ንስሃ በመግባት እና በአብ ፀጋ ውስጥ ያለማቋረጥ በመመላለስ እንደሆነ አውቋል። በዚህም ያለፈውን ረስቶ የኢየሱስን ጽድቅ ለብሶ መቀጠል ችሏል ።

በህይወታችሁ ውስጥ ውድድሩን በብቃት እንዳትሮጡ የሚከለክላችሁ ምንድን ነው?

______________________________________________________________________

________________________

______________________________________________________________________

________________________

______________________________________________________________________

________________________

______________________________________________________________________

________________________

______________________________________________________________________

________________________

______________________________________________________________________

________________________

በእርግጥ እግዚአብሔር በዚህ ምዕራፍ እርስዎን የሚያሳፍሩዎትን ትዝታዎችን ወይም ወቅታዊ ሁኔታዎችን ለመግለጥ ተጠቅሞበታል። በአንተ ላይ ሌላ ሰው የፈጸመው ኃጢአት ወይም አንተ የሠራኸውን ኃጢአት ሊሆን ይችላል። ሁለቱም ለእግዚአብሔር ፍቅር እና ይቅርታ ብቁ እንዳልሆኑ እንዲሰማህና በእፍርት እስር ውስጥ ሊያስቀምጡህ ይችላሉ። የሰማዩ አባታችሁ ከማፈር ዓለም ነፃ መውጣትን እድል እየሰጣችሁ ነው። እግዚአብሔር ያለፈው ጊዜን ለእርሱ እንድትሰጥ እየጠየቀህ ነው ።በህይወትህ ውስጥ ያለውን ኃጢአት እና ሃፍረት እንድታጋልጥ እና ምሪቱንና ፈውሱን በመቀበል ካለፈው ሰንሰለትህ ነፃ እንድትወጣ ዘንድ ነው የሚፈልገው ።

እነዚህን ነገሮች ለአማካሪዎ እንዲሁም ሀላፊነት ለሚሰማው ሰው ወይም ለፀሎት ጓደኛዎ ያካፍሉ። ለዚህ ፈተና ምን ምላሽ ይሰጣሉ?

ትምህርት 5–በሌሎች ላይ የማተኮር ያለው አደጋ

ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 3፡2፣18—19 በሕይወቱ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ሰዎች እንዴት ገልጿል?

እንደተማርነው፣ ጳውሎስ ራሱ በቀደመ ህይወቱ የመስቀሉ ጠላት ነበር። እንደገና የሐዋርያት ሥራ 7፡54—60ን አንብብና ጳውሎስ የመሰከረውን ትዕይንት ግለጽ።

እስጢፋኖስ ለአሳዳጆቹ ምን ምላሽ ሰጠ?

2 ጢሞቴዎስ 4:14—17 ኣንብብ። ጳውሎስ ለሚጎዱትና እሱን ለከዱት ሰዎች ምን ምላሽ እንደሰጣቸው ግለጽ።

2 ቆሮንቶስ 11፡23—33ን አንብብ። በጳውሎስ ላይ የተፈጸሙትን ሌሎች ጥፋቶች ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

ጳውሎስ በአገልግሎቱ ወቅት ብዙ መከራዎችን ተቋቁሟል፤ ሆኖም አጥቂዎቹን ይቅር ብሏል። እስጢፋኖስ በድንጋይ የገደሉትን ይቅር ማለቱ በጣም የነካው ይመስለኛል ምክንያቱም እሱ ራሱ በእስጢፋኖስ ስደት ውስጥ የራሱን ሚና ስለነበረው . ።

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እንዲጸልዩ ሲያስተምር የይቅርታን አስፈላጊነትን አስተምሯቸዋል። በማቴዎስ 6፡9-15 የተማርከውን አጠቃልል።

ከማርቆስ 11፡25-26 ምን ተማራችሁ?

መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ሰው ላይ የሚፈጸም በደል እንደ ዕዳ እንደሆነ ያስተምራል:: ቅር የተሰኘው ሰው ዕዳውን ይቅር ማለት ወይም ለተበደለው ክፍያ መጠየቅ ይችላል:: ይህ ይቅርታ ማድረግ በደለኛው ብቁ ስለሆነ ወይም ይቅርታ የማግኘት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ አይደለም ይሁን እንጂ ይቅር ላለማለት የመረጡ ልባቸው የሚመርዙበትን መራርነት ነው የሚመዝባቸው/የሚያመጣባቸው:: ኃጢአተኞች እንደመሆናችን መጠን ለእግዚአብሔር መክፈል የማንችለው ትልቅ ዕዳ አለብን:: ክርስቶስን እንደ አዳኛችን ስንቀበል እዳችን በቸርነቱ ተምራል ምክያቱም እዳውን የተቀጣልን ኢየሱስ ስለሆን ። እኛስ እንደዚህ ያለ ዕዳ ይቅር የተባልነው እንዴት ነው የበደሉንን ይቅር ለማለት እንቢ የምንለው?

እግዚአብሔር በየእለቱ ይቅር ይለናል እና የበደሉንንም ይቅር እንድንል ያዘናል:: ሉቃስ 6:35ን ከዚህ በታች ጻፍ::

______________________________________________________________________

______________________

______________________________________________________________________

## ትምህርት 6–ራሳችንን ላይ ብቻ ማተኮር ያለው አደጋ

**ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ላይ ራሱ ባደረጋቸው ነገሮች የመተማመን አቅም እንደነበረው ተናግሯል። ፊልጵስዩስ 3:3-6ን አንብብና ጳውሎስ እየገለጸ ያለው ምን እንደሆነ የምታምንበትን ጻፍ።**

______________________________

______________________________

> ***በራስ መተማመን***- *በራስ ጥንካሬ ወይም ሀይል/ስልጣን መተማመን ; በራስ መመካት*
>
> ***ኩራት***-*ራስን በትልቁ ማመት እና ከስር ያለውን ማጸየፍ ና መናቅ ; ምክንያታዊ ያልሆነ የበላይነት ጽንሰ-ሀሳብ።*

ጳውሎስ አጥባቂ አይሁዳዊ እንደመሆኑ መጠን ጥሩ እና ጻድቅ ሰው እንደሆነ ያምን ነበር። በፊልጵስዩስ 3:6 ላይ እንደ አሮጌው/የበፊቱ ሃይማኖቱ መመዘኛ ህይወቱ ነውር የሌለበት መሆኑን ተናግሯል። የክርስቶስ ተከታይ በሆነ ጊዜ የወደቀበትን ሁኔታ ተረድቶ በራሱ ላይ ወይንም በመልካምነቱ ላይ መታመንን አቆመ።

ለራስ መተማመን ሌላው የሚገልፀው ቃል ትዕቢት ነው።
በምሳሌ 16:18 መሠረት ሁልጊዜ የትዕቢት ውጤት ምን ይሆናል?

______________________________

______________________________

**እራስን ብቻ ማየተ ፣ እራስ ላይ ብቻ ማተኮር፣ ራስን ማገልገል፣ ራስን ጉረኛ ማረግ፣ ራስን ማታለል፣ራስን ማስወስለት፣ ራስን ብቻ መፈለግ፣ ራስን መተማመን፣ ራስ ወዳድነት እና በመጨረሻም ራስን ማምለክ ብዙ ችግሮች ያመጣል።**

ያእቆብ 3:13-16 አንብብ።ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ ራስ ወዳድነት ምኞት ምን ተማራችሁ?

______________________________

______________________________

______________________________

በሉቃስ 9:23-24 መሠረት፣ ኢየሱስ እያንዳንዱ አማኝ ምን ማድረግ እንዳለበት ተናግሯል?

______________________________

ራስን መካድ ማለት ምን ማለት ነው ብለው ያስባሉ?

| |
|---|
| **ማኅረታዊ እውነት**<br>መንፈሳዊ እድገት እንዲኖረን ትኩረታችን ከክርስቶስ ጋር በጥብቅ መቀራረብና የመንፈሳዊ ጉልምስ የግድ ግባችን መሆን አለበት ። |

**ትምህርት 7-የኃጢአት ክብደት**

*የአንድ ሯጭ ከመጠን በላይ ውፍረት በውድድር ወቅት ፍጥነቱንና ጽናቱን እንደሚያደናቅፍበት ያውቃል። በተመሳሳይም ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ውስጥ ያለው የኃጢአት ክብደት እንቅፋት እንደሚሆንባቸው ሁልጊዜ ማወቅ አለባቸው። ኃጢአት የመንፈሳዊ እድገት እንቅፋት ይሆናል ምክንያቱም ከመንፈሳዊ ብስለት ግባችን ትኩረታችንን የሚከፋፍል፣ ከሰማያዊው አባታችን ጋር ካለን ህብረትና ቅርርብ የሚለየን እና መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ኃይል ስለሚያጠፋ ነው።*

*ዕብራውያን* 12:1 *እና ምሳሌ* 5:21—22 *ኃጢአትን የሚገልጹት እንዴት ነው?*

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ታርቀን ወደ ትክክለኛ ግንኙነት እንድንመለስ የተጠላለፈ ኃጢአትን ገፈን ለመጣል የሚያስፈልገውን ነገሮች ሁሉ አዘጋጅቶልናል።

> ***እርቅ-*** *ወደ ስምምነት ወይም ጓደኝነት መመለስ።*

**ከእግዚአብሔር ጋር የመታረቅ እርምጃዎች**

**ደረጃ 1፡ ተናዘዙ**

*ኃጢአትህን መናዘዝ ማለት "ለራስህ ሚስጥራዊ፣ የተደበቀ ወይም ጎጂ የሆነ ነገርን መቀበል"– እግዚአብሔር ኃጢአት ብሎ የሚጠራው በእርግጥ ኃጢአት መሆኑን ማመን ማለት ነው። እግዚአብሔር ድርጊቶችህ በእርግጥ ከፈቃዱና ከመንገዶቹ ጋር ተቃራኒ እንደሆኑ ከእርሱ ጋር እንድትስማማ ይፈልጋል።*

በ1 ዮሐንስ 1፡9 *መሠረት፣ በትህትና ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ምላሽ ምንድን ነው?*

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________

**ደረጃ 2፡ *ንስሐ መግባት***

*ንስሐ መግባት ማለት ባደረግነው ወይም ባላደረግነው ነገር ፀፀትና ሐዘን መሰማት፣ እንዲሁም ለቀድሞ ወይም ለታቀዱ ድርጊቶች አእምሮንና ልብን መለወጥ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅህ፣ በደላችን እንደጎዳውና ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት እንደተጋረደብን በመገንዘብ፣ በተሰበረ ልብ፣ በፀፀትና በንስሐ የሚቀርብ ምላሽ ነው።*

በመዝሙር 25፡18 *ዳዊት ለእግዚአብሔር ምን አለ?*

ሌላ ሰው አስቀይመህ ወይም በደልከው ከሆነ፣ እንደ ማቴዎስ 5፡23-24 ኢየሱስ ምን እንድታደርግ ይላል?

### ደረጃ 3፡ ማመን እና መቀበል

ይህ የመጨረሻው እርምጃ ወሳኝ ነው:: ምንም ቢሰማህ፣ እግዚአብሔር ኑዛዜህንና ንስሐህን እንደተቀበለ አምነህ ሙሉ ይቅርታውን መቀበል አለብህ:: እርሱ ታማኝና ይቅር ባይ እንደሆነ በመጽሐፉ ተጽፏል፤ ስለዚህም ከእርሱ ጋር ያለህ ግንኙነት እንደተመለሰልህ እርግጠኛ ሁነህ በልበ ሙሉነት መቀጠል ትችላለህ::

ኢየሱስ በማቴዎስ 21፡22 ላይ ምን አለ?

በራሳችን እኛ ደካሞች ነን እናም ዘወትር በእግዚአብሔር የቅድስና መስፈርት መኖር ሳንችል ስንወድቅ እንታያለን። ለሌሎች ፍፁም ፍቅር፣ ደግነት፣ ትዕግስት እና ይቅር ባይነት ማድረግ ያቅተናል። በተፈጥሮ እኛ ግላዊ ነን፣ ሌሎችን ለማስቀየምና እንዲሁም ለመቀየም አቅም ያለን ፣ እንዲሁም ስለራሳችን እንጂ ስለሌሎች ብዙም የማናስብ ነን ። ራሳችን ልናረገው በማንችለው መስፈርት በህይወታችን ውስጥ ያሉትን ሰዎች እንመዝናለን። እነዚህንም ነገሮች በየቀኑ እያደረግን እንገኛለን ።

**መሰረታዊ እውነት**

አላስፈላጊ ክብደት የሯጮችን ፍጥነት እንደሚቀንስ ሁሉ በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት መንፈሳዊ እድገታችንን ይገድባል። በእግዚአብሔር ፍጹም የሚቀይረ የስልጠና እቅድ ጋር ማስማማትና /መተግበርን ማምረጥ አለብን።

ትምህርት 8-የአማኙ ግቦች

**በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 3 ውስጥ፣ ጳውሎስ የግል ግቡን እንዲሁም የህይወቱንና የህልውናውን አላማ መሪ ሃሳብ አሳይቷል። በቁጥር 14 ላይ** *ግቡና እና ዓላማውን እንደ 'በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሄርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ' ሲል ገልጾ ነበር። ይህም በሁለት ቃላት ሊጠቃለል ይችላል፤ ክርስቶስ እና ሰማይ።*

**የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊልጵስዩስ 3 ላይ በምታነብበት ጊዜ፣ ጌታን ስለራስህ የግል ግቦች እና የህይወት አላማ እንዲናገርህ ፍቀድለት። ሀሳቦችህን ፃፉ።**

ክርስቶስን ማወቅ (ቁጥር 8)

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

በክርስቶስ ውስጥ መገኘት (ቁጥር 9)

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________

የክርስቶስን ኃይል ማወቅ (ቁጥር 10)

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________

እንደ ክርስቶስ መሆን (ቁጥር 10)

______________________________________________________________________________
________________________

______________________________________________________________________________
________________________

*መንግሥተ ሰማያ* (ቁጥር 11፣20-21)

_______________________________________________
_______________

_______________________________________________
_______________

_______________________________________________
_______________

ጳውሎስ የልቡን በፈቃደኝነት የፃፋቸው መልዕክቶች አውጥቶ አሳይታል ። ጳውሎስ ሀጥያቱን ተናዘዘ ፣ ስህተቶቹን እና ድክመቱንም ገለጸ እናም ለክርስቶስ ያለውን ፍቅር ፣ ለቅድስና እና ለመንፈሳዊ ብስለት ያለውን ጥልቅ ፍላጎት በፅናት አወጀ። የእሱ የሕይወት ታሪክ የተመዘገበው ና ተፅፎ ያለው እኛን እንዲያበረታታና ልንከተለው የሚገባ ምሳሌ ስለሆን ነው።

> ***ተጠያቂነ ት****—ኃላፊነ ትን ማወጣትና ለድርጊ ት ተጠያቂ ማሆን ነ ው።*

***መንፈሳዊ እድገትህን ለመደገፍና ተጠያቂነትን ለመፍጠር፣ የበሰለ አማኝን ፈልጎ ከእርሱ ጋር መሠልጠን አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ እውነተኛ ግንኙነት ግልጽነትን፣ ሐቀኝነትንና ተጋላጭነትን ይጠይቃል፡፡ እንደዚህ አይነት ሰው ከሌለህ፣ በንቃት ፈልግና እግዚአብሔር እንዲልክልህ ጸልይ፡፡ ለዚህ አይነት ድጋፍና ተጠያቂነት እንደምትፈልግ ለፓስተርህ ወይም ለሌላ የቤተ ክርስቲያን መሪህ ንገራቸው፡፡***

***አንተን ደቀ መዝሙር ሊያደርጉህ ፈቃደኛ ሊሆኑ የሚችሉትን አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ማሰብ ትችላለህ? ስማቸውን ከዚህ በታች ጻፍ፡፡***

1. ______________________________

2. ______________________________

*መቼ ነው የምታገኛቸው?*

_______________________________________________
_______________

’*ወደ ግብ ለመድረስ*’እግዚአብሄር *ምን እንድታደርግ አበረታቶሃል?*

_______________________________________________
_______________

_______________________________________________
_______________

_______________________________________________
_______________

_______________________________________________
_______________

አሁን ከክርስቶስ ጋር ባለህ መንፈሳዊ ጉዞ ማደግ እና መጎልመስ ምን እንደሚመስል መሰረታዊ ግንዛቤ አለህ። ከእግዚአብሔር ጋር በየቀኑ እንዴት መቀራረብን ማዳበር እንደሚቻል ማብራሪያ ለማግኘት አባሪ A/ሀ ን ይመልከቱ። የሚቀጥለው ምዕራፍ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥልቅ የይቅርታ እና የማስታረቅ መርሆች  ጥናት ያቀርባል። ጸሎቴ ክርስቶስ ለልባችሁ ሊሰጥ የሚፈልገውን ፈውስ ለመቀበል ልባችሁን እንዲከፍትላችሁ ነው።

## ምዕራፍ 5

## ይቅርታ እና እርቅ

ኢየሱስን እንደ ጌታ ከተቀበልኩ ብዙም ሳይቆይ ኢየሱስ በአባቴ ላይ የያዝኩትን ጥልቅ ጥላቻ ገለጸልኝ። የበለጠ ከማካፈሌ በፊት፣ አባቴ እኔን እና ሌሎች ሰባት ወንድሞች እና እህቶቼን ለማሳደግ የተቻለውን ሁሉ ጥረት ያደረገ ጥሩ ሰው እንደነበረ እና እንደሆነ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ። እሱ በእኔ ላይ መጥፎ ፍላጎት እንዳልነበረው ወይም እኔን ለመጉዳት እንዳላሰበ አሁን አውቂያለሁ። ከአባትነቱ ከሱ የምፈልገውን ከመስጠት አልተቆጠበም። የተቻለውን ያህል ጥረት ቢያደርግም ያደረጋቸውም፣ ያላደረጋቸውም እና የተናገራቸው ነገሮች በእኔ ላይ ጉዳት ያደረሱ ሲሆን ይህም በመጨረሻ በእርሱ ላይ ጥላቻ አሳደገብኝ ። ወደ አባቴ ሄጄ ይቅር ማለት እንዳለብኝ ጌታ በግልፅ ነግሮኛል።

የብዙ ሰው ታሪኮቻቸው ከእኔ ጋር ይመሳሰላል። ወላጆች የሚፈጥሩት ክፍተቶች  መገለፅ ለማይችሉ ጥላቻ ወይም ቅሬታ ምክንያቶች ናቸው ። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ልጅ የነደፈው ልዩ ስሜታዊ እና አካላዊ ፍላጎቶች እንዲኖሩትና በሁለቱም ወላጆች ፍላጎቶቻቸው እንዲሟሉ ነው ። እንደኛው ወይም ሁሉም ፍላጎት ሳይሟሉ ሲቀር ክፍተት በልጁ ህይወት ውስጥ ይፈጠርና በስሜቱም ሲንፀባረቁ ይታያል።  ለምሳሌ፣ አባት አምላካዊ (የማያዳላ ፣ ሁሉንም በኩል የሚረዳ )አመራርን መስጠትና ሚስቱንና ልጆቹን በእውነተኛ ፍቅር ማኖር  ይኖርበታል። እናት አፍቃሪ፣ ተንከባካቢ፣ አቃፊ እና ባሏን የምታክበር እና የምታንጽ መሆን አለባት። ሁለቱም ወላጆች ለልጆቻቸው መውደድን እንዲሁም ትክክለኛ ፍቅርን እና አምላካዊ ተግሣጽን መስጠት አለባቸው። ልጅ በወላጆቹ ቸልተኝነት፣ በደል ወይም ፍቺ ምክንያት እነዚህን ነገሮች ካላገኘ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ እድገቱ ሊጎዳ ይችላል።

የቤተሰባችን አባላት፣ ጓደኞቻችን፣ የስራ ባልደረቦቻችን፣ ጎረቤቶቻችን፣ እና የማናውቃቸው ሰዎች እንኳን ቢሆኑ ሆን ብለው ወይም ሳያስቡት ሊያቆስሉን  ይችላሉ። በሚያሳዝን ሁኔታ በጣም የምንወዳቸው ሰዎች ትልቁን ጠባሳ ሊፈጥሩብን ይችላሉ። እኛ ግን ሁሌም ተጠቂዎች አይደለንም። ሌሎችንም ለመጉዳት አቅም አለን። ተጠያቂው ማን ነው? አንተ ነህ? እነሱ ናቸው? አምላክ ነው?

በዚህ ምዕራፍ ሰዎች እርስዎን ሲጎዱ ወይም ሌሎችን ሲጎዱ ምን ማድረግ እንዳለቦት እንመለከታለን።

### ትምህርት 1-የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት

*መዝሙር* 139፡1—18 እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን በቅርበት እንደሚያውቅ እና ዘመኖቻችን ሁሉ በእርሱ የተፈጠሩ እና የተሾሙ መሆናቸውን ያስተምራል።

ከኢሳይያስ 46:9—10 ስለ አምላክ ምን እንማራለን?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

በቃሉ መሰረት እግዚአብሔር ሁሉም ሀይል ያለው ና ሁሉን አዋቂ ነው። በሌላ አነጋገር እርሱ ሉዓላዊ እና ሁሉን አዋቂ ነው።ይህንን እውነት ለመቀበል አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፣

> ***ሉዓላዊ-*** *የበላይ ወይም ከፍተኛ ስልጣን ያለው፣ ከሁሉም በላይ በስልጣን የበላይ፣ ራሱን የቻለ ወይምየበላይ ስልጣን ያለው።*
>
> ***ሁሉን አዋቂ-*** *ሁለንተናዊ እውቀት ያለው ፣ ሁሉንም ነገር ማወቅ ፣ ማቂያ የሌለውጥበበኛ።*

በተለይም ብዙ መከራን ተቋቁመው ና በሌሎች እጅ ለተሰቃዩት። ለምን ሁሉን ቻይና ሁሉን አዋቂ የሆነ አምላክ ልጆቹ እንዲሰቃዩ ይፈቅዳል? ይህ ጥያቄ የብዙ ሰዎችን ልብ ይረብሻል እና በቀላሉ በአምላክ ላይ አለመተማመን ና ቅሬታን ሲያመጣባቸው ይታያል። ደግሞስ እሱ ሁሉንም ነገር የሚያውቅ ከሆነ እና ማንኛውንም ነገር ማድረግ ከቻለ ለሚከሰቱት ነገሮች ሁሉ ተጠያቂ አይደለምን?

*ይህ ጥያቄ አሁንም በአእምሮህ ውስጥ የሚመላለስ ከሆነ፣ ቆም ብለህ ለተወሰነ ጊዜ ከራስህ አንፃር ያለውን ነገር አስብ:: ከሰማይ ሆኖ ምድርን እንደምትመለከት አስብ:: ስለ እግዚአብሔርና ስለ መልካምነቱ የተማርከውን አስታውስ:: እርሱን ታምናለህ?*

*እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው የመምረጥ ነፃነት ሰጥቷል:: የሰው ልጅ እሱን መከተል እና መልካም ማድረግ ወይም መካድ እና ክፉ ማድረግ ይችላል:: ምርጫው ሁሉ በጎም ሆነ መጥፎ ፍሬ ያፈራል:: አማኞችም ሆኑ የማያምኑት በተመሳሳይ መልኩ የምርጫቸውን ውጤት እና በዙሪያቸው ያሉትን ሰዎች ምርጫ ውጤት ያያሉ/ይለማመዳሉ :: በራሳችን መጥፎ ምርጫ ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ መቀበል ከባድ አይደለም፣ ነገር ግን በሌላ ሰው ክፉ ምርጫ ምክንያት መከራ ሲደርስብንስ? ወይስ ከማናቀው ቦታ የመጣብን መከራ/ስቃይ  ሲያጋጥመንስ ?*

*እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ የሰውን ልጅ ክፉን የመምረጥ ችሎታ ቢያቆም፣ ነፃ ፈቃድ ከእንግዲህ አይኖርም ነበር:: በተመሳሳይ፣ እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑትን ከክፉ ቢጠብቅና መልካም ብቻ በሕይወታቸው እንዲኖካ ቢፈቅድ፣ ያላመኑት ሰዎች ከሥቃይ ነፃ የሆነ ሕይወት ዋስትና ለማግኘት ብቻ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይነሳሳሉ:: ወደ እርሱ የተመለስከው ለዚህ ነው? እግዚአብሔር ቀላል ሕይወት እንዲሰጥህና ከክፉ ሁሉ እንዲጠብቅህ ጠብቀህ ነበር?*

**የሰው ስቃይ**

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢዮብ የሚባል ሰው ጥሩ ሕይወት ነበረው:: ሚስት፣ ልጆች እና ብዙ ሰራተኞች እንዲሁም የተሳካ ንግድ ነበረው::

ኢዮብ 1:8ን አንብብ:: እግዚአብሔር እንዴት አየው?

____________________________________________________________________________________________________________________

ኢዮብ 1:9-11ን አንብብ:: ሰይጣን ኢዮብን በተመለከተ ለእግዚአብሔር  ምን አለው?

እግዚአብሔር በቁጥር 12 ላይ ምን ምላሽ ሰጠ?

______________________________________________________________________________

_________________________

______________________________________________________________________________

_________________________

______________________________________________________________________________

_________________________

እግዚአብሔር ሰይጣን በኢዮብ ላይ ክፉ እንዲያመጣ ፈቀደለት፣ ይህም የሁሉም ንብረቱ መጥፋት፣ የሠራተኞቹና የልጆቹ ሞት፣ እና በመጨረሻም የጤንነቱ መሟጠጥን ያጠቃልላል። ኢዮብ እግዚአብሔር ለምን እንዲህ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲሰቃይ እንደፈቀደለት አልተረዳም። ከሁሉም በላይ፣ እርሱ እግዚአብሔርን ይፈራና በጽድቅ ይኖር ነበር። በእርግጥም፣ እንዲህ ዓይነት መከራ እንዲገባው  ምንም ነገር አላደረገም ነበር።

ኢዮብ በኢዮብ 7:20 ምን ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀው?

______________________________________________________________________________

_________________________

______________________________________________________________________________

_________________________

______________________________________________________________________________

_________________________

በተለያዩ ምዕራፎች ላይ እንደምንመለከተው ኢዮብ፣ ለምን ? የሚለው ጥያቄ ተቆጣጥሮት ነበር ። ወደ እግዚአብሔር ጮኽ እንዲሁም ከወዳጆቹ ምክር ጠየቀ። እግዚአብሔር ለተወሰነ ጊዜ ዝም አለ ግን በመጨረሻም ምላሽ ሰጠ።

እግዚአብሔር በኢዮብ 38፡1-3 ላይ ምን አለ?

______________________________________________________________________________

_________________________

____________________________________

እግዚአብሔር ለኢዮብ ጥያቄዎች መልስ አልሰጠም። ይልቁንም፣ በእርሱ ፍጥረት ውስጥ የሚታየውን ኃይሉንና ክብሩን እንዲመለከት የሚያደርጉ ጥያቄዎችን አቀረበለት። የእግዚአብሔር ጥያቄዎች የኢዮብን ትኩረት ከራሱና ከሁኔታዎቹ አውጥተው የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ሰፋ ያለ እይታ እንዲኖረው አደረጉት።

ኢዮብ በኢዮብ 40፡3—5 እና 42፡1—6 ላይ ምን ምላሽ ሰጠ?

____________________________________________________________________________________________________________________________
____________________________________

____________________________________________________________________________________________________________________________
____________________________________

____________________________________________________________________________________________________________________________
____________________________________

መከራ ሲደርስብን ምክንያቱን መፈለግ ተፈጥሯዊ ምላሽ ነው። እኛም እንደ ኢዮብ ለምን ብለን ወደ እግዚአብሔር እንጮሃለን። ነገር ግን ከኢዮብ ከምንማራቸው ብዙ ትምህርቶች አንዱ፣ "ለምን?" የሚለው የተሳሳተ ጥያቄ መሆኑን ነው። በምትኩ፣ "ምን ልታስተምረኝ እየሞከርክ ነው? በዚህ የመከራ ጊዜ ውስጥ ፈቃድህ ለእኔ ምንድን ነው?" ብለን እግዚአብሔርን መጠየቅ አለብን።

እግዚአብሔር አፍቃሪ አባት ነው ክፉውን ወደ ህይወታችን አያመጣም። ሆኖም፣ ለዓላማውና ለመጨረሻ ጥቅማችን ክፉ እንዲነካን ይፈቅዳል። በእርሱ እንድንታመን እምነትን ለምኑት። ጸሎትህን ይመልሳል።

## ትምህርት 2 - ፈተናዎች እና መከራ

ዮሐንስ 16:33ን አንብብ:: ኢየሱስ ፈተናዎችንና መከራን በተመለከተ ለተከታዮቹ ምን አስተምሯቸዋል?

___

___

> **ማካራ**–ከጭቆና፣ ከስደት፣ ከማካራየሚማጣ ጭንቀት ወይም ስቃይ; አንድ ማካራ.

መከራና ሀመም ቃል ተገብቶልናል። መከራን ለማስወገድ ልናደርገው የምንችለው ምንም ነገር ባይኖርም ለእነርሱ የምንሰጠው ምላሽ ግን የእኛ ሃላፊነት ነው ።

ሚልክያስ 3:3ን አንብብ። እግዚአብሔር በእኛ ፈተናዎች ምን ያደርጋል?

___

___

መከራችን ልባችንን በእግዚአብሔርና በሌሎች ላይ እንዲጠነክር ልንፈቅድ ወይም ሁኔታችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን በመስጠት በመከራ ውስጥ ልባችንን እንዲያነጻ እንድንፈቅድለት እንችላለን:: ልብን ማጥራት ወርቅን እንደማጥራት ነው:: ወርቁ በእሳት ሲሞቅ ቆሻሻዎቹ ወደ ላይ ይወጣሉ ስለዚህ ሊወገዱ ይችላሉ:: እግዚአብሔር እያንዳንዳችን መከራን እንድንታገስ የሚፈቅደው እንድንጣራና ወደ ክርስቶስ መልክ እንድንለወጥ ነው::

1ኛ ጴጥሮስ 1፡6-7 ስለ ፈተናዎቻችን ምን ይላል?

___

___

መከራ በበዛብን ቁጥር፣ እንጠራለን:: መከራዎች የልባችንን ሁኔታ ለመፈተሽ ብቸኛው መንገድ ናቸው:: ወርቅ በውጫዊ መልኩ ንጹህ ሊመስል ይችላል፣ ነገር ግን በማይታየው ውስጡ ብዙ ቆሻሻዎች ሊኖሩበት ይችላሉ:: መከራዎቻችን በልባችን ጥልቀት ውስጥ ምን እንደተደበቀ ያሳያሉ:: በዚህ ሂደት ውስጥ በእግዚአብሔር የምንታመን ከሆነ፣ ህይወታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር፣ ተስፋ እና በራስ መተማመን ይሞላል::

ሮሜ 8፡28-29 ጻፍ::

___

ቁጥር 28 በግልጽ "ሁሉም ነገር ለበጎ ይሠራል" ይላል። ቁልፉ እምነት ነው። የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ለማመንና በመከራችንና በችግራችን መካከል በእርሱ ለመታመን ከመረጥን፣ ድል እንቀዳጃለን፣ እግዚአብሔርም ይከበራል። በመከራችን ጊዜ ምግባራችንን የሚመለከቱ ሰዎች የክርስቶስን ሥራ በሕይወታችን ውስጥ ሊያዩ ይችላሉ፣በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም የእርሱን ነጸብራቅ በእኛ ውስጥ ሊያዩ ይችላሉ።

ኢዮብ በመከራው ጊዜ ታማኝ አገልጋይ ሆኖ ቆይቷል ይህም የበለጠ መታመንን፣የበለጠ እምነት እና ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ የሆነ ቅርርብ አስከትሏል።

ኢዮብ 42:11—16ን አንብብ። አምላክ ኢዮብን መከራ እንዲቀበል ያደረገው እንዴት ነው (ቁጥር 11)?

የቀረው የኢዮብ ሕይወት ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 12-16)?

ኢዮብ ለደረሰበት መከራ እግዚአብሔርን ለመውቀስ ፈቃደኛ አልሆነም እናም በሥቃዩ እግዚአብሔርን ታምኗል። ኢዮብ በአምላክ ላይ ባለው እምነት ምክንያት የምሬት/ቂም ቦታ በልቡ ውስጥ እንዲቀመጥ አላረገም ። የኢዮብ እምነት በቤተሰቡና በወዳጆቹ አማካኝነት በሰማይ ከሚኖረው አባቱ ማጽናኛ እንዲያገኝ አስችሎታል። በተጨማሪም አምላክ በኢዮብ ታማኝነት ምክንያት ከዚህ በፊት ከነበረው በእጥፍ ባርኮታል።

ይህ ማለት ግን መከራ ሁሉ የተትረፈረፈ ምድራዊ በረከት ያስገኛል ማለት አይደለም። በተቃራኒው በዚህ ህይወት ውስጥ የተረጋገጠው ብቸኛው ነገር ችግር ነው.። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ምንም አይነት ስቃይ፣ ፈተና ወይም መከራ ቢያጋጥመን እንኳን ፣ እንባ ወይም ስቃይ በማይኖርበት ለዘለአለም እግዚአብሔር ባለበት ልንኖር ተስፋ አለን።

2 ቆሮንቶስ 1:3—4ን አንብብ። የእርስዎን ተሞክሮ ሌሎችን ለመርዳት እንዴት መጠቀም ይቻላል?

_______________________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________________

> ኢየሱስ እንዳለው እግዚአብሔር ጨለማን ከእናንተ ላይ የማያነሳበት ጊዜ አለ፣ ነገር ግን በእርሱ እመኑ። እግዚአብሔር ደግነት የጎደለው ወዳጅ ይመስላል፣ነገር ግን እሱ አይደለም፣ እርሱ ከተፈጥሮ ውጭ የሆነ አባት ይመስላል፣ ነገር ግን አይደለም፤ እንደ መጥፎ ዳኛ ይመስላል ነገር ግን አይደለም።ምንም አይነት ነገር ጠንክሮ እያደገ ቢሄድም ከእግዚአብሄር ሀሳብ በታች አርገው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ከጀርባው ከሌለ በስተቀር ማንኛውም ሁኔታ አይከሰትም፣ስለዚህም በእሱ ላይ በፍጹም መተማመን ማረፍ ይችላሉ- ***ኦስዋልድ ቻምበርስ***

እግዚአብሔር የዘላለም እቅድ አለው፡ መልካም ነገር ያሸንፋል ሁሉም ክፋት፣ መከራና ሐዘንም ይቆማል። ህመም/ጉዳት ያደረሱብንን ሰዎች ላይ ቂም ማከማቸት ወይም በሉዓላዊው አምላክ ላይ እምነት በመጣል የሌሎችን በደሎችና ድክመቶች ይቅር ማለት እንችላለን።

ክርስቶስን እንደ መድኃኒትና ጌታ ስትቀበል፣ ለዘላለም ዕጣ ፈንታህ በእርሱ ላይ እምነትህን አድርገሃል። ከቀድሞ ልምምዶችህና ከአሁን ሁኔታዎችህ ጋርም በእርሱ መታመን አለብህ። እርሱ ብቻ በመከራዎችህ ውስጥና በኩል ሊያጽናናህና በትክክል ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ጥንካሬ ሊሰጥህ ይችላል። እርሱ ብቻ ከመጥፎው መልካም ነገር ሊያመጣና የተሰበሩ ግንኙነቶችን ሊመልስ ይችላል። በመከራህ ጊዜ ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝህ ሰላም ይሰጥሃል እንዲሁም ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና፣ ክብርና ሞገስ ያመጣል።

1 ጴጥሮስ 1:3—7ን አንብብ። ይህ ጥቅስ ከእርስዎ ሁኔታ ጋር እንዴት ይሠራል?

_______________________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________________

| መሰረታዊ እውነት |
| --- |
| የእግዚአብሔር ቃል በመከራችንና በችግራችን እኛን ወደ እሱ ሊጠጋ እንዲለውጠንና ተመሳሳይ ልምድ ያላቸውን ሌሎችን ለማጽናናት እንድንዘጋጅ እንደሚጠቀም ይነግረናል። |

**ትምህርት 3–ይቅር የምንለው ለምንድን ነው?**

***ጌታ አባቴን ይቅር እንድለው እንደሚፈልግ በልቤ በተሰማኝ ጊዜ፣ ወዲያው ተቃወምኩት:: ምሬቴን/ቂምን መተው ሳልፈልግ ለብዙ ሳምንታት ከእግዚአብሔር ጋር ታገልኩ:: ለምን ይቅር እላለው? እሱ ፈጽሞ ይቅርታ አልጠየቀኝም:: ይቅርታ ይገባዋል ወይ?***

***ይቅር ማለት-*** *መተው፣ በተፈጸመው በደል ምክንያት የተያዘን ቂም መተው፣ ይቅርታ ማድረግ፣ ይቅር ማለት።*

እዳ ሲሰረዝ፣ ቀሪ ክፍያዎች ሁሉ ይተዋሉ። እኔ የበደለኝን ሰው ይቅር ካልኩ፣ በእነርሱ ላይ ቁጣዬንና ቂሜን የመቀጠል ነፃነቴን አስወግዳለሁ። የበቀል እርምጃ የመውሰድ ነፃነቴንም አስወግዳለሁ። የራሴን ኃይል እተወዋለሁ ኪሳራውንም እራሴ እወስዳለሁ። እውነተኛ ይቅርታ ያልተገባ፣ ያልተመሰገነና ነፃ ነው። ፍትሃዊ ወይም ትክክል አይደለም። ታዲያ ለምን ይቅር ማለት ያስፈልጋል?

**እግዚአብሔር ይቅርታን ያዛል:: በሉቃስ 6:35-37 ላይ ኢየሱስ ምን አለ?**

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

በቆላስይስ 3:12-13 ውስጥ የእግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች ባህሪያት ምንድን ናቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

***ለሰማዩ አባታችን መታዘዝ አማራጭ አይደለም:: ከራሳችን ፍላጎት በመነሳት ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ውስጥ የመረጥነውን ብቻ ልንታዘዝ ከመረጥን የምንኖረው ህይወት ፍሬ አልባ፣ ውጤታማ ያልሆነ እና በመንፈሳዊ መካን ህይወት ነው ::***

ይቅር የሚሉ የክርስቶስ ምስክር ናቸው :: በሉቃስ 23:34 ላይ የኢየሱስ ጸሎት ምን ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

***እንደ ክርስቲያኖች፣ የክርስቶስን ስም ወደ ጠፉት የማድረስ መብትና ጥሪ አለን:: "ክርስቲያን" የሚለው ቃል "ትንሹ ክርስቶስ" ማለት ነው:: እርሱ እንደተጓዘ መሄድ አለብን::***

ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ለበደለኞች ይቅርታን ለማምጣት ነው፣ በመስቀል ላይ ያለውን የመጨረሻውን የይቅርታ ተግባር አሳይቷል። ቤተክርስቲያንን በአለም ላይ ይቅርታን ማወጅ እንድትቀጥል አዟል። ስሙን መሸከም ካለብን፣ የበደሉንን ይቅር ማለት አለብን። የይቅርታ ዓላማ ምንድን ነው?

**ይቅርታ የወቀሳ እና የስቃይን ሰንሰለት ይሰብራል።**

ለራሳችን ታማኝ ብንሆን፣ አንድን ሰው ለበደሎቹ ያለማቋረጥ መውቀስ ምን ያህል የሚያም እንደሆነ እንቀበላለን። ምናልባትም ከበደሉ ራሱ የበለጠ የሚያም ሊሆን ይችላል። በተለይም ለማስተካከል የሚፈልጉ ከሆነ ለበደለኛውም ያማል። ይቅርታን መስጠት ከባድ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የክስና የፍትሃዊነት ጥያቄዎችን ሁሉ ስለማይፈታ፤ በሚገርም ሁኔታ ግን እነዚህ ጥያቄዎች ይቅርታው ከተሰጠ በኋላ ምንም ትርጉም አይኖራቸውም። ይቅርታ ከክርክር መውጫ መንገድን ይሰጣል እና ግንኙነት እንደገና እንዲጀመር ያስችላል።

በዘፍጥረት 37-45 ላይ የተመዘገበው የዮሴፍ ሕይወት የይቅርታን ኃይል በሚያምር ሁኔታ ያሳያል። የዮሴፍን ታሪክ ካላነበባችሁ፣ እንድታነቡት እመክራለሁ። ዮሴፍ በተሳሳተ ሁኔታ ተረድተውታል፣ በደል ደርሶበታል፣ ተከድቷል፣ ተጥሏል፣ በራሱ ወንድሞች እንኳን ለባርነት ተሸጧል። በደረሰበት ነገር ሁሉ፣ የምሬት ሥር በሕይወቱ ውስጥ እንዲሰድ አልፈቀደም። ከዓመታት መለያየት በኋላ ከወንድሞቹ ጋር ከመገናኘቱ ትንሽ ቀደም ብሎ፣ የመጀመሪያ ልጁን ምናሴ እና ሁለተኛ ልጁን ኤፍሬም ብሎ በመሰየም እግዚአብሔር በህይወቱ ያከናወነውን የፈውስ ሥራ መሰከረ።

ዘፍጥረት 41:51—52ን አንብብ። እነዚህ ሁለት ስሞች ምን ማለት ናቸው?

_________________________________________________________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________________________________________________________

በዚህ ዐውድ ውስጥ መርሳት ማለት ማስታወስን ማቆም ማለት ሳይሆን፣ ይልቁንም መተው ማለት ነው—የሚያሠቃዩ ነገሮች ትውስታ የአሁኑን ሕይወትህ እንዲቆጣጠር መፍቀድን ማቆም ማለት ነው። ዮሴፍ በወንድሞቹ ምክንያት አስከፊ ሁኔታዎችን ተቋቁሟል። በእነርሱ ላይ በምሬት ከመገንፈል ይልቅ፣ በግብፅ ውስጥ ብቻውን ባሳለፋቸው ረጅም ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር የተሰበረ ልቡን እንዲፈውስ ፈቀደለት። የዮሴፍ ፍሬያማነት ከመርሳቱ ጋር በቀጥታ የተገናኘ ነበር። ስሜቱንና ስሜታዊነቱን እንዲሁም ያለፈው ጊዜውን ለእግዚአብሔር እንዲታመን መረጠ ። እድሉ ሲሰጠውም ለወንድሞቹ ፍቅር፣ ይቅርታና ጸጋን ዘረጋላቸው።

ዘፍጥረት 45:5—8ን አንብብ። ዮሴፍ ለወንድሞቹ ምን አለ?

_________________________________________________________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________________________________________________________

ዘፍጥረት 45:15 አንብብ። ዮሴፍ ምን አደረገ?

ዮሴፍ አልወቀሳቸውም ወይም ስለበደላቸው ማብራሪያ አልጠየቀም፣ ዝም ብሎ ምሕረትንና ይቅርታን አቀረበላቸው። ዮሴፍ እና ወንድሞቹ እንደገና እንዲገናኙ እና አዲስ ህይወት እንዲጀምሩ ይቅርታ መንገዱን ጠርጓል።

**ይቅርታ በበደለኛው ላይ ያለውን የጥፋተኝነት ሸክም ያስወግዳል።**

ዘፍጥረት 50:15ን አንብብ። የዮሴፍ ወንድሞች ምን ፈሩ?

በዘፍጥረት 50፡19-21 ዮሴፍ ምን ምላሽ ሰጠ?

**ወንድሞቹ  ሐዘናቸውንና በደላቸውን ተሸክመው ወደ መቃብራቸው ይሄዱ ነበር፣ ነገር ግን ዮሴፍ ይቅርታ ሰጣቸው። ያላገኙትን እና የማይገባቸው ይቅርታ በመስጠት ጥፋታቸውን አስወግዶ ግንኙነታቸውን መልሷል። ይህ የተለመደ ይመስላሀል ?**

| መሰረታደዊ እውነት |
| --- |
| እግዚአብሔር ሁሉምሰውይቅር እንዲል ያዛል። የሚታዘዙት የልጁን ምሳሌ ይይዛሉ በዚህም ፈውስ እና እርቅ እንዲጀምር ያርጋሉ። |

ኃጢአት ወደ ዓለም በገባ ጊዜ በበደላችን እና በኀፍረታችን እንድንኖር ለዘላለም ተፈርዶብን ነበር። እግዚአብሔር ግን በደላችንን እንዲያስወግድ እና ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት እንዲያድስ ክርስቶስን በመላክ እጁን ለይቅርታ ዘረጋ። በክርስቶስ የተቀበልከው ይቅርታ ይገባሃል?

## ትምህርት 4-ይቅር አለማለት የሚያስከፍለው ዋጋ

ይቅርታ ነፃ ቢሆንም፣ ይቅር አለማለት ግን ዋጋ ያስክፍላል ። ይቅርታ አለማለት ለተፈፀመው ጥፋት የክፍያ መብትን መጠየቅ ማለት ነው። ይቅር ለማለት ፈቃደኛ አለመሆን ምሬትን እና ቂም መያዝን ያስከትላል።

ቂም መያዝ ያለፈውን በደል ደጋግመን እንድናስታውስ ያረገናል ። ቂም ማለት ያልዳነ ቁስል ላይ ያሉ ቅርፊቶችን እንደማንሳት ማለት ነው ይህም መፈወስን/ መዳንን ይከለክላል። ምሬት መርዝ ነው ያገኘውን ሁሉ ይጎዳል ። በልብዎ ውስጥ ምሬት/ቂም ካለ በሁሉም ግንኙነቶችዎ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል እንዲሁም እያሳደረም ይቀጥላል። መድኃኒቱ ይቅርታ ብቻ ነው።

*__ምሬት-__ ክፉ ነቀፋ ; በጥላቻ ወይም በጭካኔ ባህሪውተለይቶ ይታወቃል።*

*__ቂም—__ አንድ ሰው በሆነ ነገር በተሳሳተ፣ በስድብ ወይም በማሳሰሉት ነገሮች ምክንያት የሚሰማው የቁጣና የብስጭት ስሜት ሲሆን ብዙውን ጊዜ ከጥላቻ፣ ከጠላትነት እና ከክፋት ጋር ይደባለቃል።*

*__መበገን-__ ኃይለኛ ቁጣ፣ ጥልቅ እና ቁርጥ ያለ ቁጣ፣ ብዙውን ጊዜ ቁጣ፣ ሜናደድ።*

*__ቁጣ__ ማባሳጩት; ጠንካራ የብስጭት ስሜት።*

ዕብራውያን 12፡15 ስለ መራርነት ምን ይላል?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

መራርነት በልብ ውስጥ ሥር ሰድዶ መራራ ፍሬን በማፍራት ችግርን ይፈጥራል፣ ግንኙነትን ያበላሻል ፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን ሊያፈራ የሚፈልገውን መልካም ፍሬ እንዳያድግ ይከለክላል ።

ኤፌሶን 4:31ን አንብብ። መራርነትን የሙጥኝ ባለ ሰው ልብ ውስጥ ምን ማስረጃ አለ?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

### የይቅርታ ፍሬ

ከሚከተሉት ባህርያት ውስጥ በህይወቶ ውስጥ በግልጽ ይታያሉን ? ከምታያቸው ቀጥሎ ምልክት አድርግ።

| | |
|---|---|
| ኩራት | ራስን ማጽደቅ |
| እራስን መውቀስ /ስለራስ ማዘን | ስሜታዊ አለመረጋጋት |

ጭንቀት፣ ውጥረት እና ጫና
የአመጋገብ ችግሮች/መዛባቶች
በትዳር ውስጥ መተማመን አለመኖር
በሌሎች ላይ ዳኝነት እና ነቃፊነት መሰኘት
ሰላም እና ደስታ አለመኖር

የጤና ችግሮች
በግንኙነቶች ላይ እምነት ማጣት
የወሲብ ችግር
እጅግ በጣም ስሜታዊ መሆንና በቀላሉ ቅር
ከኢየሱስ ጋር የተበላሸ ህብረት

| |
|---|
| መሰረታዊ እውነት<br>ይቅርታ አለማድረግ ወደ ምሬት ያመራል፣ ሌሎች ግንኙነቶችንም ይጎዳል ፣ የሰውን ምልብ ይረብሻል። |

ኢየሱስ ይቅር ለማለት አሻፈረኝ ለሚሉ ሰዎች የሚያመጣባቸውን መዘዝ አስመልክቶ ለደቀ መዛሙርቱ በምሳሌ ተናግሯል። ማቴዎስ 18:21–35ን አንብብ።

በቁጥር 27 ላይ ጌታው ለአገልጋዩ ያለው አመለካከት ምን ነበር?

______________________________________________________________________________
________________________________

______________________________________________________________________________
________________________________

______________________________________________________________________________
_____________________________________

አገልጋዩ በቁጥር 28 ላይ አገልጋዩን እንዴት አድርጎት ነበር?

______________________________________________________________________________
________________________________

______________________________________________________________________________
________________________________

በቁጥር 34 መሠረት አገልጋዩ ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጌታው ምን ምላሽ ሰጠ?

______________________________________________________________________________
________________________________

______________________________________________________________________________
________________________________

ኢየሱስ በቁጥር 35 ላይ ያስጠነቀቀው ምንድን ነው?

______________________________________________________________________________
________________________________

_______________________________________________________________________________
_______________________________

_______________________________________________________________________________
_______________________________

እስቲ መስቀሉን አናስብ፣  ከክርስቶስ የተቀበልነውን ይቅርታ እና ድሀነት እናስብ ። እንዴት ነው የእርሱን ይቅርታ መቀበል የምንችለው እና ለሌሎች ይቅርታን ለመስጠት እምቢ ማለት የምንችለው?

ይህ ምሳሌ ዳግመኛ የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ይቅር ለማለት ካልፈለገ ዘላለማዊ ጥፋት እንደሚደርስበት አያስተምርም። ነገር ግን፣ይቅር ባለማለታችው  ያለፈውን ህመም ለማስታገስ በማያቋርጥ አዙሪት ውስጥ ተጣብቀው እንደሚታሰሩ ያስተምራል። በራሳችን እና በሌሎች ሰዎች ከሚደርስብን  ህመም/በደል ነፃ መሆን ይቻላልን ? ኃጢአትና ስብራት በሞላበት ዓለም ውስጥ ከሌሎች ጋር ተስማምተን መኖር ያለብን እንዴት ነው?

ትምህርት 5–እርስ በርስ መተሳሰብ የሚቻለው እንዴት ነው

ጎረቤትህን ውደድ

መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርስ እንዴት መተሳሰብ እንዳለብን ግልጽ መመሪያ ይሰጣል።

ማቴዎስ 22:37-40ን አንብብ። ኢየሱስ እንደተናገረው ሁለቱ ታላላቅ ትእዛዛት የትኞቹ ናቸው?

________________________________________________________________________
____________________________

________________________________________________________________________
____________________________

ኢየሱስ ራሱ እንዳለው እኛ ለሌሎች ያለን ፍቅር ለእርሱ ካለን ፍቅር ጋር እኩል መሆን እንዳለበት ነው። የትኛውን ነው ቀላል ሆኖ ያገኙት? በእርግጥ ያ ጥያቄ መልስ የማይገኝለት ነው። በመጀመሪያ የሚወድህን ሰው በአንተ ቦታ ህይወቱን እስከመስጠት ድረስ መውደድ ከባድ አይደለም። ነገር ግን ያለማቋረጥ የሚሳሳቱ፣ በሁኔታዎች ላይ ተመስርተው እና ፍፁምነት የጎደለው መንገድ የሚወዱ፣ እና ባለማወቅ ወይም ሆን ብለው ህመም/ጉዳት ያደረሱብህን ማፍቀር ቀላል ነውን?

1 ዮሐንስ 4:19—21ን ጠቅለል አድርገህ ፃፈው ።

________________________________________________________________________
____________________________

________________________________________________________________________

የምንማረው የመጀመሪያው ነጥብ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ለእኛ ላለው ፍቅር ምላሽ መሆኑን ነው። ሁለተኛው ነጥብ እግዚአብሔርን መውደድ ሌሎችንም መውደድን ይጨምራል። በሕይወታችሁ ውስጥ ያስቀመጣቸውን ሰዎች ሳንወድ የእግዚአብሔር ፍቅር ልንቀበል አንችልም።

ሮሜ 13፡8-10ን አንብብ። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ለእርስዎ ትኩረቶን የሳበ የትኛው ነው ?

________________________________________________________________________
____________________________

________________________________________________________________________
____________________________

እንደ ክርስቲያን ለጎረቤትህ ፍቅር ሊኖርህ እዳ አለብህ ። ይህን ግምት ውስጥ አስገብተሀል ? የኃጢያትህ ዕዳ የለብህም ምክን ያቱም ክርስቶስ ያንን እዳ በመስቀል ላይ ስለከፈለ። ነገር ግን የእርሱን ማዳን በመቀበል ጎረብትህን/ባልንጀራህን  የመውደድ እዳ ትሸከማለህ። *በእርግጥም* ከጎረቤቶችህ ውስጥ *ይህንን* ወይም *ያንን* ሰው አያካትትም ምክንያቱም ያደረገብኝ ብዙ

መጥፎ ነገር አለ ብለው እያሰቡ ይሆን ?!

ማቴዎስ 5:43—48ን ጠቅለል አድርገህ ፃፍ ።

__________________________________________________________________

____________________________

__________________________________________________________________

____________________________

ፍቅርህን ከማን መከልከል ትችላለህ? መልሱ ማንም አይደለም። ሁሉንም ሰው የመውደድ እዳ አለብህ። ለምን?

1ኛ ቆሮንቶስ 6፡20 ከዚህ በታች ጻፍ።

__________________________________________________________________

____________________________

__________________________________________________________________

____________________________

ለማንም ልዩነት ሳታደርጉ ክርስቶስን ለሁሉም ሰው ልታከብሩና ልታንጸባርቁ ይገባል። በሌሎች ላይ ያላችሁ ያልተወደዱ ወይም ከክርስቶስ ጋር የማይመሳሰሉ ሐሳቦች ወይም ባህሪያት ምንም ምክንያት የላቸውም እናም እግዚአብሔር ፊት ንስሀ መግባት አእንዲሁም ሰውየውን ይቅርታ መጠየቅ ግድ ይላል።

ኢየሱስ በማቴዎስ 5፡23-24 ምን አስተምሯል?

__________________________________________________________________

____________________________

__________________________________________________________________

____________________________

ወደ መሠዊያው የምንሄደው መቼ ነው? መሠዊያ የሚያመለክተው ከኢየሱስ ጋር ያለንን ኅብረት ማለትም የጸሎትና የአምልኮ ጊዜያችንን እንዲሁም በስሙ የሚደረግን ማንኛውንም አገልግሎት ነው። ኢየሱስ ከሌሎች ጋር ያለን ግንኙነት ለእርሱ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስተምሯል። እሱ በቀላሉ የሚመለከተው ነገር አይደለም እኛም ደግሞ እንደዚሁ የለብንም። ይቅርታ የምትፈልጉት ሰው ካለ ወይም ይቅር ልትሉት የሚገባችሁ ካለ፣ ኢየሱስ በዚህ ጊዜ ከእነሱ ጋር እንድትታረቁ እያዘዛችሁ ነው።

**እርቅ**

የእግዚአብሔር ልብ የሰው ልጅ ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ የተሰበረውን ሁሉ መመለስ ይፈልጋል። ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣበት ምክንያት ይህን በእግዚአብሔር እና በፍጥረቱ መካከል በኃጢአት ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት ለማስተካከል ነው ።
በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል ያለው ግንኙነት ታርቋል።

ከእግዚአብሔር ጋር የታረቀ ግንኙነት የምንቀበለው ትልቁ ስጦታ እና ትልቁ የእግዚአብሔር የልብ ፍላጎት ነው፣ ነገር ግን ይህ ተሃድሶ ገና ጅምር ነው። ኤፌሶን 4:31–32ን አንብብ። ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት የእግዚአብሔር ፍላጎት ምንድን ነው?

> ***መታረቅ*-** *ጓደኝነትን, ሰላምን ወይም ማግስን እንደገና መመለስ; ወደ ስምምነት መመለስ; መልሶ ለማግኘት; ህብረትን መመለስ.*

**ብዙ ክርስቲያኖች በአንድ ሰው ላይ ምሬትን፣ ቂም ወይም ይቅር አለማለትን ይይዛሉ ። እነዚህ ስሜቶች የበደላቸው ሰው ያሳደረባቸው ምክንያታዊ ና ስሜታዊ ምላሽ ናቸው ብሎ በቀላሉ መደምደም ይቻላል ። ምናልባት እነሱን የጎዳው ሰው ለሠራው ነገር በቂ ሥቃይ አልደረሰበትም ወይም ለባህሪያቸው በቂ ኃላፊነትም አልወሰደም.ይሆናል ። የቆሰሉበትን ሁኔታ ለሌሎች በማስረዳት ና ላሳለፉበት ችግር ሀዘናቸውን ለማጋራት እና ሃዘኔታ ለማግኘት ይሞክራሉ። ልታገናኘው ትችላለህ?**

> **የሌሎችን ይቅር ለማለት የምችልበትና የምፈቅድበት ደረጃ እኔ በግሌ የእግዚአብሔር የአባቴን ይቅርታ ምን ያህል እንደተለማመድኩኝ ግልጽ ማሳያ ነው። –ፊሊፕ ኬለር**

**በህይወትዎ ውስጥ ያሉትን ያለፈውን እና የአሁኑን ግንኙነቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ። ያልታረቅከው ሰው አለ? የጎዳህ ወይም ያስቀየመክ ሰው አለ? ወደ አእምሮ የሚመጣው ማን ነው?**

**በልብህ ውስጥ ምሬት፣ ቂም ወይም ይቅርታ አለማድረግ ስሜት ከተሰማህ ና ምንጩን ከየት እንደሆነ እርግጠኛ ካልሆንክ ሃሳብህን ከዚህ በታች ጻፍ።**

**ይቅርታና እርቅ ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን መረዳት አስፈላጊ ነው። ይቅርታ በህመም ላስከተለባችሁ ለማንኛውም ሰው ሊሰጥ ይችላል፣ ነገር ግን እግዚአብሔራዊ እርቅ ቀደም ሲል**

ለነበሩና ለተበላሹ ግንኙነቶች ነው። ከማያውቋቸው ወይም ከአጋጣሚ ሰዎች ጋር መታረቅ አስፈላጊ አይደለም።

እንዲሁም ጥበብ የተሞላባቸው ድንበሮችን የሚጠይቁ አንዳንድ የታረቁ ግንኙነቶች አሉ። ይቅርታና እርቅ ሌላውን ሰው በንቀት ወይም በጭካኔ እንዲይዝህ ነፃነት አይሰጡትም። የጎዱህ አንዳንድ ሰዎች ይቅር ብትላቸውም በኋላም ስሜታዊ ወይም አካላዊ ህመም ሊያስከትሉብህ ይችላሉ። ለስሜታዊና ለአካላዊ ደህንነትህ ድንበሮችን ማበጀት አስፈላጊ ነው። የተሳካ እርቅ በሰላምና በቸርነት የታጀበ ይሆናል፣ ነገር ግን ጥበብ የሌለው እርቅ ወደ ተጨማሪ ጉዳትና ሁከት ይመራል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ለታረቁ ግንኙነቶችህ ጥበብ የተሞላባቸው ድንበሮችን እንድታስቀምጥ ከእረኛህ ወይም ከጎለመሰ ክርስቲያን ጓደኛህ ምክር ጠይቅ።

## ትምህርት 6-የይቅርታ እርምጃዎች

## ይቅር ማለት ካስፈለገዎት

*መንፈስ ቅዱስን እርቅ ያልፈፀምክበትና ባንተ ሃጥያት ምክንያት የተጎዳ ግንኙነት ካለ እንዲገልፅልህ ጠይቀው ። ማሰብ ያለብህ በሌሎች ላይ እንዴት በአሁኑ ሰአት ጉዳት እንዳደረስክ ለጊዜው ላታውቅ እንደምትችል ነው ። መንፈስ ቅዱስ በማናቸውም ግንኙነቶችህ ማለትም ያለፈው፣ የአሁን፣ ወይም ወደፊት አንድ ወቅት ላይ ኃጢአትህን ከገለጠ እራስህን ዝቅ አድርገህ እነዚህን እርምጃዎች መከተል አለብህ።*

*ደረጃ 1፡ ኃጢአትህን ለእግዚአብሔር ተናዘዝ እና ይቅር እንዲልህ ለምነው።*

1 ዮሐንስ 1:9ን *አንብብ። ኃጢአታችንን ለእርሱ ስንናዘዝ እግዚአብሔር ምን ምላሽ ይሰጣል?*

__________________________________________________________________

____________________________

*መዝሙር* 103:12ን *አንብብ። ኃጢአታችንን ምን ያደርገዋል* ?

__________________________________________________________________

____________________________

__________________________________________________________________

*አሁን ቆም በልና ስለ ሠራኸው ልዩ ኃጢአትህ ለእግዚአብሔር ጮኸህ ምሕረት እንዲያደርግልህ ጠይቀው። በእምነት የእግዚአብሔርን ፍጹም ይቅርታና መንጻት ተቀበል። መንፈስ ቅዱስ ልብህን በፍቅሩ እንዲሞላውና የሚቀጥለውን እርምጃ ለመታዘዝ ጥንካሬና ፈቃደኝነት እንዲሰጥህ ለምነው።*

### ደረጃ 2: የበደላችሁትን ሰው በትህትና ይቅርታ አድርጉለት እንዲሁም ይቅርታን ጠይቁ።

በእንግሊዘኛ ቋንቋ ውስጥ ካሉት በጣም ኃይለኛ ሀረጎች አንዱ “ተሳስቻለሁ። እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ” ነው። ከቻልክ እነዚህን ቃላት ፊት ለፊት እንድታካፍላቸው አበረታታለሁ። የበለጠ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል ግን አብዛኛውን ጊዜ የበለጠ ውጤታማ ነው። ነገር ግን፣ ያለበት ቦታ መድረስ ካልቻልክ፣ በማንኛውም ተገቢ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች በስልክ ወይም በጽሁፍ ማካፈል/መጠየቅ ሊያስፈልግህ ይችላል። ኩራት፣ ትኩረት የሚከፋፍልብህ(አታላይ ነገሮች) ወይም ሌሎች መሰናክሎችህ ይህን የመታዘዝ ተግባር እንዲያዘገዩህ አትፍቀድ።

> መሰረታዊ እውነት
> ወደ ተበድለን ሁሉ ሄደን በትህትና ይቅርታ እንድንጠይቅ የእግዚአብሔር ቃል ያዘናል።

ለበለጠ ድጋፍ፣ ታማኝ የሆነ የክርስቲያን ጓደኛ ካንተ ጋር እንዲጸልይ እና አንት ከበደልካቸው ጋር እንድትታረቅ እንዲያደርጉህ ጠይቅ ።

## ይቅር ማለት ካስፈለግህ

በልብህ ውስጥ ምሬት ይዘህ የምትኖርባቸውን ሰዎች እንዲገልጽልህ መንፈስ ቅዱስን ጠይቅ።

እግዚአብሔር በልብህ ላይ ፈውስን እንዲያመጣ ለመፍቀድ፣ ራስህን ዝቅ ማድረግና እነዚህን እርምጃዎች መከተል አለብህ።

ደረጃ 1: በታዛዥነት ይቅር ለማለት ጥንካሬን ከእግዚአብሔርን ጠይቅ።

ከ1ኛ ዮሐንስ 5:14 እና ማቴዎስ 21:22 ምን ትማራለህ?

___________________________________________________________________________

______________________________

___________________________________________________________________________

ይቅርታ ልብ እግዚአብሔር ሊሰጥህ የሚፈልገው ባህሪ ነው፣ ነገር ግን ልትጠይቀው ይገባል። በተፈጥሮ አይመጣም አንዳንድ ጊዜም እጅግ በጣም ከባድ ይሆናል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ለመታዘዝ የሚያስፈልግህን ኃይል እንደሚሰጥህ በገባው ቃል ታማኝ ይሆናል።

**ደረጃ 2: ይቅርታህን ተናገር።**

ይቅር ማለት የሚለው ቃል ግስ ሲሆን ይህም ተግባርን የሚጠይቅ መሆኑ ግልፅ ነው ። በብቸኝነት የሚደረግ ያለፈ የቃላት አገላለጽ  አይደለም። ልክ እንደ ስጦታ ለአንድ ሰው መስጠት አለበት። ለምሳሌ እኔ ለራሴ *ለፔጥሮስ ይህንን እርሳስ ሰጣለሁ አልኩ* ፣ ግን እርሳሱን በአካል ሄጄ አልሰጠሁትም፣ ስለዚህ ለፔጥሮስ እርሳሱን ሰጠሁት? እንዳልሆነ ግልጽ ነው። እርሳሱን ለጴጥሮስ  ልሰጠው ዘንድ የመስጠት  ስሜቴ እስኪመጣ  መጠበቅ የለብኝም። በተጨማሪም እርሳሱ ለመስጠት የሚገባው መስሎ እስኪታየኝ ድረስ መጠበቅ አያስፈልገኝም ። እውነታው ግን ለጴጥሮስ እርሳሱን እንድሰጠው ዘንድ እግዚአብሔር ያዛል። ካሱ ያለው በኔ ሜዳ ነው ፣ወይ ሙሉ በሙሉ በታዛዥነት ለመኖር ካልሆነም እርሳሱን ባለመስጠት ምሬትን/ቂም መያዝን  ማስቀጠል ።

ይቅርታ ማድረግ ቀላል ነገር አይደለም። ስለዚህ ብቻህን ለመቆም መሞከር የለብህም ። ሀላፊነት የሚሰማውና ድጋፍ የሚያደርግህን የበሰለ ክርስቲያን ጓደኛ ፈልግ ፣ ለእግዚአብሔር በመገዛት ይቅርታ ለማድረግ ታዛዥ እንድትሆን ዘንድ ።

> ይቅር ማለት ስሜት አይደለም። . . . ይቅር ማለት የፈቃድ ተግባር ነው፣ ፈቃዱም የልብ ሙቀት ምንም ይሁን ምን ሊሠራ ይችላል። – ***ኮሪ ቴን ቡም***

**ደረጃ 3: ጥላቻን/ምሬትን ስለያዝክ ይቅርታን ጠይቅ።**

በአንተ ላይ ለተፈጸመው ኃጢአት ይቅርታ አለማድረግ ምክንያት ሊሆን አይችልም ። ይቅርታን አለመቀበልም እንዲሁም ምሬትን እና ቂምን በልባችሁ ውስጥ ማኖር እኩል ኃጢያተኝነት ነው ስለዚህም ለትክክለኛ እርቅ ንስሃ መግባት አስፈላጊ ነው ።

በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በሎጂስቲክስ፣ በጉዞ ዋጋ፣ በአንተ ደህንነት፣ ወይም የሌላኛው ሰው ለረጅም ጊዜ ዝም ብሎ መናገር የሚያስፈልግህን ነገር እንድትናገር ለማድረግ የሚያስጠብቅህ ከሆነ ፣በደብዳቤ፣ በኢሜል ወይም የስልክ ጥሪ ይቅርታህን የምትገልጽበት ጥሩ  መንገድ ሊሆን  ይችላል።

በጽሑፍ ሀሳብ ስትለዋወጥ ወይም ስትናገር የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውል፡-

1. ይህን የምታደርጉት ለሚወድህ እና ለሚንከባከባክብህ ለሰማዩ አባታችሁ በመታዘዝ ነው። በልባችሁ ውስጥ በደረሰባችሁ ስብራትና ምህረትን ካለማድረግ የመጣን እስራትና ጭቆና ነፃ እንድትሆኑ ስለሚፈልግ ነው።

2. በአንተ ላይ የተፈፀመውን ወንጀል እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ መድገም አያስፈልግህም። ግልጽ ኃጢአት ከሆነ፣ ወንጀለኛው ዝርዝሩን ሊያውቅ ይችላል። ጥፋተኛው አንዳንድ ጊዜ ያደረሰውን ጉዳት ላያውቅ ይችላል። ይህ በወላጆች እና በልጆቻቸው መካከል ባለው ግንኙነት የተለመደ ነው። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን አጭር ያድርጉት። ይቅር ለማለት የሚያስፈልግዎትን ምክንያቶች ሁሉ ዝርዝር ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ አይደለም።

3. ሌሎችን በራሳቸውን ጥፋት ጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማቸው ለማድረግ አትሞክር ። እግዚአብሔር የጠራችሁ እንድትታዘዙ ነው እንጂ አቃቤ ህግ ጠበቃ፣ ፈራጅ ወይም ዳኛ እንድትሆኑ አይደለም። ፈውስህ የሚመጣው በመታዘዛችሁ ምክንያት ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ስህተቶቻቸውን ሊቀበል ወይም ላይቀበል ከሚችለው ሌላኛው ሰው አደለም።

4. አጭር አድርገው። በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች፣ በከፍተኛ የስሜታዊነት ደረጃ ምክንያት፣ ያልታቀዱ ነገሮችን መናገር ቀላል ነው ይህም የስብሰባውን፣ የደብዳቤውን ወይም የውይይቱን ዓላማ ሊያደናቅፍ ይችላል።

| ማስረታዊ እውነ ት |
|---|
| የ እ ግዚአ ብሔር ቃል አ ማኞች ያ ስ ቀ የ ሟቸውን ወይም የ በ ደሉዋቸውን ሰ ዎች በ ትህ ትና ይቅር እ ን ዲሉ ያ ዛ ል። |

ይቅርታ መጠየቅ ያለብህን ሰው ወይም ይቅር ልትለው የሚገባህን ሰው መንፈስ ቅዱስ ከገለጠልህ አሁኑኑ በግልጽ ጠይቅ እና የምትገናኝበትን ቀን ጥቀስ። ይቅርታና እርቅን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ለመታዘዝ ባለው ቁርጠኝነት እንድትጸና ኃላፊነት የሚሰማህ ሁን ።

ለእናንተ በታዛዥነት ለእግዚአብሔር ትእዛዞች በይቅርታና በእርቅ ምላሽ ለምትሰጡ፣ የይቅርታ ወይም የይቅርታን የመፈለግ ተግባር የአዲስ ነገር መጀመሪያ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። እኛ ኮምፒውተሮች አይደለንም። ለአእምሮአችንና ለባህሪያችን "ማደስ" ቁልፍ ወይም "ኮንትሮል-አልት-ዴሊት" የለም። መታዘዝህን ጠብቆ ማቆየት ራስን መግዛትን፣ ዲሲፕሊንን እና ትህትና በተሞላበት በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ መታመንን ይጠይቃል፣ ይህም በልብህ ውስጥ ያለው ለውጥ እንዲቀጥል ነው።

## ይቅር ለተባሉት።

እግዚአብሔር እና የበደልናቸው ሰዎች ፊት ውድቀትዎን ለመቀበል በቂ ትሁትነትን ማሳየት በሕይወትዎ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሚሰራ የሚያሳይ ውብ ምስክርነት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በእርስዎ ላይ ሥራውን ገና አልጨረሰም። **ጥፋትህን ለመድገም እና ሌሎችን ለመጉዳት መነሳሳት ሊሰማህ ይችላል። ትግላችሁ የሚጀምረው ከዚያ ነው።**

## ለይቅርታ ሰጪዎች

**ምሬትህን እና ቂምህን በመተው የእግዚአብሔርን ልብ ማንፀባረቅ፣ የበደሉህን ይቅር ማለት ለሰማዩ አባት ዝናና እና ክብርን ያመጣል። እግዚአብሔር ግን አሁንም ባንተ ላይ አላበቃም ። አጥፊዎ ያስከተለውን ስብራት ለማስታወስ ትፈተናላችሁ። ቂም እንደገና በልባችሁ ውስጥ ሥር ለመስደድ ይሞክራል። ትግላችሁ የሚጀምረው ከዚያ ነው።**

**የጎዳሃቸው ሰዎች ወይም የጎዱህ ሰዎች የህይወትህ አካል ሆነው ሊቀጥሉ ይችላሉ። እና ምንም እንኳን እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ ትልቅ ድል ቢኖረውም፣ይህ ማለት ግን ተለውጠዋል ማለት አይደለም። በአንተ ላይ ጥላቻ ና ቂም መቋጠራቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ፣ ወይም ደግሞ አንተን መጉዳት ሊቀጥሉ ይችላሉ። ሥጋህ እንደለመደው በትዕቢትና ራስ ወዳድነት የተሞላበትን ምላሽ ሊሰጥ ይፈልግ ይሆናል።**

**ነገር ግን በኤፌሶን 4:22-24 መሰረት በቀድሞ ማንነታችን ላይ ምን ማድረግ አለብን?**

____________________________________________________________________________

___________________________________

እንደ ቀድሞው ሁኔታ ለሰዎች መልስ መስጠት አቁም እና እግዚአብሔር ወደሚሆን የሚቀይርልህን አዲስ ሰው በኃይል "ልበስ"።ያለማቋረጥ ለእርሱ እየተገዛህ ከቆየህ፣ በሕይወትህ ውስጥ እግዚአብሔር ፍሬውን ለማምረት እርሱ ታማኝ ይሆናል። አስታውስ፣ የአንተ ታዛዥነት ሌላው ሰው እንዲቀየር አይደለም። የአንተ ታዛዥነት እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ የሚሠራውን ለውጥ ምላሽ ነው።

**ፊልጵስዩስ 1:6 ጻፍ።**

____________________________________________________________________________

___________________________________

____________________________________________________________________________

___________________________________

**እኔ ይቅር የምለው ሰው ለግንኙነታችን መታረቅ ካልፈለገስ? ሮሜ 12:18 ሰላምን በመጠበቅ ረገድ ስላለህ ድርሻ ምን ይላል?**

____________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________

**አንተ ስለእርቁ ባንተ በኩል ያለውን ብቻ ነው ተጠያቂነት ያለብህ።** በሌላው ሰው ላይ ማንኛውንም የሆነ ግምት ወይም መስፈርት ልታስቀምጥ አትችልም።አቋማቸው ምንም ይሁን ምን፣ እግዚአብሄርን በማክበር ምህረት ለመጠየቅ እና ምህረት ለመስጠት **መታዘዝ አለብህ ።** ሌላው ሰው ይቅርታ ሊሰጥህ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በአንተ ላይ የፈጸሙትን በደላቸውን ካልተቀበሉ፣ እግዚአብሔር አሁንም ስለታዛዥነትህ ይባርክሃል እና ሰላሙን፣ ጸጋውን እና ምህረቱን በህይወቶ ላይ ያፈስሳል። የሌላው ሰው ምላሽ ምንም ይሁን ምን አንተ የእግዚአብሄርን ከባርነትህ ነፃ ያወጣህን ነፃነት ትለማመዳለህ።

**ይህንን ጸሎት እንደ መመሪያ ተጠቀምበት፡-**

> *ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አንተን የማምንበት ጥንካሬ እንድትሰጠኝ እጸልያለሁ። ይህን የማደርግልህ ለአንተ መሆኑን እንዳስታውስ እርዳኝ። በ____________________ ላይ ምንም ነገር አልፈልግም፣ ነገር ግን ሕይወቴን በእጅህ እሰጣለሁ። ከ____________________ ጋር ይበልጥ መስማማት እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን የእኔን ሚና ብቻ እንደምሰራ አውቃለሁ። አንተ እንድትከበር ____________________ እንዲታዘዝልህ እጸልያለሁ። **በውጤቶቹ ሙሉ በሙሉ እታመንሃለሁ። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ። አሜን።***

## ይቅር ለማለት የሚያስፈልገው ሰው ቢሞትስ? አሁንም ይቅር ልላቸው እችላለሁ?

በሰው ልብ ውስጥ ያለው መራራት/ጥላቻ ሁኔታውን ከፈጠረው ሰው እንኳዋን ከሞተ በኋላም ረዥም ጊዜ ይቆያል። ምሕረት ብቸኛው መድሃኒት ነው፣ እና ሁልጊዜም እርምጃ ይጠይቃል። መርሆዎቹ አንድ ናቸው። በመጀመሪያ ስላለፈው/ሞተው ሰው ያለዎትን መራራት/ጥላቻ ለጌታ ይናዘዙ። **ከዛ ስህተታቸውን ወይም ጥፋታቸውን እንዲሁም በእነሱ ላይ ቂም እንደማትይዝ ለጌታ ንገረው፣ እና በምትኩ፣ ይቅርታን ስጣቸው።** በታመነ ጓደኛ ወይም ፓስተር ፊት ይቅርታዎን ጮክ ብለው እንዲናገሩ አበረታታለሁ።

**እርስዎን ለመምራት የሚከተለውን ጸሎት ይጠቀሙ፡-**

> *ጌታ ኢየሱስ ሆይ በመስቀል ላይ ስለሞትክ እና ስለ ኃጢአቶቼ ሁሉ ይቅር ስላልክኝ አመሰግንሃለሁ። ይህን ሰው ላደረሰብኝ ጉዳት የግድ ይቅር ማለት እንዳለብኝ በቃልህ ተስማምቻለሁ። እነዚህን የይቅርታ ቃላት ለመታዘዝ እና ለመናገር ጥንካሬን እጠይቅሃለሁ። ____________________ ን ለ ____________________በደሉ ይቅር እላለሁ። ምሬቴን እንድታስወግድልኝ እጠይቅሃለሁ። ይህን ምሬት ለረጅም ጊዜ ስለያዝኩት ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ አሜን ።*

**አንድ የመጨረሻ ሀሳብ**

በመጨረሻ ጌታን ታዝዤ እና አባቴን ይቅር ብያለው፣ እና በልቤ የያዝኩትን ምሬት እና ጥላቻ ለእግዚአብሔር ስሰጥ፣ ከዚያ ወዲያው ነፃነት እና በረከት ተከተለኝ ። እግዚአብሔር ለእናንተም እንዲሁ ይፈልጋል። ሌሎችን ይቅር ለማለት ወይም ከሌሎች ይቅርታ የመጠየቅ ችሎታህ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ይቅርታ ጋር ካለህ ልምድ ጋር የተያያዘ ነው። ምሕረት ለማድረግ እና ምሕረት ለመቀበል ዝግጁ መሆን በእውነት ንስሐ መግባታችን፣ የእግዚአብሔርን ምሕረት መቀበላችን፣ እና ሕይወታችንን ለእርሱ መስጠታችን ምልክት ነው። ለእግዚአብሔር የተገዛ ልብ ለሌሎች ግትር ልብ ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር ፊት ትሁት ይሁኑ፣ ስለ ምሕረት/ይቅርታ ያለውን ትእዛዝ ይታዘዙ፣ እና ከበደል እና ከቁጣ ባርነት ነፃ ይውጡ።

> ማስረታዊ እውነት
> የሌሎች ምላሽ ወይምድርጊት
> ምንምይሁን ምን ለእርሱ
> በመታዘዝ እንድንቀጥል
> የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል።

*የመጀመሪያ እና ብዙውን ጊዜ በይቅርታ የሚፈወሰው ሰው ይቅርታን የሚያደርገው ሰው ብቻ ነው . . .*
*በእውነት ምሕረት/ይቅርታ በምናደርግበት ጊዜ፣ እስረኛን ነጻ እናወጣለን፣ ከዚያም ያ ነጻ የወጣው እስረኛ እኛ እንደሆንን እናውቃለን። —ሉዊስ ስሜድስ*

***ይህ ምዕራፍ እግዚአብሔር በይቅርታና በእርቅ አማካኝነት ሊሰጥህ የሚፈልገውን ነፃነት እንድትቀበል ጠቃሚ መመሪያ እንደሆነልህ እጸልያለሁ። ቀላል አይደለም፣ ምክንያቱም በክርስቶስ ያለንን ነፃነት እንዳንለማመድ ያለማቋረጥ የሚጥር ተቃዋሚ አለን። የሚቀጥለው ምዕራፍ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ስለሚካሄደው ሃይለኛውና የማይታየው ጦርነት ላይ ያተኩራል እናም ጠላታችንን ለመዋጋትየሚያስፈልጉህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሳሪያዎች ያስታጥቅሃል።***

**ምዕራፍ 6**

***መንፈሳዊ ጦርነት***

ወንዶች ልጆቼ በልጅነታቸው ወቅት ብዙ ጊዜ የቀለም ኳስ ጫወታን እንጫወት ነበር። ፔንትቦል የሚባለው ጨዋታ መሳሪያ አርቴፊሻል ጠመንጃ ውስጥ በጣም በቀለም የተሞሉ ፕላስቲክ ኳሶችን/ጥይቶችን የሚይዝና በመተኮስ ተጫዋቾችን በማሸነፍ የምጫወተው ጨዋታ ነው። ከተመቱ ይወጣሉ ። ተጫዋቾቹን ለማሸነፍ ብዙ የጦር ስልቶችን መጠቀም ይቻላል። ከምርጦቹ ስልቶች አንዱ በስውር ከጀርባቸው በድንገት መከሰትና መምታት ነው። የሚመታው ሰው ትክክለኛ መከላከያ ካልለበሱ ሊያቆስላቸው ወይም ሊያሳብጣችው ይችላል። ከነቲራ ብቻ ለብሰው የነበሩ ሰዎች በሚቀጥለው ጨዋታ ብዙ ተጨማሪ መከላከያ ይዘው/ለብሰው ይገኛሉ ። ነገር ግን አደጋው ከትንሽ እብጠት በላይ ከሆነስ? ለጦርነቱ እንዴት ይዘጋጁ ነበር?

የምንኖረው በአካላዊ ዓለም ውስጥ ሲሆን በግዑዙ ዓለም ውስጥ በቀላሉ ተጠምደን እንኖራለን። የታሪክ መጽሐፎች የተለያዩ አገሮች በተለያዩ ምክንያቶች ከጠላቶቻቸው ጋር እንደሚዋጉ ይነግረናል። በግሌ ደግሞ፣ ጠላቶቻችንን እንደ ሌሎች አካላዊ ፍጡራን እናያቸዋለን፣ እነሱም በቃላትና በተግባራቸው በተለያየ ደረጃ ጉዳትና ጥፋት ያስከትሉብናል።አውራ ጎዳና ላይ ያለው መናኛ ሹፌር፣ ወሬና ውሸት የሚያናፍሰው፣ አጭበርባሪው፣ ሌባው፣ ደፋሪው፣ ነፍሰ ገዳይ የሆኑ ሰዎች ሁላ የምናያቸውና የምንዳስሳቸው አካላዊ ጠላቶች ናቸው። ነገር ግን በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ የማይታይ ጠላት አለ፣ ከምታየው፣ ከምትነካው ወይም ከሚሰማህ ከማንኛውም ነገር የበለጠ አደገኛ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እንድትዘጋጅ ይፈልጋል።

## ትምህርት 1 - የማይታየው ጠላት

ኤፌሶን 6፡12 በየቀኑ የምንታገልባቸውን በጣም አደገኛ ዛቻዎች ይገልጻል። እነማን ናቸው?

____________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________
____________________________________________________________

የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛ ጠላቶቻችን አካላዊ ሳይሆኑ መንፈሳዊ እንደሆኑ ያስተምረናል። ያስተውሉት ወይም አያስተውሉት፣ እርስዎ በዙሪያዎ በሚካሄደው መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ነዎት። እንደ አለመታደል፣ ከዚህ ጦርነት ለመውጣት የሚያስችል ምርጫ የለዎትም። ጦርነቶቹ የእርስዎን ፈቃደኛ ተሳትፎ አይጠብቅም ። እርስዎ ሁልጊዜ በጦርነቱ የውጊያ ፊት ለፊት መስመር /ረድፍ ላይ ነህ። ሁለት አማራጭ አለ አንድ በቃሉ ብርሃን ውስጥ ቆመህ ለእግዚአብሔር ታዘህ የጠላትን ጥቃት መዋጋት ወይም ለጨለማ ተገዝተህ ሽንፈትህ የሚያመጡትን ችግሮች/ህመሞች/መጥፎ ውጤቶች ልትለማመድ /ልታይ ትችላለህ።

ይህ ለእርስዎ ከመጠን በላይ ድራማ ሊመስሉት ይችላል ? ከሆነ ይገባኛል። በጨለማ ወጥመድ ውስጥ ለማሰር እና ልባችሁ እግዚአብሔር ላይ እንዲያምፅ ከሚዋጋ መንፈሳዊ ጠላት ጋር የሚደረግ የማይታይ ጦርነት "ሌላ ዓለም ውስጥ ያለ ጦርነት" ይመስላል። ነገር ግን ይህ ጦርነት በማመንዎ ወይም ባለማመንዎ ላይ የተመሰረተ አይደለም። እንደውም ጠላት ስለ እርሱ መገኘት ሳታውቅ ብትቀር ይመርጣል። ለእርሱ በጣም ቀላሉ ታዳኝ አዳኝ የለም ብሎ የሚያምነው ሰው ነው። ግን ማየት የማትችለውን ጠላት እንዴት ነው የምትዋጋው?

ለቀን ተቀን ጦርነቶችህ ለመዘጋጀት የመጀመሪያው እርምጃ ከማን እና ከምን ጋር እየተዋጋህ እንደሆነ በደንብ መረዳት ነው።

**የሰይጣን አመጣጥ**

ብዙ ሰዎች ዲያብሎስ ሁሉንም ክፉ ነገር እንደሚወክል ይገነዘባሉ። እሱ ብዙ ጊዜ በቀልድ መልክ በትከሻዎ ላይ እንዳለ ትንሽ ቀይ ቀንዳምናመንሻ የያዘ እንዲሁም አንድን ሰው መጥፎ ነገር እንዲያደርግ የሚያሳምን አርገው ይስላሉ ። እውነታው ግን ከዚያ በላይ በጣም ተንኮለኛና አደገኛ ነው።

ግን ከየት ነው የመጣው? ቆላስይስ 1:16 እና ነህምያ 9:6ን ጠቅለል አድርገህ ፃፍ ።

ዘፍጥረት 1:31ን አንብብ። እግዚአብሔር ስለ ፍጥረቱ ምን አለ?

እግዚአብሔር ያልፈጠረው በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ያለ ምንም ነገር የለም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ መልካም አድርጎ እንደሚቆጥረው ያስተምራል። ይህ ማለት ሰይጣን እንኳን በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው፣ እና በመጀመሪያ የተፈጠረው መልካም እንዲሆን ነበር። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ካሉት የሰማይ መላእክት ሠራዊት አንዱ ነበር። ታዲያ ምን ተፈጠረ? ይሁዳ 1:6 እና 2 ጴጥሮስ 2:4ን አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ስለ መላእክት ምን ይላሉ?

1ኛ ጢሞቴዎስ 3:1-7 በቤተክርስቲያን ውስጥ ኤጵስ ቆፖስ ለመሆን በሚፈልግ ሰው ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ባህሪ ይናገራል። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:6 ላይ ምን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል?

በመጀመሪያ ጥሩ የነበረው ዲያብሎስ በትዕቢቱ የተወገዘ ሆነ። ሰይጣን መልአክ በነበረበት ጊዜ እንደ እግዚአብሔር መሆን፣ ከሥልጣኑም እኩል ወይም ታላቅ ለመሆን እና ንጉሥ ሆኖ እንዲመለክ ይፈልግ እንደነበር ይታመናል። በዘፍጥረት 3:5 ላይ "እንደ አምላክ ትሆኛለሽ" በማለት ሔዋንን በኤደን ገነት ሲፈትን ተመሳሳይ ሐሳብ ማንሳቱ ምንም አያስደንቅም።

በማቴዎስ 4:9 ላይ ሰይጣን ለኢየሱስ የአለምን መንግስታት ሁሉ ካቀረበለት በኋላ ምን ጠየቀው?

ሰይጣን በእግዚአብሔር ልዕለ ሃያልነት ና የመመለክ ታላቅነት ቀንቷል። በእግዚአብሔር ላይ ያሳየው ኩራቱ እና አመፁ

መውደቂያው ሆነለት። ራእይ 12:7—9 እና ሉቃስ 10:18 አንብብ። አምላክ የሰይጣንን ትዕቢት እንዴት ያስተናገደው ?

ዘንዶ /ድራገን እየተባለ የሚጠራው ሰይጣን ከተከታዮቹ ሌሎች መላእክት ጋር ከሰማይ ተጣለ። ራእይ 12:3—4ን አንብብ። ከሰይጣን ጋር ምን ያህል መላእክት ተባረሩ?

የራእይ መጽሐፍ በምሳሌያዊ ና በቁጥራዊ አነጋገር የተሞላ ሲሆን ብዙ ምሁራንና የመጽሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎችና ተንታኞች ከእያንዳንዱ ጥቅስ በስተጀርባ ያለውን ትርጉም ለማጥናት ስፍር ቁጥር የሌለውን ሰዓታትን አሳልፈዋል። "ዘንዶው" የተባለው ሰይጣን ከመላእክቱ አንድ ሦስተኛውን "ከዋክብትን" ከእርሱ ጋር ወደ ምድር እንደወሰደ ይታመናል። እነዚህ የወደቁ መላእክት ክፉ ሥራውን የሚሠሩ የሰይጣን አጋንንት በመባል ይታወቃሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን የተጣለበትን ጊዜ አይገልጽም። የሚመስለው ግን ፍጥረታት ሲፈጠሩ በነበረ በመጨረሻው ቀንና በሔዋን ፊት እንደ እባብ በተገለጠ ጊዜ መካከል የሆነ ነው።

**ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች የሰይጣን ውድቀት በኢሳይያስ** 14፡12—17 **እና በሕዝቅኤል** 28፡12—19 **ተመዝግቧል ብለው ያምናሉ**። የኢሳይያስ ጥቅስ በተለይ ለባቢሎን ንጉሥ የተሰጠ ትንቢታዊ ቃል ነው፣ የሕዝቅኤል ጥቅስ ደግሞ ለጢሮስ ንጉሥ የተሰጠ **የልቅሶ ሐዘን** ነው። ሰይጣን የእነዚህ ጥቅሶች ዋና ርዕሰ ጉዳይ መሆኑን በትክክል ለማወቅ ባንቻልም፣ ለእነዚህ ሁለት ነገሥታት የተሰጡት ቃላት እና ሰይጣን የወደቀበት መንገድ መካከል ግልጽ የሆነ መመሳስል አለ።በምናውቀው መሰረት፣ ሰይጣን ምናልባት እነዚህን ነገሥታት በእነዚህ ጥቅሶች ወቅት ሊያስገድድ ወይም በውስጣቸው ሊኖር ይችላል፣ ልክ እንደ ሉቃስ 22:3 ከየሱስን ከመገደል በፊት በይሁዳ እስካርዮት ውስጥ እንደነበረው ሁኔታ። በመጨረሻም፣ **በሰው ልጅ የኃጢአት ምክንያት የመጣው እርግማን ሰይጣን በዚህች ምድር ላይ ጉዳት እንዲያመጣ መሰረት ሰጥቶታል**።

## ትምህርት 2 የዚህ ዘመን አምላክ

**በሚቀጥሉት ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ ሰይጣን የተገለጸው እንዴት ነው?**

ዮሐንስ 14:30; 16:11

______________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________

______________________________

2ኛ ቆሮንቶስ 4:4

______________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________

______________________________

ኤፌሶን 2:2

______________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________

______________________________

**ማወቅ ያለብህ ነገር ሰይጣን ዓለምንና ነዋሪዎቹን በፈጣሪ ላይ እንዲያምፁ በብልጠት ተጽዕኖ የሚያሳድር አደገኛ ጠላት መሆኑን ነው። እግዚአብሔር መጀመሪያ የፈጠረውን መልካም ነገር ሁሉ ሊያበላሽ ይፈልጋል። በ1ኛ ጴጥሮስ 5:8 ላይ የተገለጸው እንዴት ነው?**

> ***ሰይጣን***- *የሰው ልጅ ታላቅ ጠላት; የጨለማው አለቃ ዲያብሎስ።*
>
> ***ዲያብሎስ***- *የእግዚአብሔር ተቃዋሚ፤ እርሱ ሥልጣን ሥር ቢሆንም በእርሱ ፈቃድ ብቻ የሚሠራ፤ የክፋትና የጽድቅ-አልባነት የበላይ መንፈስ፤ ፈታኝ።*

__________________________________________________

______

__________________________________________________

______________________________________

**ሰይጣንና አጋንንቱ የሚውጡትን ታዳኞች በመፈለግ ስራዮ ብለው በምድር ዙሪያ ይዞራሉ። በ2 ጢሞቴዎስ 2:25—26 መሠረት አምላክን በመቃወም የሚኖሩ ሰዎች ሁኔታ ምን ይመስላል?**

______________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________
____________________________

_________________________________________________________

በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑት ከጠላቶች ምንም መከላከያ የላቸውም። የሰው ልጅ ከእሱ ጋር አይመጣጠኑም። እሱ የበለጠ ጠንካራ እና ጥበበኛ ነው እናም ከክርስቶስ ውጭ በራሳቸው ኃይል የሚታመኑትን ማንኛውንም ሰዎች ማሸነፍ ይችላል።

**የማይቀር ሽንፈት**

ሰይጣን የእግዚአብሔር እና የእግዚአብሔር ልጆች ጠላት ነው፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ተገዳዳሪ አለመሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው።. እሱ ኃይለኛ ነው፣ነገር ግን ሁሉም ኃይል የለውም.። እሱ ተንኮለኛ ነው፣ግን ጥበብ ሁሉ የለውም፣ ጅምላ ጥፋትን ማጥፋት ይችላል፤ እርሱ ራሱ ግን ይጠፋል።

በዘፍጥረት 3:15 ላይ እግዚአብሔር ለእባቡ ምን አለው?

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

ዕብራውያን 2:14ን አንብብ። ኢየሱስ ሰይጣንን ያሸነፈው እንዴት ነው?

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

በማቴዎስ 25:41 እና ራእይ 20:10 መሠረት የሰይጣን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ምንድን ነው ?

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

ሰይጣንና አጋንንቱ የሚዋጉት ቀደም ሲል በተሸነፉት ጦርነት ነው፣ እና እውነታውን በጥሞና ያውቁታል። የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በሰይጣን ኃይል ላይ የመጨረሻውን ጥፋት አስከትሏል፤ ይህም የሴቲቱ "ዘር" የሰይጣንን ራስ ይቀጠቅጣል የሚለው የአምላክ ትንቢታዊ ቃል መፈጸሙ ነው።

ማቴዎስ 28:18ን አንብብ፡፡ ሁሉም ስልጣን ያለው ማነው?

________________________________________________________________________________
________________________

ማቴዎስ 8:28-32 በኢየሱስ እና አጋንንት ያደረባቸው ሁለት ሰዎች መካከል የሆነው ሁኔታ ይዘግባል፡፡ ኢየሱስ ሲመጣ አጋንንቱ ምን አሉት?

________________________________________________________________________________
________________________

________________________________________________________________________________
________________________

________________________________________________________________________________
________________________

አጋንንቱ ኢየሱስን ማን እንደ ሆነ በትክክል አውቀው ፈሩት፡፡ በአቅራቢያው ወደሚገኘው የአሳማ መንጋ ውስጥ ለመግባት የእርሱን ፍቃድ መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ ኢየሱስ በቁጥር 32 ላይ ምን መለሳላቸው?

________________________________________________________________________________
________________________

ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ቃል አጋንንትን ከያዙአቸው ሰዎች አስወጣቸው፡፡ ማርቆስ 1:23—27 አንብብ፡፡ በቁጥር 27 ላይ ምስክሮቹ ስለ ኢየሱስ ምን ተመልክተዋል?

________________________________________________________________________________
________________________

________________________________________________________________________________
________________________

________________________________________________________________________________
___________ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሁሉም ሥልጣን አለው፣ እናም አንድ ቀን በቅርቡ ተመልሶ ሰይጣንንና አጋንንቱን ለዘላለም በስቃይ ውስጥ እንዲኖሩ ወደ ሲኦል ሊልክ ይመጣል፡፡ እስከዚያ ቀን ድረስ ግን የጠላትን ጥቃት ለመዋጋት 'ንቁ ና ጠንቃቃ' እንድንሆን የጴጥሮስን ማሳሰቢያ መከተል አለብን፡፡

## ትምህርት 3–የዲያብሎስ ተንኮል

የሰይጣን መጨረሻ እየተቃረበ ቢሆንም እስካሁን አልደረሰም። ምን ያህል ጊዜ አለው? ማቴዎስ 24:36ን አንብብ። መጨረሻው መቼ እንደሚሆን ማን ያውቃል?

______________________________________________________________________________

______________________________

ሰይጣን ምን ያህል ጊዜ እንደቀረው አያውቅም፤ ስለዚህም ከመጥፋቱ በፊት ሳይደክምና ሳይታክት በብዙ ሰዎች ልብ እና አዕምሮ ውስጥ የአመፅ ዘርን ይዘራል።

**የጠፋትን ማሳወር**

የሰይጣን ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

2ኛ ቆሮንቶስ 4:4

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

ማቴዎስ 13:19

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

2ኛ ቆሮንቶስ 2:11

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

__

2 ጢሞቴዎስ 2:26

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

ሰይጣን ከሁሉ አስቀድሞ የሰውን ልጅ አዕእምሮ ከወንጌል እውነት ለመሰወር የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። እንደ አለመታደል ሆኖ፣እውነትን ለማታለል/ለማጭበርበር ብዙ የሚመርጣቸው ና የሚተካቸው ውሸቶች አሉ። ኢየሱስ በማቴዎስ 7፡13-14 ስለ ሕይወትና ስለ ጥፋት መንገድ ምን አለ?

የሕይወት መንገድ አንድ ብቻ ነው እርሱም በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሌሎች ነገሮች ሁሉ ትርጉም የለሽ ናቸው መጨረሻቸውም ሞት ነው። ሰይጣን ይህን እውነታ ጠንቅቆ ያውቃል። የሰው ዘርን ሁሉ ነፍሰ ገዳዮች እና አስገድዶ ደፋሪዎች በማረግ ህይወታችውን ለራሱ ማረግ ተፅዕኖ ማሳደር አይጠበቅበትም ምንም እንኳን አንዳንዶች እነዚያን መንገዶች እንዲከተሉ ቢያበረታታም ። ውዳሴያቸውንና አምልኮአቸውን ቢቀበልም ትእዛዙን ለማስፈጸም የሰይጣን ሠራዊት አያስፈልገውም። እሱ የሚፈልገው የሰውን ልጅ ልብ እና አዕእምሮ ከወንጌል መልእክት ማሳወር ብቻ ነው የሚያስፈልገዋል። ሌላው ነገር ሁሉ ለእርሱ በቂ ነው። ግን ሴጣን የሰውን ልጅ ከእውነቱ ማራቅ/መሰወር የሚችለው እንዴት ነው? 2ኛ ቆሮንቶስ 11:14 ጻፍ።

በዚህ ምክንያት ነው ሰይጣን በትክክል በጣም አደገኛ ና የዓለምን መንገዶች ለመምሰል የቻለው ።ክፋቱን እንደ “መልካም” በመለወጥ የተዋጣለት ነው።የኢየሱስን ጽድቅና ሥልጣን የማይቀበሉ ሰዎች ለእሱ ተንኮል ሙሉ በሙሉ የተጋለጡ ናቸው።

እሱን ለመግለጽ በዘፍጥረት 3፡1 ምን ቃል ተፅፎአል?

በኤፌሶን 6:11 መሠረት ምን መቃወም አለብን?

***ብልሀ***- *ሌሎችን የማታለል ችሎታ ያለው፥ ብልሃተኛ; ተንኮለኛ.*

***ተንኮለኛ***- *በብልሃት አታላይ; ንቁ ; የማሰብ ችሎታ ያለው፡*

***ሚሃግብሮች***- *እቅዶችን ወይምንድፎችን ማዘጋጀት; በብልሃት በማሰብ ለማከናወን.*

***ተንኮል***-*ለማጥመድ ወይም ለማታለል የታሰበ ሥልት*

*ወይምዘዴ*

______________________________________________

በ2 ቆሮንቶስ 11:3 መሠረት ሰይጣን የሚዋሸውና የሚያሴረው ለምንድን ነው?

______________________________________________

________________________________________________________________

_________________________

________________________________________________________________

_________________________

ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥ ነው፣ እናም በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ መዳንን እና የዘላለም ሕይወትን ይሰጣል። ሰይጣን የቻለውን ያህል ብዙ ሰዎችን ከዚህ ቀላል እውነት ለማሳወር ይጥራል።እናም ይህን ዓለም በአጀንዳው ውስጥ እንዲካተት በብልሃት ተቆጣጥሯል።

**ትምህርት 4–የዚህች ዓለም መንገዶች**

በ1ኛ ዮሐንስ 5፡19 መሠረት የዓለም ሁኔታ ምን ይመስላል?

ዮሐንስ 15፡18-21 ዓለም ስለ ክርስቲያኖች ስላለው አመለካከት ምን ይላል?

"የዚህ ዘመን አምላክ" በሁሉም የዚህ ዓለም ስርዓቶች ውስጥ ሰርጎ ገብቷል። ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ትምህርት፣ ፋሽን፣ መዝናኛ እና ዓለማዊ ፍልስፍና ሁሉም በእሱ ክፉ ተጽዕኖ ሥር ናቸው። እንዲያውም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን እና ሌሎች የሃይማኖት ተቋማትንም በተሳካ ሁኔታ ያንቀሳቅሳል። በዚህም ይህ ዓለም በጨለማ የተሞላ መሆኑ ምንም አያስደንቅም።

በዮሐንስ 3፡19-20 ላይ ኢየሱስ ስለሰው ልጆች ተግባር ምን አለ?

በቆላስይስ 2፡8 ላይ ምን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል? ይህ ጥቅስ ለእርስዎ በግልዎ እንዴት ይሠራል?

የዚህ ዓለም መንገዶች ብዙ ሰዎችን እንደሚማርኩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቃል። በማርቆስ 4፡ 1-20 ያለውን የዘሪውን ምሳሌ አንብብ። በቁጥር 18-19 እንደተገለፀው በ"እሾህ" መካከል የተዘሩት ዘሮች ትርጉም ምንድን ነው?

የምንኖረው በዚህች ምድር ላይ በብዙ “እሾህ” መካከል ነው። ሰይጣን የሰውን ነፍስ መያዝ ካልቻለ፣ የዚህን ዓለም ጥቃቅን ነገሮችን በመጠቀም ከአምላክ መንግሥት በማዘናጋት ስሜታቸውን ለማግኘት ይጥራል። እርስዎን የሚያዘናጉ የዚህ ዓለም ጥቃቅን ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

1 ዮሐንስ 2፡15—17ን አንብብና ይህ ዓለም የሚያቀርባቸውን ሦስቱን ነገሮች ዘርዝር።

1. ______

2. ______

3. ______

### *የሥጋ ምኞት*

በሥጋ ተፈጥረናል በአሁኑ ጊዜ የምንኖረው በሥጋ ነው። ሥጋችን ተፈጥሯዊ የሆነ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምኞቶች አለው። ምግብ እንራባለን፣ መጠጥን እንጠማለን፣ ጓደኝነትን እንናፍቃለን፣ የፆታ ግንኙነትን እንመኛለን፣ በተለያዩ መዝናኛዎችም ደስተኞች ነን። አምላክ የሰጠን ሥጋዊ ምኞቶች በራሳቸው ኃጢአት አይደሉም፣ደግሞም እግዚአብሔር የፈጠራቸው ናቸው። ነገር ግን የእነዚህ ምኞቶች ፍጻሜ ኃጢአት የሚሆነው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ እነርሱን ለማርካት ስንፈልግ ነው።

> ማኅረታዊ እውነት
> ሥጋዊ ምኞት ማለት ከኃጢአት እርካታን ሚፈለግ ማለት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ 5፡19-21 በሥጋ ምኞት የታሰሩትን በማስረጃ ይዘረዝራል። ከዚህ በታች ዘርዝራቸው። ከእነዚህ ነገሮች መካከል በህይወቶ ውስጥ የተገለፁ አሉን ?

"ሰይጣን አደረገኝ" ወይም "እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ፈጠረኝ" የሚለውን ሐረግ እንደሰማህ እርግጠኛ ነኝ። ከኃጢአተኛ ምኞታችን ወይም ድርጊታችን ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ነገር

ከራሳችን ሌላ በማንም ላይ መውቀስ የሰው ተፈጥሮ ነው፡፡ ነገር ግን እንደ ያዕቆብ 1:13-14፣ ለኃጢአት የመፈተናችን እውነተኛ ምንጭ ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ማርቆስ 7:21—23 አንብብ፡፡ ከልባችን ውስጥ የሚወጣው ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

የኃጢአተኛ ምኞቶችህ ከውስጥህ ነው የሚመጡት፣ ሌላ የምታላክክበት ሰው የለም፡፡ ተቃዋሚው፣ ዲያብሎስ ልክ በኤደን ገነት ውስጥ ለሔዋን እንዳደረገው፣ ከአምላክ ፈቃድ ውጭ ምኞቶችህን እንድትፈጽም ድክመቶችህን ይጠቀማል፡፡ ዘፍጥረት 3፡6ን አንብብ፡፡ ሔዋን ስለተከለከለው ፍሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ምን አስተዋለች?

________________________________________

---

________________________________________

________________________________________

ሰይጣን ሔዋን ፍሬውን እንድትበላ ፍላጎት አላሳደረባትም፡፡ ፍላጎቷ የመጣው ከራሷ ልብ ነው፣ ወይም ይልቁኑ፣ በአጭሩ  በጊዜው ሆዷ ነው፡፡ የሔዋንን ሆድ በረሃብ ሲያጉረመርም እንደሰማህ መገመት ትችላለህ፡፡ *ሥጋዋ* ምግብ ፈልጎ ነበር፣ እና ሰይጣን ረሃቧን በተከለከለው ፍሬ እንድታረካ/እንድታስታግስ ብቻ ሀሳብ አቀረበ፡፡ ሔዋን እግዚአብሔር በልግስና ከሰጣቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ የምግብ አማራጮች  ነበሯት፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲርቁ የተናገረውን ፍሬ ፈለገች፡፡

**ትምህርት 5-የዓይኖች ምኞት**

በዘፍጥረት 3፡6 ላይ ስለተከለከለው ፍሬ ሔዋን ያስተዋለችው ሁለተኛው ነገር ምንድን ነው?

የተከለከለው ፍሬ የሔዋንን ረሃብ ሚሟላት መቻሉ ብቻ ሳይሆን አስደናቂ ጣዕም ያለውም ይመስላል፡፡ ምናልባት ሔዋን ከበላችው ከማንኛውም ነገር የተሻለ ጣዕም ይኖረዋል ብላ ገምታ ይሆናል፡፡ ምን "የተከለከለ ፍሬ" ለእርስዎ ጥሩ ይመስልዎታል ?

ንጉሥ ዳዊትም ለዓይኑ ምኞት ሰለባ ሆነ፡፡ 2 ሳሙኤል 11፡2—4ን አንብብ፡፡ ምን አደረገ?

ዛሬ ከየትኛውም የታሪክ ጊዜ ይልቅ ከ "ጣሪያቸው" ቁልቁል የሚመለከቱ ሰዎች በዝተዋል ብዬ እከራከራለሁ(ነገሮችን ከላይ ሆኖ ማየት)፡፡ የኢንተርኔት መፈጠር እና የኮምፒዩተር እና የሞባይል መሳሪያዎች የቴክኖሎጂ እድገቶች ከብዙ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ልማት ጋር የአይን ምኞቶች የበለጠ ተደራሽ ፣ ማራኪ እና የበለጠ ሱስ የሚያስይዝ ሆኖ አያውቅም፡፡ ዓለም የሚያቀርበው ማንኛውም ነገር በማንኛውም ጊዜ ከእጅዎ መዳፍ ላይ ሊታይ ይችላል፡፡ አጋንንቱ “ተመልከቱ” የሚለውን ቃል ብቻ በጆሮ ሹክ ማለት ብቻ ነው የሚያስፈልገው ፡፡

ዘጸአት 20፡17 ጻፍ፡፡

ዳዊት ውብ የሆነችን ሴት አይቶ ከእርስዋ ጋር የፆታ ግንኙነት ለማድረግ ተመኘ፣ የንጉስነት ሥልጣኑን አላግባብ በመጠቀም የእሱ ያልሆነውን ወሰደ፡፡ የዳዊትን

*__ምኞት/መጎምጀት__- የሌላውን ንብረት ለማግዝ ሚፈለግ; በፍትወት ስሜት መመኘት; የሌላውን የሆነ ነገር ከማከን በላይ መመኘት፡፡*

ኃጢአት ማወቅ ቀላል ነው ምክንያቱም ይህ ታሪክ አንድ ሰው የብልግና ሥዕሎችን/ቪዲዎችን ሲመለከት ወይም የሱ/የሷ ያልሆነውን ወንድ ወይም ሴት ለፆታ ግንኙነት በሚፈልግ ጊዜ ራሱን ሀጥያት ይደግመዋልና ነው ።
ኢየሱስ በማቴዎስ 5፡28 ላይ ስለ ወሲባዊ ምኞት ምን ብሏል?

___

___

___

የጾታ ብልግናሁልጊዜ በዓይን ፍላጎት የተነሳ የሚመጣ ነው፣ ይሁን እንጂ ዓይናችን ሊመኛቸው ከሚችላቸው ከዚህ ዓለም ነገሮች መካከል አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው?

ኢየሱስ በማቴዎስ 6፡22-23 ላይ ስለ ዓይኖቻችን ምን ይላል?

___

___

**የህይወት ትዕቢት**

በዘፍጥረት 3፡6 ላይ ሔዋን ስለተከለከለው ፍሬ ያስተዋለችው ሦስተኛው ነገር ምንድን ነው?

___

___

___

ሰይጣን ሔዋንን ከእርሱ ፈቃድ ውጭ የእግዚአብሔርን እውቀት እንደምትቀበልና እንደ እርሱ እንደምትሆን አሳመናት። እዚያም የሰው ልጅ ዋናው ነገር አለ፡ የሕይወት ትዕቢት። ትዕቢት የሁሉም ኃጢአት ሥር ነው—ከእግዚአብሔር የበላይነት ላይ የሚደረግ የዓመፅ ምንጭ። ትዕቢት ከሁሉም በላይ ራስን ከፍ ከፍ ለማድረግ ይፈልጋል እናም ራስን እንደ የመጨረሻው ሥልጣን አድርጎ ይናገራል። ሮሜ 1፡20-25 የሕይወት ትዕቢት ሰለባ የሆኑትን ይገልጻል። እንዴት ተገለጹ?

___

________________________________________

በአጭሩ፣ አለም እግዚአብሄርን አላስፈላጊ እንደሆነ ያስተምራል፣ ስልጣኑ ሕልውናእንደሌለው ፣ አንተ የጽንፈ ዓለም ማእከል እንደሆንክ ያስተምራል። እንግዲህ ሕይወት የፈለግከው ሁሉ ማረግና መሆን ነው። ጥሩ የሆነውን ትወስናለህ ። እውነት የሆነውን ትወስናለህ ። ሰውነትህ የራስህ ነው ፤ የሥጋ ምኞትህ ምንም ይሁን ምን እንዲያረካህ ታስቦ ነው ስለዚህም ነው የዚህ ዓለም ነገሮች ማራኪ የሆኑት ነው የሚሉት ። ሐቀኛ ከሆንክ ሥጋህ ይህን መልእክት ማመን እንደሚፈልግ ታምናለህ ። እንዲሁም ሆን ብለህ  በፈቃደኝነት ኃጢአት በፈጸምኩ ቁጥር ይህን መልእክት ለማመን ትመርጣለህ።

በተጨማሪም የሕይወት ትዕቢት በተፈጥሮ ኃጢአት በማይሆኑ ነገሮችም ሊሸሸግ ይችላል ። ሰዎች ሊኮሩባቸው የሚችሉ ዓለማዊ ስኬቶችን የሚያሳዩ አንዳንድ ምሳሌዎች ጥቀስ ?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

1 ጢሞቴዎስ 6:10 ስለ ሀብት ምን ይላል?

________________________________________

________________________________________

ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት በጣም በስህተት ከተተረጎሙት ጥቅሶች አንዱ ነው። “ገንዘብ የክፋት ሁሉ ሥር ነው” የሚለውን ሰምተህ ይሆናል ነገር ግን ያ ትክክል አይደለም። ገንዘብ ወደ ክፋት ሁሉ የሚመራው ከተወደደ ብቻ ነው። ዓለማዊ ስኬቶች ኃጢአት እንዳልሆኑ መረዳት አስፈላጊ ነው። በአካዳሚክ የላቀ ውጤት መመረቅ፣ የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት መሆን፣ የኖቤል የሰላም ሽልማት መቀበል፣የተሳካ ንግድ ማፍራት እና የመሳሰሉት ጥሩ ነገሮች ናቸው። ነገር ግን እነዚህ መልካም ነገሮች የመጨረሻ ግቦቻችን ከሆኑ፣ የግል ማንነት ወይም መገመቻ ምንጭ ከሆኑ፣ በማታለል ወይም በሌላ የኃጢአተኛ መንገዶች የተገኙ ከሆኑ፣የተፈለጉት ወይም ምኞት ውስጥ የገቡት ራስን ለማርካት እና ክብርን ለመጎናጸፍ ማለትም  ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ ከሆነ የሚመደቡት ክኃጢአተኛ የሕይወት ትዕቢት ምድብ ሥር ነው ።

ማስረታዊ እውነት
በክርስቶስ አማኞች እንደሚሆናችን ማጠን ሁል ጊዜ ልንጠነ ቀቅባቸውየማብ ቡሦስት አስፈሪ ጠላቶች አሉን፦ (1) የዚህ ዓለምሥርዓት፣ (2) መንፈሳዊ ያልሆነ የወደቀ ተፈጥሮአዊ ምኞታችን እና (3) ዲያብሎስ።

ለራስህ ደስታና ክብር የዓለምን ስኬቶች እየፈለግህ ነው? ወይስ እርሱ በሰጣችሁ ስጦታዎች ጥሩነትን በመለማመድ እግዚአብሔርን እያከበርክ ነው?

## ትምህርት 6 - የጠላት ጥቃቶች

ሰይጣን ከክርስቲያኖቹ ራሳቸው በላይ የሚጠላው እነሱ እሱ ከሁሉ በላይ የሚጠላውን የክርስቶስ  አምባሳደሮች በመሆናቸው ነው ። ነፍስህን ለክርስቶስ ከሰጠህ ሰይጣን መዳንህን ሊወስድብህ አይችልም። አንተ ሁሉን በሚችል አምላክ ጥበቃ ሥር ነህ እና በመሥዋዕቱ ደም ጻድቅ ሆነሃል። ነገር ግን ዲያብሎስ ሰላምን ለመንጠቅ እና የአብን ለህይወትህ ያለውን እቅዶች ለማክሸፍ የተቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ ማወቅ አለብህ። ባህሪህን ለማጥፋት ወጥመዶችን አዘጋጅቶ ለሥጋህ ምኞት ባሪያ እንድትሆን ያደርግሃል። እንደ አማኞች እነዚህን ወጥመዶች ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው ።

በዮሐንስ 8:44 ላይ ሰይጣን እንዴት ተገልጿል?

_______________________________________________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________________________________________

በማቴዎስ 4:3 ላይ ሰይጣን ምን ተብሏል?

_______________________________________________________________________________________________________________

በራዕይ 12:10 ላይ ሰይጣን ምን ይባላል?

_______________________________________________________________________________________________________________

እነዚህ ጥቅሶች ጠላት ክርስቲያኖችን የሚያጠቃባቸውን የተለያዩ መንገዶች ያሳያሉ። የእሱ መንፈሳዊ ትጥቅ ውሸቶችን፣ የኃጢአት ፈተናዎችን፣ እና ኩነኔዎችን ወይም ውንጀላዎችን ያካትታል። ከሚከተሉት ምንባቦች የሰይጣንን ስውር ጥቃቶች ግለጽ፦

ማቴዎስ 16:21-23

_______________________________________________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________________________________________

ዮሐንስ 13:2

_______________________________________________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________________________________________

የሐዋርያት *ሥራ* 5:3

በ2 ቆሮንቶስ 11፡14 ተመስርቶ ***ከበርነስ ማስታወሻዎች*** (studylight.org በ አዲስ ኪዳን ላይ የሚከተለው አስተያየት በሰይጣንን ስውር ዘዴዎች ላይ ግልፅ የሆነ ምልከታን ይሰጣል ።

> ሰይጣን በግልጽ ጦርነት አያካሂድም። ከክርስቲያን ወታደር ጋር ፊት ለፊት አይገናኝም። በድብቅ ያልፋል፣ አቀራረቦቹን በጨለማ ውስጥ ያደርገዋል፣ ከስልጣን ይልቅ ተንኮልን ይጠቀማል እና በጉልበት ከማሸነፍ ይልቅ ማታለል እና ክህደትን ይፈልጋል ። . . .ሰይጣን በግልጽ አይታይም። ወደ እኛ የሚቀርበው በአስጸያፊ መልክ ሳይሆን . . የሚያታልሉንንና ወዲያውኑ የማንቃወማቸውን ፈተናዎች በፊታችን በማኖር ነው ። እሱ ዓለምን በሚማርክ ገጽታ ያቀርባል፣ምንም ጉዳት የሌላቸው ወደሚመስሉ ተድላዎች ይጋብዘናል፣ እናም ወደ ኋላ ማፈግፈግ እስከማንችል ድረስ ወደ ማርካት ይመራናል።

ሰይጣን ካንተ የበለጠ ብልህ መሆኑን ማስታወስ አለብህ። እሱን በሀሳብ መብለጥ አትችልም ። እሱን ብቻህ ብትጋፈጠው ሁል ጊዜ ትሸነፋለህ ። ወደ አእምሮህ እና ወደ ልብህ በፈጣኑ የሚገባበትን ስስ ቦታዎች ያውቃል ስለዚህም በእነዚህ በኩል ነው በተደጋጋሚ የሚያጠቃውም ።

የሚከተሉት ቅዱሳን ጽሑፎች ስለ ልባችንና እምሯችን ምን ይላሉ?

ኤርምያስ 17፡9

ምሳሌ 4፡23

**ሰይጣን ሃሳቦቻችሁን እና ስሜቶቻችሁን በውሸት እና በፈተና ሊጠቀምበት ከቻለ በባህሪያችሁ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያውቃል። በኃጢአት ከወደቃችሁ፣ በፍጥነት አዕእምሮአችሁን እና ልባችሁን በክሶች እና በኩነኔዎች ያጠቃል።**

***ሜጬቆን*** *- ማገደል*

*; በአእምሮ ወይም በሰውነ ት የሚሰማ ሸክም ወይምሚደናቀፍ ስሜት.*

መሰረታዊ እውነ ት

እግዚአብሐር ልጆቹን በፈቃደኝነ ት ከዚህ ዓለምጋር መመሳሰልን እንዲተዉእንዲሁም በመንግስቱ ሞርሆች ማሰረት እንዲኖሩ ይጠይቃል።

**የእግዚአብሄርን *መመሪያዎች* እስክትታዘዙ እና በቃሉ እና በሀይሉ ሀይል ጸንታችሁ እስክትቆሙ ድረስ ይህ ዑደት *ደጋግሞ* ይቀጥላል። እግዚአብሔር በሰይጣን ጥቃት እና በሥጋችሁ ምኞት ላይ ፍጹም ድል የምታገኙበትን *መንገድ* አዘጋጅቶላችኋል። መሸነፍ፣ *መታለል* ወይም መጥፋት አያስፈልግም።**

### ትምህርት 7-በጦርነቱ ውስጥ ድል

በዘፍጥረት ሰይጣን በሰው ልጆች ላይ ያደረሰውን የመጀመሪያ ጥቃት እና የሰው ልጅ መጥፋት ዘግቦአል ። ድል ምን ይመስላል? ማቴዎስ 4:1-11 ኢየሱስ በሰይጣን ሊፈተን ወደ ምድረ በዳ የሄደበትን ጊዜ ይዘግባል። በቁጥር 2 ላይ፣ ኢየሱስ አርባ ቀንና ሌሊት ያለምግብ እንዳሳለፈ እንማራለን። ምን ያህል እንደተራበ እና የተዳከመ ሊሆን እንደሚችል መገመት ትችላለህ።

በማቴዎስ 4:3 ሰይጣን በመጀመሪያ የፈተነው እንዴት ነው?

____________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________

__________________________________________________________

ሰይጣን በመጀመሪያ ኢየሱስን የፈተነው የሥጋው ምኞት በማንሳት የምግብ ረሃቡን እንዲያስታግስ ነው። ኢየሱስ በቁጥር 4 ላይ ምን ምላሽ ሰጠ?

____________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________

ሰይጣን በቁጥር 5-6 ላይ ያለውን ሁለተኛውን ፈተና እንዴት እንደሞከረው አንብብ። ሰይጣን ኢየሱስ ከመቅደሱ ላይ እንዲወረውር እና እግዚአብሔር መላእክቱን ልኮ እንዲይዘው አድርጎ ፈተነው። በሌላ አነጋገር፣ በክብሩ እንዲመካ ፈልጎ ነበር። ኢየሱስ በቁጥር 7 ላይ እንዴት ምላሽ ሰጠ?

____________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________

የሰይጣን ሦስተኛውን ፈተና በቁጥር 8-9 አንብብ። ሰይጣን ኢየሱስን በአይን አምሮት ሊያታልለው ሞከረ እና እሱን ሰግዶ ቢያመልክው የምድርን መንግስታት ሁሉ እንደሚሰጠው ቃል ገባለት።

ኢየሱስ በቁጥር 10 ላይ ምን ምላሽ ሰጠ?

____________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________________

ሰይጣን በቁጥር 11 ላይ ምን አደረገ?

ኢየሱስ ለእያንዳንዱ  ፈተና  ምን ምላሽ ሰጠ?

ኢየሱስ ጠላት የሚያቀርበውን እያንዳንዱ ፈተና ሁሉ ለመዋጋት እና የሥጋውን ፍላጎት ሁሉ ለመቋቋም የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል እንደ መሣሪያ ተጠቅሟል። መዝሙር 119:11 ምን እንድታደርግ ያበረታታሃል?

በዕብራውያን 4:12 ላይ ቃሉ እንዴት ይገለጻል?

የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰይፍ ተገልጿል ። እርሱም ለሰይጣን ጥቃቶች እና ለሥጋ ፈተናዎች ዋና ማጥቂያችን ነው ። ኢየሱስ እውነትን በማቅረብ የጠላትን ውሸት ተዋግቷል። የእግዚአብሔርን ቃል በልብህ እንዴት ታስቀምጣለህ ? ኢያሱ 1:7-9 ምን ያስተምራል?

በየቀኑ መፅሃፍ ቅዱስን ለማጥናት፣እውነቱን ለማሰላሰል እና በትግልዎ ውስጥ የሚረዱዎትን ምንባቦች ለማስታወስ መበርታትን ያስፈልጋል። አንድ ወታደር በሰይፍ ያለው ብቃት የሚወሰነው በትኩረቱ፣ በቁርጠኝነቱ እና በአጠቃቀሙ ነው። የእግዚአብሔር ቃልም እንዲሁ ነው። ቀንና ሌሊት አሰላስለው፣ አስታውሰው ፣ የተማርከውን በተግባር ላይ አውለው። ያኔ ጊዜ ብቻ ነው ጠንካራ ማጥቃትን የምትችለው እንዲሁም የሰይጣንን ውሸቶች መቁረጥ የምትችለው። ግን ጠንካራ መከላከያም ያስፈልግዎታል።

> መሰረታዊ እውነት
> ክርስቶስን በቅርብ ስንከተልና በመንፈስ ስንሞላ፣ በሥጋችንና በኃጢአታችን ላይ ድል እንነሳለን።

ኤፌሶን 6:10—11ን አንብብ። መንፈሳዊ ጥንካሬ ከየት ይመጣል?

ሰይጣንን እንዴት እንቃወማለን?

**የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ**

ኤፌሶን 6:14—17 አማኝ በጠላት ጥቃት ላይ ድልን ለማግኘት መልበስ ያለበትን ስድስት መንፈሳዊ የጦር ትጥቅ ይዘረዝራል። ከታች ጻፋቸው።

1. ___
2. ___
3. ___
4. ___
5. ___
6. ___

በቁጥር 18 ላይ ምን ተጨማሪ መመሪያ ተሰጥቷል?

ማስረታዊ እውነት

እግዚአብሔር ልጆቹ የሰጣቸውን
ማሉ ትጥቆችእየተገለገሉ
በመንፈሳዊ ትግሎቻቸውውስጥ
ፍፁምድል እንደሚያሸንፉ ቃል

**ጸሎት እንደ ክርስቲያኖች ካሉን ሁሉ በጣም ኃይለኛ መሣሪያ ነው። በሰማይና በምድር ላይ ሙሉ ስልጣን ካለው ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ እና ቀጥተኛ የሆነ የግንኙነት መስመራችን ነው ። በማንኛውም አጋጣሚ እና በሁሉም ወቅቶች፣ በጸሎት አማካኝነት ከሰማዩ አባታችን ጋር መቀራረብ አለብን።**

**ትምህርት 8–ክርስቶስ ጠበቃችን ነው።**

ሮሜ 8:13 እና ገላትያ 5:17 *ሥጋችንንና መንፈሳችንን በተመለከተ ምን ይላሉ?*

እንደ ክርስቲያን፣ በአንተ ውስጥ የሚኖሩ ሁለት ተቃራኒ ተፈጥሮዎች አሉህ - መንፈስ እና ሥጋ። ሥጋህ የኃጢአት ተፈጥሮህ ነው—“አሮጌው ሰውነትህ” ወይም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት “አሮጌው ሰው” ነው። ልማዶቹ፣ ምኞቶቹ፣ አስተሳሰቦቹ እና ምላሾቹ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፅድቅ የሚቃወሙ እና ከእሱ መራቅን ይፈልጋሉ።

ሮሜ 6 አንብብ።

ከክርስቶስ ጋር የሞተው ምንድን ነው (ቁጥር 6)?

አሮጌው ሰውነትህ */የቀድሞው ራስህ ለምን ነበር የሞተው* (ቁጥር 2, 6, 10, 11)?

አሁን ከምን ነፃ ወጥተናል (ቁጥር 7)?

እግዚአብሔር ከኃጢአትና ከኃጢአታችን ተፈጥሮ ጋር በምናደርገው ትግል ምን እንድናደርግ አዞናል (ቁጥር 13)?

ሮሜ 6 ወደ ክርስቶስ ከመምጣታችን በፊት የኃጢአት ባሪያዎች እንደ ነበርን ያስተምረናል። በኃጢአት ላይ ድልን ለማግኘት አሁን የምን ባሪያ መሆን አለብን (ቁጥር 16-22)?

ገላትያ 2:20 በራስህ አባባል ደግመህ ጻፍ።

ኢየሱስ ለኃጢያአታችን ሁሉ ስርየት በመስቀል ላይ አርጎአል ። የኃጢአትህ ተፈጥሮ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ ተቀበረ በዚህም አሁን በእርሱ አዲስ ሕይወት አለህ! ሰይጣን ግን በተሰጠህ ነፃነት ሊጨቁንህ ይሞክራል። አሁንም የጠላት እና የስጋ ፈተናዎች ያጋጥምሀል። ከሳሹ በኢዮብ እንዳደረገው ሁሉ እናንተንም ለመምታት እና እናንተን ለማስፈረድ እድልን በትዕግስት እየጠበቀ ነው። ግን ብቻህን አይደለህም ።

ዕብራውያን 2:18 ስለ ኢየሱስ ምን ይላል?

ኢየሱስ የሚገጥሙህን ፈተናዎች ያውቃል እና የሥጋህን ምኞቶች ይረዳል። ጠላት እንዴት እንደሚያጠቃህ እንኳን አስቀድሞ ያውቃል።

በሉቃስ 22፡31 ላይ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ምን አለው?

እንደገና፣ ሰይጣን ከማጥቃቱ በፊት ከኢየሱስ ፈቃድ እንደሚያስፈልገው እናያለን። ኢየሱስ በቁጥር 32 ምን አለ? የኢየሱስን ቃላት ልብ በሉ፦ "ወደ እኔም በተመለስክ ጊዜ"። ጴጥሮስ ወደ ክርስቶስ ለመመለስ በመጀመሪያ ከእርሱ መራቅ ያስፈልገው ነበር። ጴጥሮስ በቁጥር 33 ከክርስቶስ ጋር እስከ ሞት ድረስ እንደሚሄድ በልበ ሙሉነት ተናገረ፣ ኢየሱስ ግን በቁጥር 34 እንዴት መለሰ?

በእርግጠኝነት፣ ሉቃስ 22፡56—62 የጴጥሮስን ክህደት መዝግቧል። ሰይጣን ኢየሱስን ጴጥሮስን እንደ ስንዴ ሊያበጥረው ዘንድ አስፈቀደው፤ ኢየሱስም ሰጠው። ኢየሱስ በጠላት እንድንፈተን የፈቀደው ለምንድን ነው?

ሉቃስ 22:32 ን ጻፍ።

ሰይጣን የጴጥሮስን እምነት ለማጥፋት እና ክርስቶስን በመክዳቱ በሐዘንና በውርደት ሊጫነው እንደፈለገ ምንም ጥርጥር የለውም፣ ነገር ግን ኢየሱስ ሌሎች እቅዶች ነበሩት -"ወደ እኔም በተመለስክ ጊዜ ወንድሞችህን አጽናቸው።"
1ኛ ቆሮንቶስ 10፡12-13 ስለ ፈተና ምን ይላል?

1 ዮሐንስ 2:1-2ን አንብብ። የእኛ ጠበቃ ማነው?

***ጠበቃ*** *የሌላውን ጉዳይ የሚሟጎን; ማንኛውንም ምክንያት በክርክር የሚከላከል፣ የሚያጸድቅ ወይም*

______________________________________________________

በቆላስይስ 2፡14-15 መሰረት ክርስቶስ ምን አደረገ?

________________________________________________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________________________________________________

**ሰይጣን የሚከስህ እና የሚኮንንህ ነገር ሁሉ በመስቀሉ ላይ ተሰርዟል። የክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ የጠላቱን ትጥቅ አስፈትታል፣አሁን ለጊዜው ያለው በነገስታቱ ንጉስ ምህረት ነው። ኢየሱስ በዙፋኑ ላይ በአብ ቀኝ ተቀምጦ ስለእናንተ ይሟገታል። ድልህ ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ነው! ነገር ግን በዚህ ምድር ላይ እስትንፋስን እስከሳብክ ድረስ፣ በብርሃን ለመራመድ ወይም በጨለማ ለመራመድ በማንኛውም ጊዜ ምርጫ ይኖራል።**

**ትምህርት 9-በብርሃን ተመላለሱ**

ለአፍታ ጨለማን አስብ። ምንድነው ይሄ? የብርሃን አለመኖር ብቻ አይደለምን? ሙሉ ጨለማን ለማግኘት ብቸኛው መንገድ ሁሉንም የብርሃን ምንጮች ማጥፋት ነው. ኤፌሶን 6:12 ሰይጣን "የዚህ ዓለም የጨለማ ገዥ" ሲል ገልጾታል። የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ብርሃን ምን ይላሉ?

1ኛ ዮሐንስ 1:5

የዮሐንስ ወንጌል 8:12

መዝሙረ ዳዊት 119:105

የዚህ ዓለም ጨለማ ምክንያት የእግዚአብሔር፣ የኢየሱስ ክርስቶስ እና የመንፈስ ቅዱስ አለመኖር ነው። ጠላት የሚገዛው በዚያ ነው። ጳውሎስ በአንድ ወቅት በክፉ ተጽዕኖ ሥር ነበር፣ በጨለማ ውስጥ ይኖር ነበር። ክርስቲያኖችን ሊያሳድድ ወደ ደማስቆ በሚወስደው መንገድ ሲሄድ፣ ኢየሱስ ተገልጦለት ና ተገዳድሮት ተልእኮውን ለወጠው። በሐዋርያት ሥራ 26:17-18 ላይ ኢየሱስ ጳውሎስን ሊጠቀምበት የነበረው ለምን ነበር አለ?

የእግዚአብሔር ብርሃን የዚህን ዓለም ጨለማ ያበራል። ብርሃኑም ላንተ/ቺ ደርሷል።

የሚከተሉትን ጥቅሶች በራስዎ ቃላት ጻፉ።

ቆላስይስ 1:13

__________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________

ኤፌሶን 5፡8-9

__________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________

በእግዚአብሔር ጸጋና በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት ከዚህ ዓለም ጨለማ ድነሃል።የሱን ብርሃኑን ትሸከማለህ ነገር ግን ከጨለማ ነፃ አይደለህም። ሉቃስ 11:35 ምን ያበረታታል?

__________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________

በዮሐንስ 3፡20-21 መሠረት ጨለማ ምን ይፈራል?

__________________________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________________________

የጨለማው ብቸኛው ስጋት ብርሃን ነው ይህም የማይታየውን ስለሚያጋለጥ ነው። የዳናችሁት

በእምነት ነው፣ ነገር ግን ጠላት እና ይህ ዓለም ወደ ጨለማውን በፈቃድህ እንድትገባ መፈታተናችሁን ይቀጥላሉ። ሆን ተብሎ የእግዚአብሔርን ቃል አለመታዘዝ ከብርሃኑ መውጣት እና እራስዎን ለአጋንንት ጥቃት ማጋለጥ ነው። ይህም ሰይጣን የሚጠቀምበትን ቦታ ያገኛል ማለት ነው ። የደበቅከው ና ያልተናዘዝከው  ጨለማ በልብህ አለን ?

1ኛ ዮሐንስ 1፡6-7 ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ህብረት ምን ይላል?

ይህ የእርስዎ የየቀኑ ደቂቃ በደቂቃ ፍልሚያ ነው ። የእግዚአብሔርን ትጥቅ በመልበስ እና በትህትና ለቃሉ በመገዛት የጨለማን ኃይሎች መዋጋት አለባችሁ። በያዕቆብ 4፡6-10 ላይ ያለውን መልእክት ለጥቂት ጊዜ አሰላስል። ይህ ክፍል እርስዎን የወቀሰውና እና ያበረታታዎት እንዴት ነው?

የጠላትን ጥቃት እና የሥጋ ምኞትን በተሳካ ሁኔታ ለመዋጋት እና በእግዚአብሔር ብርሃን እንድንመላለስ ምን መመሪያ ተሰጥቷል?

ሮሜ 12፡1-2

2ኛ ቆሮንቶስ 10፡3—6

ፊልጵስዩስ 4:6-8

2 ጢሞቴዎስ 2:22

ገላትያ 5:16

---

**መሰረታዊ እውነት**

ምንምእንኳን ኃያል ጠላት ቢኖረንም፡ የበለጠና ሁሉምሀይል ያለውእግዚአብሔር አለን፤ እርሱ በሰይጣንን ሙሉ በሙሉ የሚያዝ ነው።

**አንድ የመጨረሻ ሀሳብ**

በወደቀ አለም ለክርስቶስ የምንኖር አማኞች እንደመሆናችን መጠን መንፈሳዊ ጦርነትን ሁሌ መዋጋት እንቀጥላለን። ሆኖም፣ እግዚአብሔር በሱ ድል አድራጊነት ጸንተን እንድንቆምና በሰይጣን ወይም በሥጋችን ምኞት እንዳንሸነፍ ቃል ገብቷል። እንዳንወድቅ እግዚአብሔር ታማኝ ይሆናል እናም እሱ ወዳለበት ሰማያዊ ቤታችን በደህና ያደርሰናል። የሚቀጥለው እና የመጨረሻው ምዕራፍ የሚያተኩረው ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ዘመን ፍጻሜ በሚገልጹት ላይ ነው።

## *ምዕራፍ* 7
## *ሞት እና የመጨረሻው ጊዜ*

*ለማይታወቅ ነገር መፍራት እና መገረም የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ምላሽ ነው። ከሞት በኋላ ስላለ ሕይወት የሚደረግ ውይይት መስማት የሚያስደስትም ሆነ የሚያስፈራ ሊሆን ይችላል። ከህይወት በኋላ ያለው ሕይወት በብዙ ፊልሞች እና ቴሌቪዥን ስራዎች ውስጥ በተደጋግሞ የሚገኝ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ሞተን ተመለስን የሚሉና ታሪካቸውን የሚናገሩ ሰዎች የሚጽፉት መፅሃፎች ብዙ ጊዜ በጣም የሚሸጡ ይሆናሉ። የሰው ዘር ከዚህ ሕይወት ባሻገር ምን እንዳለ ለማወቅ የጋራ ፍላጎት አለው። ምክንያቱም እውነታው እንደሚያሳየው ሁሉም ሰው በመጨረሻ ሟች ነውና ነው።*

**ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት እና በፍጻሜው ዘመን ስለሚሆነው ነገር ብዙ ፍልስፍናዎች አሉ ምክንያቱም በታሪክ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ሥልጣኔዎች ሕይወት ከሞት በኋላ እንደማያልቅ ስለሚስማሙ ነው። የሰው ነፍስ ዘላለማዊ እንደሆነች ማመን በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ በደመ ነብስ ያለ ይመስላል። ከሁሉም የተለያዩ የድህረ ህይወት ፍልስፍናዎች ውስጥ መምረጥ ቀላል ነው። በጣም የሚስበንን/ማራኪ የሆነውን ማመን እንመርጣለን።ግን የእውነቱን እና የማታለሉን ፍልስፍና እንዴት መለየት እንችላለን ?**

### ትምህርት 1–እውነትን መለየት

በ1 ዮሐንስ 4:1 *ምን ዓይነት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል* ?

__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________

በ1 ዮሐንስ 4:2—3 *መሠረት የእውነትን መንፈስ እንዴት ልንለይ እንችላለን*?

__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________

**የእግዚአብሔር ቃል ሁሉም እውነት የሚቆምበት መሰረት ነው። በዮሐንስ 14:6 ኢየሱስ ክርስቶስ "እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ። በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" ብሎ ተናገረ። ኢየሱስ በዮሐንስ 10:9 ላይ እርሱ በር እንደሆነ እንዲህ አለ፦ "በእኔ የሚገባ ቢኖር እርሱ ይድናል።" የእውነት መፈተኛው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።**

**ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ይሰበካልን? የኃጢአት መናዘዝ፣ ለክርስቶስ መገዛትና ትምህርቱን መታዘዝ ይመከራል? በገላትያ 1:6—9 ላይ ያለውን ማስጠንቀቂያ በድጋሚ ጻፉ።**

__________________________________________________________________________________
________________________________

መክብብ 3:11 ኣንብብ። እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ያስቀመጠው ምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ሥራ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ ማን ሊያውቅ ይችላል?

እግዚአብሔር ዘላለማዊነትን በልባችን አስቀምጧል፣ ነገር ግን የምንኖረው በጊዜ በተገደበ ጊዜያዊ አለም ውስጥ ነው። የዘላለምን ፅንሰ-ሀሳብ እና በመጨረሻው ዘመን ዙሪያ ያሉ እንቆቅልሾች በዐእምሮአችን ለመረዳት አስቸጋሪ ናቸው።

የእግዚአብሄርን ስራ በራሳችን እውቀት መግለጥ አይቻልም ነገርግን አንዳንድ ምስጢሮቹን እንድንገልጥ መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል። የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሞት ምን ይላል? ከሞትን በኋላ ምን ይሆናል? ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መጨረሻው ዘመን ምን ያስተምራሉ?

**ማስታወሻ**፡ በተለያዩ ክርስቲያኖች መካል የእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት የተለያዩ ትርጓሜዎች እንዳሉ መረዳት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን እኔ የማበረታታችሁ የጳውሎስን ምክር በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡10-31 የፃፈውን ነው እሱም ልዩነቶች በእናንተ እና በሌሎች አማኞች መካከል አለመግባባት እንዲፈጠር አትፍቀዱ የሚለውን ነው ። በትሑትነት መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስን ጥበብ ፈልግ፣ እንዲሁም አምላክን ሁልጊዜ አክብር።

**ሲኦል**

የለበስነው ስጋ ለያንዳንዱ ግለሰብ ነፍስ ወይም መንፈስ ጊዜያዊ ድንኳን ነው። ነገር ግን የሰው ስጋ ወደ ፍጻሜው ሲመጣ ነፍስ ምን ይሆናል? ኢየሱስ በሉቃስ 16፡19-31 ላይ ስለ ሁለት ሰዎች አንድ ታሪክ ተናግሯል– ስለ አንድ ሀብታም ሰው እና አልዓዛር ስለሚባል ለማኝ።

አልዓዛር ከሞተ በኋላ የት ሄደ (ቁጥር 22)?

ሀብታሙ ሰውዬ ከሞተ በኋላ የት ሄደ (ቁጥር 22-23)?

ለሀብታሙ ሰው ሲኦል ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 23-24)?

የአብርሃም እቅፍ ለአልዓዛር ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 25)?

አልዓዛርንና ባለጠጋውን በመሃላቸው ምን ለያያቸው (ቁጥር 26)?

> *ገሃነብ - የሙታን መኖሪያ; የጠፉ ሟፍስት ቦታ; ሲኦል.*

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሲኦል በመባል የሚታወቀው ገሀነብ ፣የሰው ልጅ መንፈስ ከስጋ ወጥቶ/ተለይቶ የሚሄዱበት ቦታ ነው። ሲኦል የሚለው የዕብራይስጥ ቃል አንዳንድ ጊዜ እንደ “መቃብር” “ጉድጓድ” ወይም “ገሀነብ” ተብሎ እንደየአምዱ ይተረጎማል። በጊዜው ሲኦል ሁለት ክፍሎች ያሉት ይመስላል፣እነሱም በማይሻገር ገደል ይለያሉ ነበር፣. በአንደኛው በኩል በእግዚአብሔር ለማያምኑ የተከለለ የሥቃይ ቦታ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔር ለሚያምኑት የተሰጠ የመጽናኛ ቦታ ነው። ግን ሲኦል የሚገኘው የት ነው?
በሕዝቅኤል መፅሀፍ ላይ ግብፃውያን እንደሚሞቱና “ጉድጓድ” ተብሎ በሚጠራው በሲኦል ጥልቀት ውስጥ ከሚገኙት ክፉ ገዥዎች ጋር እንዴት እንደሚገናኙ የሚናገር ትንቢት አለ። ሕዝቅኤል 32:18, 24ን አንብብ። ሲኦል የሚገኘው የት ነው?

የ1ኛ ሳሙኤል መጽሐፍ ንጉሥ ሳኦል ከነቢዩ ሳሙኤል መንፈስ (ከሞተ ቦሃላ ከአካሉ የተለየው ነብስ/መንፈስ)ጋር ያደረገውን ከተፈጥሮ በላይ የሆነ መንገድ ግንኙነት ይዘግባል። 1 ሳሙኤል 28:1-19 አንብብ።

በዚህ ቁጥር የተገለፀችው? ሴት ምን አየች (ቁጥር 13)?

ሳሙኤል ሳኦል በሚቀጥለው ቀን የት ይሆናል ብሎ ነገረው (ቁጥር 19)?

የሳሙኤል መንፈስ ሳኦል በማግስቱ እንደሚሞትና እነሱን እንደሚቀላቀል ለሳኦል ነገረው።

ዳዊት ስለወደፊቱ አሚሚቱ በመዝሙር 16:9-11 ላይ ምን ብሏል?

ዳዊት ከሞተ በኋላ ወደ ሲኦል እንደሚሄድ የተረዳ ይመስላል ነገር ግን እግዚአብሔር በዚያ እንደማይተወው በማመኑ ተስፋ ነበረው፡፡ በመጨረሻ በእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም እንደሚኖር እምነት ነበረው ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱሱን ኢየሱስን መበስበስን እንዲያይ አይፈቅድምና፡፡

**ትምህርት 2–የሲኦል ኃይል ፈርሷል**

ኢየሱስ ለሦስት ቀናት እንደሞተ እና መንፈሱ ከምድራዊ አካሉ ተለይቶ እንደነበረ እናውቃለን። መንፈሱ ግን የት ሄደ? መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በሞተበት ወቅት ስለነበረበት ሁኔታ ዝርዝር ማብራሪያ ባይሰጥም አንዳንድ ቁልፍ ጥቅሶች ግን ፍንጭ ይሰጡናል።

በማቴዎስ 12፡40 መሰረት ክርስቶስ ከሞተ በኋላ የት ሄደ?

______________________________________________________________________________

______________________________

በሉቃስ 23፡43 ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለነበረው ሌባ ምን አለው?

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡18-20 መሰረት ኢየሱስ የሰበከው ለማን ነው?

______________________________________________________________________________

______________________________

1 ጴጥሮስ 4፡6 ሙታንን በተመለከተ ምን ይላል?

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

በራዕይ 1፡18 ላይ ኢየሱስ ስለራሱ ምን አለ?

______________________________________________________________________________

______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________

እንደነዚህ ቅዱሳን ጽሑፎች መሰረት ክርስቶስ "የሲኦል መክፈቻዎች" ይዞ ወደ ሲኦል ወርዶ በአብርሃም እቅፍ ውስጥ ወደሚገኘው ክፍል (ከዚህ ጊዜ ቦሀላ "ገሀነበ" ብለን ወደምንጠራው )ሄዷዋል ፡፡

ከዚያ በስቃይ ስፍራ ውስጥ በእሳት ባህር ውስጥ ለነበሩት ነፍሳት ሁሉ ሰበከ (1 ጴጥሮስ 3:18—20)፣ እንዲሁም በአብርሃም ሕብረት/እቅፍ ውስጥ ለነበሩት ነፍሳትም ወንጌልን ሰበከ(እሱ መሲሁ እንደሆነም በመግለፅ ) (1 ጴጥሮስ 4:6)።

ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ብዙም ሳይቆይ ለማርያም በተገለጠ ጊዜ በዮሐንስ 20:17 ምን አለ?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ከኤፌሶን 4:8—10 የተማርከውን ግለጽ።

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ በሞቱ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር የሚለውን አስተሳሰብ የሚሰርዙ ይመስላሉ። የበለጠ የሄደበት ቦታ የሚመስለው ነፍሳትን ለመስበክ "ወደ ምድር ታችኛ ክፍል" ወደ ሲኦል ነው። ከዚያም ወርዶ  ፈሪሃ አምላክ ያላቸውን  ከሞት መንጋጋ አውጥቶ፣ "ምርኮን ማረከ"።

የኢየሱስ ሞት እና ትንሣኤ ምንጊዜም በአጽናፈ ዓለም/universe/ ታሪክ ውስጥ ሁልጊዜ እጅግ ወሳኝ ክስተት እንደሆነ ይቀጥላል ። ከክርስቶስ ትንሣኤ በፊት የሞቱት ሁሉ ከሁለቱ የሲኦል ክፍሎች በአንዱ ታስረው ነበር። ነገር ግን ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ በሲኦል ውስጥ ያለው የሞት ኃይል ተሰብሮአል/ወድቋል።

በሆሴዕ 13:14 ላይ ምን ትንቢት ተነግሯል?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ሮሜ 6:9 ስለ ክርስቶስ ምን ይላል?

______________________________________________________________________________

በዮሐንስ 10፡17-18 መሠረት ኢየሱስ በምን ላይ ሥልጣን ነበረው?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡19-22 መሰረት ክርስቶስ ለሞቱት ምን ሆነላቸው?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

በሲኦል የነበሩት ጻድቃን መናፍስት ቅዱስ በጉ ደሙን አፍሶ የኃጢአታቸውን ዋጋ ከፍሎ እስኪሸፍንላቸው ድረስ በእግዚአብሔር ፊት መውጣት አልቻሉም ነበር፡፡ እርሱ የእነርሱ የመጀመሪያ ፍሬ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሲኦል ውስጥ ያሉት ፈሪሃ አምላክ የሌላቸው ነፍሳት እስከ መጨረሻው ፍርድ ድረስ በዚያ ይቀራሉ፣ ነገር ግን በአብርሃም እቅፍ የነበሩት ቅዱስ ነፍሳት  አሁን በሰማይ ከኢየሱስ ጋር ናቸው፡፡

ፊልጵስዩስ 2:5-11ን አንብብ፡፡

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ምን ሰጠው?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

ለኢየሱስ ስም የሚሰግዱት ሦስት የተለያዩ  ቦታዎች  የትኞቹ ናቸው?

________________________________________________________________________

ምላስ ሁሉ ምን መመስከር አለበት?

የሰማይ፣ የምድር እና የሲኦልም ጥልቁ ነዋሪዎች ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይሰግዳሉ። ምላስ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራል።

**የአማኙ ሞት**

አሁን ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ በአብ ቀኝ ተቀምጦ ሳለ በሚከተለው ጥቅስ መሰረት የሚሞቱ አማኞች ነፍሳቸው ምን ይሆናሉ?

2ኛ ቆሮንቶስ 5፡8

ፊልጵስዩስ 1፡23

> ማስረታዊ እውነት
> ክርስቲያኖች ከዚህ አለም ሕይወት ሲያልፉ ወዲያውወደ ሰማይ ኢየሱስ ወዳለበት እንዲሄዱ ይደረጋል ።

ሞት ምን ያስተምራሉ?

ከክርስቶስ ትንሣኤ ጀምሮ የሞቱ አማኞች ሁሉ ነፍሳቸው በሰማይ ከኢየሱስ ጋር ለመሆን በቀጥታ ይሄዳል። ወደ ሲኦል አይወርዱም ምክንያቱም ክርስቶስ ለኃጢአታቸው ዋጋ ከፍሏልና።

የሚከተሉት ክፍሎች በክርስቶስ ሆነው ስለሞቱ ጻድቃን

ዕብራውያን 2፡14-15

1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13—14

መዝሙረ ዳዊት 116:15

ምሳሌ 14፡32

በኢየሱስ ክርስቶስ አማኝ ከሆንክ ሞትን በመፍራት መኖር ወይም ድነው ላለፉ ወዳጆች ማዘን አያስፈልግም። ከዚህ ይልቅ የማዳን ጸጋውን ሳያውቁ ለሚጠፉት የኢየሱስ ክርስቶስን ምሥራች ለመስበክ ትጋ ፣ምክንያቱም መጨረሻው እየቀረበ ነውና።

## ትምህርት 3–የመጨረሻው ዘመን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት ትንቢታዊ ግንዛቤን የሚሰጡ ብዙ ምንባቦች አሉ። ሊቃውንት እና ተንታኞች በመጨረሻው ዘመን ዙሪያ ያሉትን ምስጢራት ሁሉ ለመረዳት ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥንቃቄ አጥንተዋል። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ እንዳመለከትኩት፣ በክርስቲያኖች መካከል በዘመን ፍጻሜ ስለሚፈጸሙት ልዩ ልዩ ክንውኖች የጊዜ ሰሌዳን በተመለከተ የተለያዩ ትርጓሜዎች እንዳሉ መረዳት አስፈላጊ ነው።

እያንዳንዱን አተረጓጎም በመፈተሽ ጊዜ ከመውሰድ ይልቅ በእያንዳንዱ ዐቢይ ክስተት ዙሪያ ያሉትን ቅዱሳት መጻሕፍት በአጠቃላይ መመልከቱ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል እነሱም፦ የክርስቶስ ተቃዋሚ መገለጥ፣ ታላቁ መከራ፣ የቤተ ክርስቲያን/ክርስቲያኖች መነጠቅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት፣ የክርስቶስ ሺህ ዓመት ግዛት ፣ የመጨረሻው የፅድቅ ፍርድ ፣ ሲኦል፣ እና አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ናቸው ።

### የመጨረሻዎቹ ቀናት

መጨረሻው ሲቃረብ እንዴት እናውቃለን? በመጨረሻዎቹ ቀናት የዓለምን ባህሪ በተመለከተ የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ይላሉ?

ማቴዎስ 24:3-8

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ማቴዎስ 24:9-14

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2 ጢሞቴዎስ 3:1-7

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2ኛ ጴጥሮስ 3፡3-4

1ኛ ዮሐንስ 2፡18

ጢሞቴዎስ አንዳንድ የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት በመጨረሻው ዘመን ያሉበትን ሁኔታ ገልጿል። ከሚከተሉት ጥቅሶች ምን ትማራለህ?

1 ጢሞቴዎስ 4:1-3

2 ጢሞቴዎስ 4:3-4

እነዚህ ገለጻዎች ዛሬ ምን ያህል እንደተለመዱ ማወቁ ልብን ይሰብራል። እነዚህ ባህሪያትና ክስተቶች በሁሉም ጊዜያት ውስጥ ሁልጊዜ እንደነበሩ እውነት ነው፣ ነገር ግን ምድር ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ስትዘጋጅ ድግግሞሽነታቸውና መጠናቸው ይጨምራል። እነዚህ ባህሪያት በታሪካችን ከሌላው ጊዜ ይልቅ ዛሬ በጣም ጎልተው ይታያሉ ብዬ እከራከራለሁ። መጠናቸውም ጊዜ እየገፋ ሲሄድ እየጨመረ ይሄዳል። ነገር ግን መጨረሻው እንደተጀመረ እንዴት እናውቃለን?በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-3 መሰረት ማን መገለጥ አለበት?

## ትምህርት 4–የክርስቶስ ተቃዋሚ መገለጥ

የክርስቶስ ተቃዋሚ ማን ነው? በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ የዳንኤል መጽሐፍ በመፅሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች የተሞላ ነው። በዚያን ጊዜ ዳንኤል ትንቢቶቹ ምን ትርጉም እንዳላቸው ባያውቅም ከበርካታ ዓመታት በኋላ እግዛብሔር ዮሐንስን የራእይን ትንቢታዊ መጽሐፍ እንዲጽፍ አነሳስቶታል፤ ይህም የዳንኤልን ትንቢቶች ግልጽ እንዲሆን አድርጎታል።

ራእይ 13:1-5ን አንብብ።

ዘንዶው ለአውሬው ምን ሰጠው (ቁጥር 1-2)?

______________________________________________________________________

______________________________

ዮሐንስ ከአውሬው ራሶች በአንዱ ላይ ምን አይቷል (ቁጥር 3)?

______________________________________________________________________

______________________________

ቁስሉ ምን ሆነ (ቁጥር 3)?

______________________________________________________________________

______________________________

ዓለም ለተአምራዊው ፈውሱ ምን ምላሽ ሰጠ (ቁጥር 3-4)?

______________________________________________________________________

______________________________

የአውሬው ስልጣን እስከመቼ ቀጠለ (ቁጥር 5)?

______________________________________________________________________

______________________________

በምዕራፍ 6 ላይ፣ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው ዘንዶ ሰይጣን ነው። የክርስቶስ ተቃዋሚ አውሬ ተብሎ ይታወቃል። ራዕይ 13:2 ሰይጣን በምድር ላይ እንዲገዛ ለክርስቶስ ተቃዋሚ ኃይሉንና ሥልጣኑን እንደሰጠው ይናገራል። በአንድ ወቅት ላይ አንድ ዓይነት ገዳይ ቁስል ይደርስበታል፣ ነገር ግን ከዚያም በተአምራዊ ሁኔታ ይፈወሳል። ዓለምም እርሱን በማምለክ ምላሽ ትሰጣለች።

ዳንኤል 9:26 "ሊመጣ ያለውን ልዑል" በሚል አሁን *የክርስቶስ ተቃዋሚ* እንደሆነ የምናውቀውን ያመለክታል።

ዳንኤል 9:27ን አንብብ። ይህ "ልዑል" በመጀመሪያ ምን ያደርጋል?

______________________________________________________________________

______________________________

"በሳምንቱ አጋማሽ" ምን ያደርጋል?

እንደዚህ ትንቢት፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ ከእስራኤል እና ከአጎራባች አገሮች ጋር አንድ ዓይነት የሰላም ስምምነት ያደርጋል ወይም ያጠናክራል። ነገር ግን "በሳምንቱ መካከል" ስምምነቱን አፍርሶ አንድ ዓይነት አስጸያፊ ነገር ይፈጽማል።በራዕይ 13፡5-8 መሠረት፣

የክርስቶስ ተቃዋሚ ከአርባ ሁለት ወራት በኋላ ምን ያደርጋል?

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡3—4 የክርስቶስን ተቋዋሚ ድርጊቶች የሚገልጸው እንዴት ነው?

እነዚህ ሦስቱ ምንባቦች (ዳንኤል 9፡27፤ ራእይ 13፡6፤ 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡4) ሁሉም የሚናገሩት ስለ አንድ ክስተት ነው። በማቴዎስ 24፡15 ላይ ኢየሱስ ይህን ክስተት ምን ብሎ ጠራው?

የጥፋት ርኩሰት የሚሆነው የክርስቶስ ተቋዋሚ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ ራሱን አምላክ ነኝ ብሎ ሲናገር ነው። ዳንኤል ይህ ክስተት "በሳምንቱ መካከል" እንደሚፈጸም ሲጠቅስ፣ ራዕይ ደግሞ ከአርባ ሁለት ወራት በኋላ እንደሚፈጸም ይናገራል። በግልጽ፣ በዳንኤል ትንቢቶች ውስጥ ያለው እያንዳንዱ የአንድ ሳምንት ጊዜ ሰባት ዓመት ጋር እኩል ነው።ራእይ 13:11—17ን አንብብ።

ሌላኛው አውሬ በምድር የሚኖሩት ሁሉምን ምን እንዲያደርጉ ያረጋቸዋል  (ቁጥር 12)?

ሌላው አውሬ ዓለምን የክርስቶስን ተቋዋሚ እንዲያመልክ የሚያሳምን እንዴት ነው (ቁጥር 13-14)?

ለክርስቶስ ተቋዋሚው ምስል የማይሰግዱ ሰዎች ምን ይሆናሉ (ቁጥር 15)?

አውሬው እያንዳንዱን ሰው ምን እንዲያደርግ ያስገድደዋል (ቁጥር 16-17)?

ራእይ 16:13 ሌላውን አውሬ የሚገልፀው እንዴት ነው?

በዳንኤል 8፡23-25 ያለውን ትንቢት አንብብ እና የክርስቶስ ተቋዋሚን አገዛዝ ግለጽ፡፡

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ሰይጣን (ዘንዶው)፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ (አውሬው) እና ሐሰተኛው ነቢይ (ሌላው አውሬ) በዚህ ምድር ላይ የሚገዙት ጊዜ *ታላቁ መከራ* ተብሎ በሚባለው ነው፡፡ በዳንኤል መጽሐፍ ትንቢት ይህ ጊዜ ሰባት ዓመት እንደሚቆይ ተናግሯል፡፡ ራእይ በዚህ ጊዜ ውስጥ ስለሚፈጸሙት አስደናቂ ክንውኖች ዝርዝር ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

**ትምህርት 5–ታላቁ መከራ**

ኢየሱስ በማቴዎስ 24፡15-22 መከራውን እንዴት ገለጸ?

በዳንኤል ትንቢት 9:24 ላይ ስለ መከራው ግብ/አላማ ምን ይላል?

በዳንኤል የተተነበዩት ሰባ ሳምንታት (490 ዓመታት) የእስራኤል ሕዝብ ከመሲሑ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የሚያደጉትን እርቅ ያመለክታሉ። ከሰባዎቹ ሳምንታት ውስጥ ስልሳ ዘጠኙ አልፈዋል። እስራኤላውያን ኢየሱስን በትንቢት የተነገረለት መሲህ አድርገው አልተቀበሉትም፣ እና እስከ ዛሬም ድረስ አዳኛቸው እስኪመጣ ድረስ እየጠበቁ ናቸው። የክርስቶስ ተቋዋሚ ከተገለጠ በኋላ የመጨረሻው ሳምንት (ማለትም ሰባቱ ዓመታት) ይጀምራል።

ታላቁ መከራ የማያምነው ዓለም በጽድቅ-ቢስነታቸው ጫፍ ላይ የሚደርሱበት፣ የእስራኤልም ሕዝብ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ መሲሕ የሚቀበሉበትና እግዚአብሔር እርሱን በናቁት ላይ ቁጣውንና ፍርዱን የሚያወርድበት ልዩ የሰባት ዓመት ጊዜ ነው። ስለ መከራው ጊዜ በጣም ግልጽ የሆነው መግለጫ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። ብዙ ክርስቲያኖች ይህን መጽሐፍ ለማንበብ ይፈራሉ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ ለመረዳት አስቸጋገር ስለሚሆን፣ ነገር ግን እንደ ራዕይ 1:3 እና 22:7፣ ይህን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሰዎች እግዚአብሔር ምን ቃል ይሰጣል?

የሚከተለው በመከራው ወቅት ስለሚፈጸሙት ክንውኖች አጠቃላይ ንድፍ መግለጫ ነው።

**ስድስቱ ማህተሞች**

በራዕይ 5:1 ላይ በሰባት ማኅተሞች የታተመ ጥቅልል መጽሐፍ ቀርቧል። ምዕራፉ እየገፋ ሲሄድ፣ ሰባቱ ማኅተሞች አንድ በአንድ ይከፈታሉ ፣ የታላቁ መከራ ክስተቶችም ይገለጣሉ። እያንዳንዱ ማኅተም ሲከፈት፣ ታላላቅ ጥፋቶችና የእግዚአብሔር ቁጣና ኃይል ማሳያዎች በምድር ላይ መፍሰስ ይጀምራሉ። ከራዕይ ምዕራፍ 6 ጀምሮ ይከታተሉ።

- ሐሰተኛው ክርስቶስ ሊያሸንፍ መጣ (ቁጥር 1-2)
- ሰላም ከምድር ተወሰደ (ቁጥር 3-4)
- ረሃብ (ቁጥር 5-6)
- ሞት በሰይፍ፣ በረሃብ፣ በቸነፈር እና በአውሬው (ቁጥር 7-8)
- ሰማዕታት የሚሆኑ ክርስቲያን ለበቀል ይጮኻሉ (ቁጥር 9-11)
- ሽብር እና የተፈጥሮ አደጋዎች (ቁጥር 12-17)

**ሰባቱ መለከት**

በራዕይ 8:1 የሰባተኛው ማኅተም መከፈት ተከትሎ በሰማይ ጸጥታ ነገሰ ከዚያም ተከታታይ ሰባት የመለከት ተነፋ። መላእክት የመጀመሪያዎቹን ስድስት መለከቶች ሲነፉ፣ ምድር የእግዚአብሔርን ቁጣ ማየቷን እስከ ሰባተኛው ቀንደ መለከት ድረስ ቀጠለች፣ ሰባተኛውም የሚመጣውን የክርስቶስን መንግሥት ያውጃል። በራእይ 8:2—9:21 እና 11:15—19 ተከታተል።

- የምድር አንድ ሦስተኛው ይቃጠላል (8:7)
- የባህር ሲሶው ደም ሆነ (8:8-9)
- የወንዞች አንድ ሶስተኛው መራራ ተደረገ (8:10-11)
- ጨረቃ እና የከዋክብት አንድ ሶስተኛው ጨለሙ (8:12-13)
- የሚያሰቃዩ ፍጥረታት ከጥልቅ ጉድጓድ ይለቀቃሉ (9:1-12)
- የሰው ልጅ አንድ ሦስተኛው በወራሪው ሠራዊት/አውሬ  ጠፋ (9:13—21)
- ነጎድጓድ፣ መብረቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ እና የበረዶ አውሎ ንፋስ (11:15—19)

**ሰባቱ የቁጣ ፅዋዎች**

በመጨረሻው መለከት ሲነፋ፣ ሌላ ተከታታይ ፍርድ ፈሰሰ በራዕይ 16 ላይ እንደተገለፀው በእግዚአብሔር ቁጣ የተሞሉ ሰባት ጽዋዎች ናችው ። በምዕራፉ ሁሉ ያንብቡት

- የአውሬውን ምልክት በተሸከሙት ላይ ቁስል ይወጣል (ቁጥር 2)
- ባሕር ደም ሆነ የባሕር ሕይወትም ሁሉ ተገደለ (ቁጥር 3)
- ወንዞችና  ምንጮች ደም ሆኑ (ቁጥር 4)

• ፀሐይ ሰዎችን በነበልባላ ታቃጥላለች (ቁጥር 8)

• የአውሬው መንግሥት ጨለመች (ቁጥር 10)

• ኤፍራጥስ ወንዝ ለመጪው ጦርነት ዝግጅት ይደርቃል (ቁጥር 12)

• መብረቅ፣ ነጎድጓድ፣ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ እና የበረዶ አውሎ ንፋስ (ቁጥር 17-21)

**የአርማጌዶን ጦርነት**

ስድስተኛው የእግዚአብሔር ፍርድ ፅዋ ሲፈስ ፣ የአርማጌዶን ጦርነት ተብሎ የሚታወቀው ታላቁ የእግዚአብሔር ጦርነት ተከፈተ (16፡13—16)። የክርስቶስ ተቃዋሚ እና የምድር ነገሥታት ሁሉ ሠራዊቶቻቸውን በመሰብሰብ ከእስራኤል እና ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚደረገው ጦርነት ይሰባሰባሉ ።

በራእይ 16:17 መሠረት ሰባተኛው ጽዋ በፈሰሰ ጊዜ ከሰማይ ቤተ መቅደስ የታወጀው የትኞቹ ቃላት ናቸው?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

የአርማጌዶን ጦርነት ማብቂያ ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ይከተላል። ስለዚህ አስደናቂ ክስተት ከመናገሬ በፊት፣ በመጀመሪያ ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከተወሰኑ የፍጻሜ እምነቶች አንዱን ማስተዋወቅ እፈልጋለሁ።

> *Eschatology /*
> ***ኢሻቶሎጂ***- *እንደ ሞት፣ ትንሳኤ፣ ያለመሞት፣ የዘመኑ ፍጻሜ የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት፣ ፍርድ እና የወደፊት ሁኔታ ያሉ የኋለኛው ወይምየ ሚሺፈሽ ዘመን ትምህርት።*

> መሰረታዊ እውነት
> የሚከራውዘመን እግዚአብሔር ልጁን በናቁት ላይ ቁጣውን የሚያወርድበት የሰባት ዓመት ጊዜ ነው።

## ትምህርት 6–የቤተክርስቲያን መነጠቅ

መነጠቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን ከምድር ላይ ነጥቆ ወደ እርሱ የሚወስድበት ክስተትን ያመለክታል። 1ኛ ተሰሎንቄ 4:16—17̈(1ኛ ተሶሎንቄ 4 15) ምን እንደሚሆን ይናገራል?

________________________________________
____________________

________________________________________
____________________

"የተነጠቀ" የሚለው ሐረግ ከግሪክ ቃል "ሀርፓዞ" የመጣ ሲሆን ትርጉሙ "ተነጥቆ መወሰድ" ማለት ነው። የላቲን አቻው ቃል "ራፒዮ" ሲሆን የእንግሊዝኛው "መነጠቅ" የሚለው ቃል የመጣው ከዚህ ነው።

በክርስቶስ አካል ውስጥ፣ መነጠቅ መቼ እንደሚሆን በተመለከተ ክርክር አለ። በአጠቃላይ ሦስት የአስተሳሰብ ትምህርት ቤቶች አሉ፡

- **ቅድመ-መከራ** - መነጠቅ የሚከናወነው ከታላቁ መከራው ጊዜ በፊት ነው።
- **የመከራ አጋማሽ** - መነጠቅ የሚከናወነው በታላቁ መከራው አጋማሽ ወቅት ላይ ነው።
- **ከመከራ በኋላ** - መነጠቅ የሚከናወነው ከታላቁ መከራው ጊዜ በኋላ ነው የሚሉ ሲሆን።

እነዚህ እያንዳንዳቸው አመለካከቶች የይገባኛል ጥያቄያቸውን ለመደገፍ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይጠቀማሉ ነገር ግን የተለያዩ ትርጓሜዎች አሏቸው። የእነዚህ ልዩነቶች ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን ለሚፈጸሙት ሁነቶች ሁሉ ግልጽ የሆነ የጊዜ ገደብ አለመስጠቱ ነው። እነዚህ ስለ ንጥቀት የተለያያ የጊዜ ሰሌዳ ንድፈት ያላቸው አስተሳሰቦች ቢኖሩም፣ ሁሉም ግን የቤተክርስቲያን ንጥቀት (ራፐቸር) እንደሚሆን ይስማማሉ።

ኢየሱስ በዮሐንስ 14፡1-3 ምን አስተማረ?

________________________________________
____________________

________________________________________
____________________

የቅድመ- ታላቁ መከራ እይታ ከሌሎቹ ሁለት አመለካከቶች ጋር ሲወዳደር የበለጠ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ እንዳለው አምናለሁ። ቀጥሎ ያለው ስለ መነጠቅ ምን ያስተምራል?

ማቴዎስ 24:36-44

________________________________________
________________________________________
________________________________

1ኛ ተሰሎንቄ 1፡9-10

1 ተሰሎንቄ 5:1-11

ራእይ 3:10

ከመከራ በፊት የነበረው አመለካከት የእግዚአብሔርን ባህሪ እና ጻድቃንን ከሚመጣው ቁጣ ለማዳን ያለውን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ እንደሚያካትት አምናለሁ። መነጠቅ በተለይ መቼም ቢሆን፣ እውነታው ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ቤተክርስቲያኑን ወደ እርሱ እንደሚሰበስብ ነው።

**የተከበረው አካል**

ከኢየሱስ ትንሳኤ በኋላ ና ከመነጠቅ በፊት የሞቱት አማኞች ነፍሳቸው ከሥጋዊ አካላቸው ተለይታለች። ነፍሳቸው በሰማይ ከኢየሱስ ጋር ስትቀላቀል ሥጋቸው በምድር ላይ ይቆያል። ነገር ግን መነጠቁ በሚከሰትበት ጊዜ ተአምራዊ ነገር ይከሰታል።

1 ቆሮንቶስ 15:49—58ን አንብብ።

አማኙ የማንን አምሳል ይይዛል (ቁጥር 49)?

በአማኙ ላይ ምን ይሆናል (ቁጥር 51-52)?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

አማኙ “የሚለብሰው” (ቁጥር 53) ምንድን ነው?

_______________________________________________

ከዚህ ለውጥ በኋላ “የተዋጠው” ምንድን ነው (ቁጥር 54)?

_______________________________________________

በመጨረሻው መለከት ሲነፋ፣ ነፍሳቸው በሰማይ ያሉ ግን አካላቸው ምድር ላይ ተቀብሮ የነበሩ አካላቸው የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፣ በምድር ላይ በሕይወት ካሉት ጋር “በቅፅበት” ተለውጠው ለእነርሱ የተዘጋጀውን የከበረ ሥጋ ይቀበላሉ። . ጊዜያዊው ምድራዊ ስጋችን የተሰራው ከምድር አፈር ነው ፣ ነገር ግን የምንለብሰው የከበረ አካል የማይበላሽ እና የማይሞት፣ ለሰማያዊው የዘላለም ሕይወት የሚገባው ነው።

በ1ኛ ዮሐንስ 3፡2 መሰረት እነዚህ የተከበሩት አካላት ምን ይመስሉ ይሆን?

_______________________________________________

_______________________________________________

አዲሱ የተከበረው የአማኞች አካል ከትንሣኤው በኋላ እንደ ኢየሱስ የተከበረ አካል ይሆናል። በሚቀጥሉት ምንባቦች ውስጥ የክርስቶስ አካል በምን ዓይነት ባሕርያት ተገልጾዋል?

ሉቃስ 24፡31

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ሉቃስ 24፡36-43

ዮሐንስ 20፡24-29

መነጠቅ ከመከራው በፊትም ሆነ በመከራው ጊዜ ወይም በኋላ ክርስቶስ እንደገና ወደ ምድር ለመውረድ ሲዘጋጅ አማኞች በአዲስ በተከበረ ሰውነታቸው  ይሆናሉ ።

**ትምህርት 7–የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት**

የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከየትኛውም ጊዜ በላይ አስገራሚ ክስተቶች አንዱ ይሆናል። የክርስቶስ የመጀመሪያ ወደ ምድር መምጣት በትሕትና የተሞላ ነበር - በጨለማ መንደር ውስጥ በከብቶች በረት ውስጥ ከአንዲት ድሀ ድንግል የተወለደው እና ተራ እረኞች ያበሰሩት ነበር ። ዳግም ምጽአቱ ግን እሱ ያለውን አስደናቂ ኃይልና ክብሩን  ሙሉ ማሳያ ይሆናል። የአርማጌዶን ጦርነት ሲቀጣጠል፣ ክርስቶስ ራሱን ለዓለም ሁሉ ያሳውቃል።

ራእይ 19:11—21ን አንብብ።

ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ እንዴት ተገልጿል (ቁጥር 11-13)?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ክርስቶስን የሚከተሉ ሰዎች እንዴት ይገለፃሉ (ቁጥር 14)?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ኢየሱስ አህዛብን በምን ይመታቸዋል (ቁጥር 15)?

______________________________________________________________________________

በኢየሱስ ልብስና ወገቡ ላይ የተጻፈው ምንድን ነው (ቁጥር 16)?

______________________________________________________________________________

የክርስቶስ ተቃዋሚ እና ሐሰተኛው ነቢይ (ቁጥር 20) ምን ሆነ?

______________________________________________________________________________

ክርስቶስን የማይቀበሉ ሁሉ ምን ይሆናሉ (ቁጥር 21)?

በቁጥር 19 ላይ የተጠቀሰው “በሰማይ ያለው ሰራዊት” ቀደም ሲል የተነጠቁትን እና የተለወጡ አማኞችን ያቀፈ ነው።

በራእይ 17:14 መሠረት ከእርሱ ጋር ያሉት ምን ተብለዋል?

በይሁዳ 14-15 መሠረት፣ “ጌታ” በወረደው ጊዜ የሚመጣው ከማን ጋር ነው?

እርሱን በማይቀበሉት ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለማስፈጸም ክርስቶስ ከቤተክርስቲያኑ ጋር ወደ ምድር ይመጣል። ስለ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት የተማርከውን ጻፍ።

ማቴዎስ 24፡27-31

የሐዋርያት ሥራ 1፡11

ዘካርያስ 14:1-4

ራእይ 1:7

ማኅረታዊ እውነት
ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን በማጠቅ ወደ ሰማይ ከሰበሰበ በኋላ፣ አማኞች የከበረ አካላቸውን ይቀበላሉ እና ወደ ምድር ለሁለተኛውምጽአቱ ሲማለስ አብረውት ይማጣሉ ።

**የክርስቶስ የሺህ ዓመት ግዛት**

**ኢየሱስ ጠላቶቹን ካሸነፈ በኋላ መንግሥቱን በምድር ላይ ያደርጋል፡፡ ራእይ 20:1-6ን አንብብ፡፡**

ሰይጣን ምን ይሆናል (ቁጥር 1-3)?

ከክርስቶስ ጋር የሚኖረው እና የሚነግሥ ማነው (ቁጥር 4)?

ይህ ጊዜ ምን ያህል ቆይታ ይኖረዋል (ቁጥር 4-6)?

ኢየሱስ በምድር ላይ ከቅዱሳኑ ጋር ለአንድ ሺህ አመት ሲገዛ ሰይጣን መጨረሻ በሌለው ጉድጋድ ውስጥ ይታሰራል፡፡

ከሚከተሉት ምንባቦች ስለ ሺህ ዓመት ጊዜ ምን ተማራችሁ?

ኢሳይያስ 2:1-5

ኢሳይያስ 11:5-10

በሉቃስ 1፡31-33 መልአኩ ገብርኤል ለማርያም ምን ነገራት?

የኢየሱስ የሺህ ዓመት ግዛት እጅግ በጣም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ፍጻሜ ይሆናል። ታላቅ የሰላም፣ የደስታ እና የመጽናናት ጊዜ ይሆናል፣ ግን ለዘላለም አይቆይም። ራእይ 20:7-10ን አንብብ።

በሺህ ዓመቱ መጨረሻ (ቁጥር 7) ምን ይሆናል?

ሰይጣን ከተለቀቀ በኋላ ምን ያደርጋል (ቁጥር 8)?

በሰይጣን የተታለሉ ሰዎች ምን ይሆናሉ (ቁጥር 9)?

የሰይጣን የመጨረሻ ፍርድ ምን ይሆን (ቁጥር 10)?

ይህ የራዕይ ክፍል ከሰይጣን ተጽእኖ ውጪ በሺህ ዓመቱ ጊዜ ኢየሱስን ለመቃወም የሚመርጡ ብዙ ሰዎች እንደሚኖሩ ያሳያል ሴይጣን እንኳን ሳያስታቸው ። ሰይጣን ከተለቀቀ በኋላ፣ ክርስቶስን እና ህዝቡን ለማጥፋት በሚደረገው ሙከራ የመጨረሻውን መጨረሻ ጥቃት ለመሰንዘር እምቢተኞችን ይሰበስባል። ነገር ግን እግዚአብሔር በሰማይ በእሳት ያጠፋቸዋል። ሰይጣንንም ወደ ክርስቶስ ተቃዋሚው እና ወደ ሐሰተኛው ነቢይ በእሳት ባሕር ውስጥ ለዘላለም ይወረውረዋል። ከዚያም የመጨረሻውና የማይደገመውን ፍርድ ይሰጣል።

**ትምህርት 8–ጻድቅ ፈራጅ**

በሐዋርያት ሥራ 17፡30-31 መሠረት፣ እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ እንዲሆን የሾመው ማን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ኢየሱስ በዮሐንስ 5፡30 መሠረት የእርሱ ፍርዱ የጽድቅ ነው ያለው ለምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ማቴዎስ 25:31—46ን አንብብ።

ኢየሱስ በፊቱ የተሰበሰቡትን ሕዝቦች ሁሉ ምን ያደርጋቸዋል (ቁጥር 32-33)?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ኢየሱስ በቀኙ ላሉት ምን ይላቸዋል (ቁጥር 34-40)?

______________________________________________

______________________________________________

ኢየሱስ በግራው ያሉትን ምን ይላቸዋል (ቁጥር 41-46)?

የሚገርመው፣ ሁሉም መንገዶች ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ። እያንዳንዱ ሰው በፈጣሪ ፊት ይቆማል ወይ በትህትና የክርስቶስን ፅድቅ ለብሶ ወይም ራቁቱን፣ እስከ በደሉ ወይ በኃጢአታቸው የተኮነነ ሆኖ ። እንደገና በቤተክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስን ፍርድ በተመለከተ አንዳንድ የተለያዩ እምነቶች/አመለካከቶች አሉ ። አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ጊዜያት ስለሚፈጸሙ በርካታ የኢየሱስ ፍርዶች ይናገራል ብለው ያምናሉ። ሌሎች ከሺህ አመት ግዛቱ መጨረሻ ላይ የሚፈጸመው አንድ ፍርድ ብቻ እንዳለ ያምናሉ።

ምንም እንኳን እነዚህ የተለያዩ እምነቶች/አመለካከቶች ቢኖሩም፣ እውነታው ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ፈራጅ ነው፣ እናም ሁሉም በፊቱ ይቆማሉ ፍርዳቸውንም ይቀበላሉ።

**የክርስቶስ የፍርድ ወንበር**

አንዳንዶች የክርስቶስ የፍርድ ወንበር ለዳኑት ብቻ የተወሰነ የመጀመሪያው ፍርድ እንደሆነ ያምናሉ ። ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ና በታላቁ መከራ ወቅት ላይ እንደሚከናወን ያምናሉ ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለኃጢአት ዋጋ ስለከፈለ የኩነኔ ፍርድ አይደለም። የተቀበሉት ሁሉ ከኃጢአታቸው ተለይተዋል። ከዚህ ይልቅ የእያንዳንዱ ግለሰብ ታማኝነትና አገልግሎት ፍርድ ነው ።

1 ቆሮንቶስ 3:11—15ን አንብብ።

ለሁሉም አማኞች መሠረት ማን ነው (ቁጥር 11)?

በክርስቶስ መሠረት ላይ ምን ዓይነት ነገሮች መገንባት ትችላላችሁ (ቁጥር 12)?

ሥራህ እንዴት ነው የሚፈተነው (ቁጥር 13)?

ውጤቶቹ ምን ይሆናሉ (ቁጥር 14-15)?

በ1 ቆሮንቶስ 4:5 መሠረት ኢየሱስ ወደ ብርሃን የሚያመጣው ምንድን ነው?

ከ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡9—11 ምን ተማራችሁ?

በህይወታችሁ ውስጥ ከምትገነቡት ነገር የክርስቶስን የእሳት ፈተና የማይቋቋም ማንኛውንም ነገር ታውቃላችሁ?

በጽድቅ ፈራጅ ፊት የልብ ሚስጥራዊ ዓላማዎችና ምኞቶች ሁሉ ይገለጣሉ። በራስ ወዳድነት ምኞት፣ በዓመፅ እና በትዕቢት የሚደረግ ማንኛውም ነገር አመድ ሆኖ ይቃጠላል። ነገር ግን ንጉሡን በማገልገል ውስጥ ያለው ትህትና፣ ራስን የማይወድ ታዛዥነት ያሉት ተግባራት ይቆያሉ እናም በተገቢው መልኩ ይሸለማሉ ።በሚከተሉት ምንባቦች ውስጥ ምን ይሸለማል?

2 ጢሞቴዎስ 4:7-8 ሽልማት፡ የ_______________________________ አክሊል

ያእቆብ 1:12 ሽልማት፡ የ_______________________________ አክሊል

1ኛ ጴጥሮስ 5:4 ሽልማት፡ የ_______________________________ አክሊል

በራዕይ 4:9-11 መሠረት ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች አክሊላቸውን ምን ያደርጋሉ?

____________________________________________________________________
__________________________

____________________________________________________________________
__________________________

____________________________________________________________________
__________________________

በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ከመሆን ጋር ሲወዳደር የትኛውም ሽልማት ወይም ክብር ዋጋ የለውም!

**ትምህርት 9-የነጩ ዙፋን ፍርድ**

**የነጩ ዙፋን ፍርድ በአንዳንዶች ዘንድ ንስሐ ላልገቡ ኃጢአተኞች ብቻ ተጠብቆ እንደሚቆይ ይታመናል እናም የሚከናወነው በክርስቶስ የሺህ ዓመት ግዛት መጨረሻ ላይ ሰይጣን ወደ እሳቱ ባህር ከተወረወረ  በኋላ ነው።**

ራእይ 20:11-15 ኣንብብ።

ፍርዱ ሲጀምር ክርስቶስን የተቃወሙ ምን ለማድረግ ይሞክራሉ (ቁጥር 11)?

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

ሙታን እንዴት ይፈረድባቸዋል (ቁጥር 12)?

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

ሙታን ከየት መጡ (ቁጥር 13)?

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ ሰዎች ምን ይሆናሉ(ቁጥር 14-15)?

______________________________________________________________________
____________________________

______________________________________________________________________
____________________________

**በሲኦል ጥልቅ ውስጥ ፍርድን የምትጠብቅ እያንዳንዱ ነፍሳት እና በእግዚአብሔር እሳት በሺህ አመት መጨረሻ ጦርነት የተበሉ ሁሉ በናቁት ና ባልተቀበሉት ፊት ይቆማሉ  ከዛም ፍርዳቸውን ይቀበላሉ።**

በሚቀጥሉት ምንባቦች መሠረት የተፈረደባቸው ሰዎች ለኢየሱስ ምን ምላሽ ይሰጣሉ?

ሮሜ 3፡19

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ፊልጵስዩስ 2፡9-11

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ሁሉን ቻይ በሆነው ጻድቅ ዳኛ ፊት አፍ ሁሉ ጸጥ ይላል። ሁሉም ጌታ መሆኑን ያውቃሉ ፍርዱንም ይቀበላሉ.።

**ሲኦል**

ክርስቲያኖች ስለ ገሀነብ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መመሪያ/ ትምህርት አለመቀበል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለመደ መጥቷል። ብዙዎች አምላክ የፍቅር አምላክ እንደሆነና ማንንም ሰው ወደዚህ አስከፊ የሥቃይ ቦታ ለዘላለም እንደማይልክ ያስባሉ።ከሚከተሉት ምንባቦች ስለ እግዚአብሔር ልብ ምን ተማራችሁ?

1 ጢሞቴዎስ 2፡3-6

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2ኛ ጴጥሮስ 3፡9

______________________________________________________________

እግዚአብሔር በእውነትም የፍቅር አምላክ ነው እና ማንም ወደ ሲኦል እንዲገባ አይፈልግም። ለዚህም ነው የማምለጫ መንገድን በትክክል ያዘጋጀው። ዮሐንስ 3:16—21ን አንብብ።

እግዚአብሔር ልጁን የላከው ለምንድን ነው (ቁጥር 16-17)?

ሰዎች የተወገዙት እንዴት ነው (ቁጥር 18-20)?

አሳሳቢው እውነት ሰዎች አዳኙን በመቃወም ለራሳቸው ሲኦልን መምረጣቸው ነው። ኢየሱስ ጻድቅ ፈራጅ ነው፣ እና ኃጢአተኞች ንስሐ ለመግባት እና ይቅርታውን ለመቀበል እምቢ ካሉ፣ ለዘለአለም የኃጢአታቸውን ቅጣት እንዲከፍሉ ይፈርዳል። የገሃነምን ትምህርት የማይቀበሉ ሰዎች የኢየሱስንም ትምህርቶች ችላ ብለዋል ። በሚቀጥሉት ምንባቦች ውስጥ የክርስቶስን ቃላት ጠቅለል አድርጉ።

ማርቆስ 16:15-16

ማቴዎስ 13:40-43

> ማሳረታዊ እውነት
> እርሱን የማይቀበል ሁሉ ውግዘተና ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ክርስቶስ

**በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት፣ ሲኦል እውነተኛ ቦታ እንደሆነና የተዘጋጀውም አዳኙን ለሚክዱ ሰዎች ነው። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን የተቀበሉት ስማቸው በህይወት መጽሐፍ ተጽፎ ከኢየሱስ ጋር ለዘለአለም ይኖራሉ።**

**ኢየሱስ በሚከተሉት ምንባቦች ውስጥ ስለ መንግሥተ ሰማያት ምን ብሏል?**
**ዮሐንስ** 14፡1-3

**ዮሐንስ** 16፡22

## ትምህርት 10–አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር

የክርስቶስ የሺህ ዓመት ግዛት ሲያበቃ፣ ራዕይ ስለ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይናገራል። ራዕይ 21—22 አንብብና ባዶውን ሙላ።

- ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር ______________________________________________(21፡1)።
- ከዚህ በሃላ __________________________________ (21፡1) አልነበረም።
- ገነት እግዚአብሔር _________________ ___________(21፡3) ያለበት ቦታ ነው።
- እግዚአብሔር ________________________________ (21፡4)።
- ክዚህ በሃላ _________________________________ (21፡4) አይኖርም።
- እግዚአብሔር ሁሉን ያደርጋል __________________ (21፡5)።
- የተጠማ ___________________________________ (21፡6)።
- ድል የሚነሳ ______________________________ (21፡7)።
- ገነት ብሩህ ናት፣ ልክ እንደ ___________________ (21፡11)።
- ግድግዳው የተሠራው ከ______________________ (21፡18-20) ነው።
- አሥራ ሁለቱ በሮች የተሠሩት ከ_____________....__ (21፡21) ነው።
- ጎዳናዎቹ የተሠሩት ከ________________________ (21፡21) ነው።
- በሰማይ ያለው መቅደስ ______________________ (21፡22) ነው።
- መንግሥተ ሰማያት በ________________________ (21፡23) ታበራለች።
- በሮቹ በጭራሽ ____________________________ (21፡25)።
- ዜጎቹ _____________________________________ (21፡27) ናቸው።
- በሰማይ የ__________________________________________ ወንዝ አለ (22፡1)።
- የ__________________________________________________ (22፡2) ዛፍ አለ።
- ____________________________________________________ (22፡3) የለም።
- ____________________________________________________ (22፡3) አለ።
- በመንግሥተ ሰማያት እኛ ___________________________ (22፡3-5)።

መንግሥተ ሰማያት ያለው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቅድስና እና ክብር ያንጸባርቃል። በሰማይ ያሉ የእግዚአብሔር ቤት ነዋሪዎች በሙሉ በእርሱ ፊት በፍጹም ሰላም፣ ደህንነት እና ፍፃሜ ለዘላለም ይኖራሉ። ከእንግዲህ ፍርሃት፣ ሀዘን፣ መከራ፣ ብቸኝነት ወይም ችግር አይኖርም። እግዚአብሔር ይመስገን!

> መሰረታዊ እውነት
> መንግሥተ ሰማያት እግዚአብሔር ለሁሉምአማኞች እያዘጋጀ ያለው ቦታነው። ሁሉምነዋሪዎች በሚጨረሻ ፍጹምፍቅርን፣ ደስታን፣ ሰላምን፣ ነፃነትን፣ እርካታን እና ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ጋር ትክክለኛ ግንኙነትያገኛሉ።

### መደምደሚያ

ይህ ምዕራፍ ስለ ሞት እና ስለ ፍጻሜው ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ስለሚናገረው ነገር የተወሰነ

ግልጽነት እንደሰጣችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ስለ ሲኦል፣ ስለ መነጠቅ፣ ስለ መከራ ጊዜ እና ስለመሳሰሉት የተለያዩ ፓስተሮች፣ ተንታኞች ወይም የነገረ መለኮት ምሁራን ተለዋጭ ትርጉሞች ልታገኝ ትችላለህ፣ ነገር ግን በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያለው የተለያየ አስተያየት እንዲረብሽህ አትፍቀድ። ለእውነት ወደ ቅዱሱ ቃል ተመልከት እና በትህትና ለእግዚአብሔር የመጨረሻ ሥልጣን እና ሁሉን አዋቂነት ተገዛ። አንተ በኃያሉ እጆቹ ውስጥ ነህ፣ እና በፍጻሜው የሚሆነው ነገር ሁሉ በእሱ ቁጥጥር ስር ነው። በየቀኑ በእርሱ እና በቃሉ ኑሩ። ፃድቅን ተከታተል፣ ወንጌልን አካፍል/ስበክ ፣ እናም የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የክብር ዳግም መምጣት በጉጉት ይጠብቁ!

### አባሪ ሀ

### ከእግዚአብሔር ጋር ዕለታዊ ቅርርብን ማዳበር

በድህነት የሚገኘው ትልቁ ስጦታ ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ እና ጥገኛ ግንኙነት የመፍጠር ችሎታ ነው። ከእኛ  ከዚህ በላይ የበለጠ የሚፈልገው ነገር የለም።

**ጊዜ መድቡ።**

የቀኑን በጣም ጥሩውን  ሰዓት ምረጥ(ጥዋት ወይም ምሽት)  እና ከእግዚአብሄር ጋር  ለእለት ተዕለት አምልኮ ስጥ። በማትችለው  ግብ እራስህን ለተስፋ መቁረጥ ወስጥ አታስገባ ። በትንሽ ጀምር፣ እና ስታድግ ደግሞ ጊዜው ጨምር። በየቀኑ በአስራ አምስት ደቂቃዎችን መድበህ ጀምር ።

**የመጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ ምረጥ።**

አንድ ምዕራፍ (ረጅም ምዕራፍ ከሆነ ያነሰውን ምዕራፍ) ወይም ጥቂት ጥቅሶችን አንብብና አሰላስለው። በተጨማሪም፣ ከዕለታዊ የአምልኮ መጽሐፍ ማንበብ ትፈልግ ይሆናል። ለጥቆማዎች **አባሪ ለ**፡ የሚመከሩ መጽሐፍትን ይመልከቱ።

**ጸልዩ።**

አሁን ባነበብካቸው እውነቶች ላይ በተለይ ጸልይ። በሕይወታችሁ ላይ እንዴት እንደሚተገበሩ እንዲገልጽልህ  እግዚአብሔርን ጠይቀው። ራስህን ለስልጣኑ ለማስገዛት እና በታዛዥነት ምላሽ እንድትሰጥ በትህትናን ጸልይ።

**እሱን ስሙት።**

ጥቂት ደቂቃዎችን በዝምታ አሳልፉ፣ ዝም ብላችሁ አዳምጡ። ይህ መጀመሪያ ላይ ምቾት ላይኖረው ይችላል ።  እኛ የምንኖረው የማያቋርጥ ትኩረትን የሚከፋፍል ነገሮች ያሉበት ጊዜ ነው እና በጸጥታ መቀመጥን አልለመድንም.። ጽና እና እግዚአብሔር ለእርስዎ ለመናገር ታማኝ ይሆናል።. መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ውስጥ እንደሚኖር እና በሃሳቦቻችሁ ሊያገለግልዎ እንደሚችል አስታውሱ።

**ማስታወሻ  አስቀምጥ / ፃፍ ።**

ጸሎቶችዎን፣ ልምዶችዎን፣ ሃሳቦችዎን ወይም አስተያየቶችዎን ለግል አገልግሎት እንዲውሉ በየጊዜው በመደበኛነት ይመዝግቡ። ጥቅሶች ለእርስዎ ምን ትርጉም እንዳላቸው እና ጌታ ለልብዎ የሚናገረውን ማንኛውንም ነገር ይፃፉ።

**እንደገና ጸልዩ።**

በጸሎቶችህ ላይ ያለማቋረጥ ትኩረት አድርግ።እንዲመራዎት የ **አመምል**  ዘዴን ይጠቀሙ፡-

አ– አምልኮ–እግዚአብሔርን አምልኩ እና አመስግኑ።

መ– መናዘዝ–ማንኛውንም  ኃጢአቶች መናዘዝ እና ንስሐ መግባት።

ም–ምስጋና–በህይወትህ እግዚአብሔር ስለሰጠህ በረከቶች  ምስጋናህን ግለጽ።

**ል – ልመና -** በትሕትና የአንተን ፍላጎቶች እና የሌሎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ጥያቄ አቅርብ።

በእለታችሁ ሁሉ የእርሱን መገኘት እንድታውቅ እና እውቅና እንድታገኝ  እንዲረዳህ  በመጠየቅ ፀሎትህን ዝጋ።

**አባሪ ለ**

**የሚመከሩ መጽሐፍት።**

**ከእግዚአብሔር ጋር ያለዎትን ግንኙነት ለማጠናከር ብዙ ጥሩ መጽሃፎች ቢኖሩም እርስዎን ለመምራት፣ ለማስተማር እና ለመሞገት የሚከተሉትን እንመክራለን።**

## Discipleship Books

Experiencing God: Knowing and Doing the Will of God by Henry T. Blackaby, Richard Blackaby,
and Claude V. King
*Man to Man* by Charles R. Swindoll
Marriage Is a Ministry series by Craig Caster
Men of Courage: God's Call to Move Beyond the Silence of Adam by Dr. Larry Crabb
Parenting Is a Ministry series by Craig Caster
Understanding Teens series by Craig Caster

## Devotional Books

Daily Experience with God by Andrew Murray
Drawing Near: Daily Readings for a Deeper Faith by John F. MacArthur
Every Day with Jesus: First Steps with New Believers by Greg Laurie
Experiencing God: Knowing and Doing the Will of God by Henry T. Blackaby, Richard Blackaby,
and Claude V. King
Meet the Bible: A Panorama of God's Word in 366 Daily Readings and Reflections by Brenda
Quinn and Philip Yancey
*Moments Together for Couples* by Dennis and Barbara Rainey
My Utmost for His Highest by Oswald Chambers
On the Other Side of the Garden: Biblical Womanhood by Virginia Ruth Fugate
*Our Daily Bread*, simple digital and printed devotionals at https://odb.org/
Self-Confrontation by John C. Broger
*Streams in the Desert* by Mrs. Charles E. Cowman
The Love Dare Day by Day: A Year of Devotions for Couples by Stephen and Alex Kendrick
*The One Year Book of Psalms* by William J. Peterson and Randy Petersen

## Devotional and Discipleship Resources for Teens

Bad to the Bone: Fifteen Young Bible Heroes Who Lived Radical Lives for God by Miles McPherson
Bible app by YouVersion (available on Apple and Android)
BibleProject podcasts and videos, https://bibleproject.com/
Growing Little Women: Capturing Teachable Moments with Your Daughter by Donna J. Miller, with
Linda Holland
Josh McDowell Daily Devotions, subscribe online at josh.org/resources/youth-family/daily-
devotions/youth/
*Talksheets* by David Lynn (various books for junior high and high school)
*Youth Devotions* by Josh McDowell

Relationship Books
*For Men Only* by Shaunti and Jeff Feldhahn
*For Parents Only* by Shaunti Feldhahn and Lisa A. Rice
*For Women Only* by Shaunti Feldhahn
*For Young Men Only* by Jeff Feldhahn and Eric Rice with Shaunti Feldhahn
*For Young Women Only* by Shaunti Feldhahn and Lisa A. Rice
Lady in Waiting: Becoming God's Best While Waiting for Mr. Right by Jackie Kendall and Debby Jones
Praying for Your Future Husband: Preparing Your Heart for His by Robin Jones Gunn and Tricia Goyer
The Power of a Praying Wife by Stormie Omartian

## Talking about Sex

How to Talk Confidently with Your Child about Sex by Lenore Buth
More Than Just the Talk: Becoming Your Kids' Go-To Person about Sex by Jonathan McKee

አባሪ ሐ

*መዝገበ ቃላት*

እነዚህ ትርጓሜዎች የተወሰዱት ከዌብስተር አዲስ ዓለም አቀፍ መዝገበ ቃላት የእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ ሁለተኛ እትም Unabridged፣ G & C Merriam Company (1939) ነው።

**መቆየት/መኖር**: ለመደገፍ፣ለመገዛት፣ ሳይሸነፍ ለመጽናት፣ የተረጋጋ ወይም ቋሚ ሆኖ ለመቆየት።

ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ለመመሥረት እና የድል ሕይወትን ለመምራት፣ በእርሱ ውስጥ መኖር አለብን–በጸሎት ከእርሱ ጋር መነጋገር፣ ቃሉን ማሰላሰል፣ እና የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ማዳመጥ አለብን።

መዝሙር 91:1; ዮሐንስ 15፡4-10

**ተጠያቂነት፡-** መልስ /ሀላፊነት እንዲሰጥ መጠራት ያለበት፣ለአንድ ሰው ተግባር ተጠያቂ "

እንደ ክርስቶስ አካል አባላት፣ እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ለማበረታታት፣ ለመጠበቅ፣ ለመገሰጽ እና ለማረም ባለው ዓላማ እርስ በርሳችን ተጠያቂነት እንዲኖረን ይጠራናል። ሉቃስ 9:10; ሮሜ 14:12; ገላትያ 6:1; 1ኛ ጴጥሮስ 4:5

**ጉዲፈቻ፡-** የራስ አድርጎ መውሰድ ወይም መቀበል; ለማጽደቅ; ለመቀበል; በምርጫ ዝምድና እንደ ልጅ መውሰድ ፣ ወራሽ፣ ጓደኛ ወይም ዜጋ እንዲሆን ።

ኃጢአተኛ ንስሐ ገብቶ ክርስቶስን እንደ አዳኝ እና ጌታ አርጎ ሲቀበል፣ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ በጉዲፈቻ ገብተዋል ማለት ነው እናም ከልጆቹ አንዱ ይሆናሉ። ወደ አብ የመድረስ መብት ተሰጥቷቸዋል እናም ከመለኮታዊው ርስት ይካፈላሉ። በልባቸው ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆናቸውን በልባቸው ያረጋግጣል።

ሆሴዕ 1:10; ዮሐንስ 20:17; ሮሜ 8፡14፣15፣17።

**ሐዋርያ**፡- "የተላከ; መልእክተኛ; ከአሥራ ሁለቱ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት አንዱ፣ በተለይም አብረውት የነበሩትና ምስክሮቹ ሆነው የተመረጡት፣ ወንጌልንም ይሰብኩ ዘንድ የተላኩት።

ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ወደ ራሱ ጠርቶ ከዚያ ወደ ዓለም ላካቸው ፈቃዱን እንዲያደርጉና እና እቅዱን እንዲያሟሉ ዘንድ።

ማቴዎስ 28:18—20; ሮሜ 1፡1; ገላትያ 1፡1

***ዳግመኛ መወለድ***፡"እንደገና መታደስ፤ የታደሰ; መንፈሳዊ ሕይወትን ማግኘት"

እያንዳንዱ ሰው በአካል ይወለዳል ፣ነገር ግን ኃጢአተኛ ንስሐ ገብቶ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ እና አዳኝ አድርጎ ሲቀበል፣ በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ይወለዳሉ። የእግዚአብሔር መንፈስ በልባቸው ውስጥ እንዲኖር ይመጣል፣ የእግዚአብሔርንም መንግስት ሕይወት ለእነሱ ይሰጣል።

ሕዝቅኤል 36:26,27; ዮሐንስ 3፡1-8

**የተወገዘ**፡"ስህተቱ ፣ ጥፋተኛ፣ ዋጋ ቢስነቱ፣መሸነፉ የተፈረደበት/የታወቀ። ቅጣት፣ ውድመት ወይም መውረስ የተፈረደበት ።

እያንዳንዱ ሰው በኃጢአት የተወለደ፣ በደለኛ እና የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት በራሱ ላይ ወሰደ እና የእያንዳንዱን ወንድና ሴት ኃጢአት ወደ መስቀል ተሸከመ፣ ስለዚህም አማኞችን ሁሉ ንጹሕ እና የፀደቁ ናቸው በማለት ተናገረ።

ሮሜ 5፡16—18፤ 8:1; 13፡2።

**ኑዛዜ፡-** "የግል፣ የተደበቀ ወይም እራስን የሚጎዳ ነገር እውቅና መስጠና መናገር /ማረጋገጥ ።

አንድ አማኝ እግዚአብሔርን ደስ በማያሰኙ አስተሳሰባቸው፣ ፍላጎቶች ፣ አመለካከቶች፣ ወይም ድርጊቶች በእግዚአብሔር ቃል ወይም በመንፈስ ቅዱስ ሲወቀስ/ሲወገዝ ትክክለኛው ምላሽ መናዘዝ ነው። እውነተኛ ኑዛዜ በንስሐ ይከተላል።

2 ሳሙኤል 12:13; 1ኛ ዮሐንስ 1፡9-10

**ማሳመን/መውቀስ** ፡- "በጣም ማሳመን ወይም እምነት; ስህተት እንዳለ የመተማመን ወይም እውነቱን ለመቀበል የመገደድ "

መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው በልብ ውስጥ ያለ ኃጢአትን ማሳመን/መውቀስ የሚችለው ። የመንፈስ ቅዱስ ፍርድ ትሑት አማኝን እንዲናዘዝ እና ንስሃ አእንዲገባ ያረገዋል ።

*መዝሙር* 32:3—5; ዮሐንስ 16፡7-8

***ተግሣጽ፡*** *"ማስተማር፣ ለተሰጡት መስፈርት/መመሪያዎች ራስን ማስገዛትን ወይም መታዘዝን መሰልጠን/መማር;* *በመመሪያዎችና ትግበራዎች ማደግ።*

*ማንም በተፈጥሮ መንፈሳዊ ብስለትን እና አምላካዊ ባህሪን አያዳብርም።ባለፀጋው ጌታ ተግሳፅን በእያንዳንዱ አማኝ ህይወት ውስጥ የሚጠቀመው ለማስተማር፣ ለማሰልጠን እና ወደ በሳል ጻድቅ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን ለማሳደግ ነው ።*

*መዝሙር* 86:11; *ዕብራውያን* 12፡5-11

***ማነጽ***፡- *"ግንባታ; ሥነ ምግባራዊ, አእምሮአዊ ወይም መንፈሳዊ መሻሻል; መመሪያ"*

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ሰውን ከአባቱ ጋር ግንኙነት እንዲፈጥር ለማረግ ነው። በተመሳሳይ መልኩ፣ አማኞች በክርስቶስ እንዲያድጉ እና ከአብ ጋር መንፈሳዊ ቅርርብ እንዲኖራቸው እርስ በርሳቸው እንዲበረታቱ ተጠርተዋል።

ሮሜ 15፡2; 1 ቆሮንቶስ 14:12,26; ኤፌሶን 4፡29

**ኅብረት**፡- አንድ ላይ መሆን ፣በፍላጎት, በአካሄድ ወይም ስሜት የተሰባሰቡ ማህበረሰብ፣ በጓደኝነት ወይም በእኩል ላይ የተመሰረተ አብሮ ወይም አንድ መሆን ።

እውነተኛ ክርስቲያናዊ ኅብረት ከአንዱ ወደ አንዱ መሰጠትን እና መቀበልን ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ እና በአካሉ (በቤተክርስቲያን) የመካፈል እና የመሳተፍ የጋራ አንድነት ላይ ያተኩራል።

ዮሐንስ 17:3, 21; 1 ቆሮንቶስ 1:9; 1ኛ ዮሐንስ 1፡3-7

**ማክበር**፡- "ክፍተኛ ክብርን፣ ውዳሴን ወይም አድናቆትን መስጠት፣ ክብር ማድረግ።"

*አማኙ ከክፉ/አመፃ ሥራ ሲሸሽ እና በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲኖር እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ እና በመድኃኒቱ ፍቅር ሲኖር እግዚአብሔርን ያከብራል።***ማቴዎስ** 5:16; 1 ቆሮንቶስ 6:20; *ራእይ* 15:4

**ጸጋ**: "ያልተገባ የእግዚአብሔር ሞገስ፤ ለሰው ልጆች ለመታደስ ወይም ለመቀደስ የተሰጠ ነፃ የእግዚአብሔር ስጦታ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ የተገኘ መዳን፤ የእግዚአብሔር ፍቅር፤ ንሰሀ ለሚገባ ኃጢአተኛ ምሕረት።"

ጸጋ ለማይገባቸው የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ለኃጢአት ይቅርታ ሙሉ በሙሉ ከቸርነቱ የተሰጠ እንጂ ይቅርታ በተደረገለት ሰውየ የትኛውም ሁኔታ/ደረጃ ላይ የተመሰረተ አደለም።

ሰቆቃወ ኤርምያስ 3:22; ሮሜ 5:1-2; 6:14—15።

**ትህትና** : "በመንፈስ ትሑት መሆን፣ ከትእቢትና እና ኩራት ነፃ መሆን፣ ራስን ዝቅ ማድረግ ፣ የመገዛት ወይም ትሑት/ጨዋነት፣ በመንፈስ የማይኮሩ ና ነገረኛ/ጠብ ጫሪ/ተከራካሪ ያልሆነ ።

ትህትና የትዕቢት ተቃራኒ ነው እና የእግዚአብሔር ባህሪ ነው። እግዚአብሔር ከፍ ያለ ነው፣ ነገር ግን ለፍጥረታቱ ደህንነት ሲል ራሱን ዝቅ ያደርጋል። እግዚአብሔር በትሑታን ላይ ጸጋውን ያወርዳል።

መዝሙረ ዳዊት 113:5—6፤ ያእቆብ 4:6

**የጠበቀ**: "በግል ግንኙነት ወይም በማህበረሰብ ውስጥ ቅርብ፤ የሚታወቅ፤ በጥብቅ የተቆራኘ፤ የራስ ውስጣዊ የሆን ።" ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ እንዲሆኑ መንገድ ለመፍጠር እንዲሁም ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲካፈሉ/እንዲፈጥሩ ነው።

ምሳሌ 3:32; ዮሐንስ 15:15

**ጽድቅ መስጠት** (Justification): "ከጥፋተኝነት ወይም ከነቀፋ ነፃ መሆንን ማስታወቅ፣ንስሀ መስጠት፣ ጽድቅ እንደሆነ መቁጠር፤ ከኃጢአት ወይም ቅጣት ነፃ መሆንን"

መጽደቅ የውግዘት ተቃራኒ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ፈራጅ ነው እና ለእያንዳንዱ ሰው የመፅደቅን ወይም የጥፈተኛነትን ፍርድ ይሰጣል። የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ በክርስቶስ ይቅር ተብለዋል እንዲሁም ጸድቀዋል።

ኢሳይያስ 53:11; ሮሜ 3:28።

**ምሕረት፡-** *"በቅጣት ጉዳት ከማድረስ መታገስ፣ ርህራሄን ወይም ይቅርታን የማድረግ ባህሪ ፣ ምህረት ለማድረግ ወይም ለመርዳት ፈቃደኛ መሆን ፣ እንደ ርህራሄ ወይም ሞገስ መገለጫ ተደርጎ የሚቆጠር በረከት።*

እግዚአብሔር ለተቸገሩና ለተጨነቁት  በምሕረት፣ በደግነት ሊረዳ ባለጠጋ ነው። ምንም እንኳን የሰው ልጅ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ጥፋተኛ ቢሆንምና  ፍርዱ የሚገባው ቢሆንም ክርስቶስን እንደ አዳኝ እና ጌታ አርገው ለተቀበሉት ሁሉ ምህረትን ይሰጣል።

ዘጸአት 34:6; ኤፌሶን 2:4

**ትዕቢት/ኩራት**፡- *"የራስን ዋጋ ክፍ የማረግ ስሜት እና ከስር ያለውን ወይም ክፍ ያላለውን መጥላት። ምክንያታዊ ያልሆነ የበላይነት"*

ትዕቢት የትሕትና ተቃራኒ ነው። ትዕቢት እራስን ማፅደቅ፣ እራስን መፈለግ፣ በራስ መተማመን እና ከእግዚአብሔር ነፃ  ማድረግ ነው። በራስ ችሎታ መመካት ወይም እምነት ማድረግ ነው። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን/ኩራተኞችን ይቃወማል።

ምሳሌ 11:2; 16:18; ኢሳይያስ 2:17; 1 ዮሐንስ 2:16; ያእቆብ 4:6

**ማስታረቅ/ቤዛነትን ማግኘት**( propitiation)፡-

*"መርዳትና ምሕረት ማግኘት፤ ማስታረቅ፤ ንስሀ ማስገባት፤ የክርስቶስ ራሱን መስዋዕት ማድረግ እና ሞት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ፍርድ እንዲታገስና በዚህም በእግዚአብሔርና ሰው መካከል እርቅ አእንዲመጣ ሆንዋል/አስችልዋል።"*

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው እናም ክፋትን አጥብቆ ይቃወማል። የእግዚአብሔር ቁጣ በአለም ኃጢአት ላይ የሚመጣው የእርሱ እውነተኛና ቅዱስ ፍርድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ህይወቱን ሲሰጥ የሰው ልጆችን ኃጢአትና ዓመፅ ሁሉ በራሱ ላይ ወሰደ። የደሙ መስዋዕትነት የእግዚአብሔርን ቁጣ አስታገሰ/አረካ። ኢየሱስ የኃጢአታችን ማስተሰረያ ነው። ኃጢአታቸውን ለእግዚአብሔር የተናዘዙ እና ክርስቶስን እንደ አዳኝ በማድረ ጌታ የተቀበሉ ሁሉ ይቅርታ ይደረግላቸዋል እና ከቁጣው ይልቅ የእግዚአብሔርን ጸጋ ይቀበላሉ።

መዝሙረ ዳዊት 7፡11—13; 1ኛ ዮሐንስ 2፡1-2

**ማስታረቅ ወይም መታረቅ** (reconciliation or reconcile)፡- "ወደ ስምምነት ወይም ጓደኝነት መመለስ; እንደገና ወደ ሰላም፣ ኅብረት ወይም ሞገስ ለመመለስ፡፡

ቃሉ ኃጢአተኞች የእግዚአብሔር ጠላቶች እንደሆኑ እና ቁጣው እንደሚገባቸዋል በግልጽ ያስተምራል፡፡ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት እና የዓለምን ኃጢአት በማስወገድ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ጠላትነት አሸንፏል፡፡ ኢየሱስ ኃጢአተኛው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቅ አስችሎታል፡፡

ሮሜ 5:10; 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡18-19

**ነፃ ማውጣት / መቤዠት** ፡-"በክፍያ ይዞታን መልሶ ለማግኘት፤ ከምርኮ ወይም ከባርነት ነፃ ለማውጣት ወይም ለማዳን፣ ማገገም ወይም ነፃ መውጣት "

ከኤደን ገነት ጀምሮ የሰው ልጅ የኃጢአት ባሪያ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሳኤው የሰው ልጆችን ወደ እግዚአብሔር መለሰ፡፡ አማኞች በክርስቶስ ነፃ ወጥተዋል፣ የማያምኑ ግን የኃጢአት ባርነት መያዛቸውን ቀጥለዋል፡፡

ማርቆስ 10:45; 1ኛ ጴጥሮስ 1:18-19

**ንስሐ መግባት**፡ " መጸጸት ወይም ማዘን ፣ያለፈውን ወይም የታሰበውን ድርጊት በተመለከተ ሀሳብን ወይም ልብን መለወጥ; አንድ ሰው ላደረገው ወይም ሊያደርገው ለነበረው ነገር መፀፀት "

አንድ አማኝ ለሠራው ኃጢአት በእውነት ሲጸጸት ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ይናዘዛል፣ ከኃጢአቱ ይመለሳል፣ ራሱን ለእግዚአብሔር ይሰጣል፣ እናም በጸጋው ይሄዳል፡፡

ማቴዎስ 3:8; የሐዋርያት ሥራ 26:20ለ; ኤፌሶን 4፡28

**ፃድቅ**፡- "ትክክለኛ ነገር ማድረግ፣ ልክ፣ቀጥ ያለ፣ ፍትሃዊ፣ በተለይም ከስሕተት፣ ከጥፋተኝነት ወይም ከኃጢአት የጸዳ; በጎነት; የሚገባው"

መጽሐፍ እንደሚል ጻድቃን ከእግዚአብሔር ጋር የሚራመዱ/የሚጓዙ ናቸው። የወደቁ ኃጢአተኞች በኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቃን ሆነዋል። ማዳኑን ለሚቀበሉት ጽድቁን በጸጋ ያካፍላል።

ዘፍጥረት 6:9; ሮሜ 5፡19

**መቀደስ፡-** "መንፃት/መጥራት ፣ የእግዚአብሔር የጸጋ ሂደት ሲሆን የሰው ፍቅር ከኃጢአት ርቆ ና ከፍ ከፍ ወዳለ ወደ እግዚአብሔር የበላይ ፍቅር የሚያስገባበት ሂደት ነው

እግዚአብሔር አማኙን የሚቀድሰው መዳንን እንዳገኘ ነው። በመቀጠልም አማኙ ከእርሱ ጋር በኅብረት እና በመታዘዝ ሲመላለስ በቅድስና ሂደት ውስጥ ይቀጥላል። መቀደስ ሙሉ የሚሆነው አማኙ አዳኙን ለዘላለም ሲገናኝ ነው።

1 ቆሮንቶስ 6:11; 1 ተሰሎንቄ 5:23; 1ኛ ዮሐንስ 3፡2

**ኃጢአት፡** "የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ፣ለመለኮታዊ ፈቃድ አለመታዘዝ፣ የሞራል ውድቀት፣በደል"

ኃጢአት በእግዚአብሔር ቃል፣ ሥልጣን፣ በጎነት፣ ጥበብ፣ ፍትህ፣ ወይም ጸጋ ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው። ኃጢአት ከዓመፀኛ ልብ ወይም ከተታለለ አእምሮ የሚወጣ ሲሆን በአመለካከት፣ በአስተሳሰብ፣ በቃል ወይም በድርጊት ይገለፃል።

መዝሙር 51:4; 1 ዮሐንስ 3:4; ሮሜ 14፡23

**ሉዓላዊ፡** "ከፍተኛ ና የበላይ ሀይል ያለው ፣ከሁሉም በላይ የበላይ የሆነ ቦታ ያለው ፣ ራሱን የቻለ ወይም የበላይ ሥልጣን ያለው።

እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው፡ እርሱ በፈጠረው ሁሉ ላይ ከፍተኛ ኃይል፣ ገደብ የለሽ ጥበብ እና ፍጹም ሥልጣን አለው።

መዝሙረ ዳዊት 139፡1—16፤ ተመልከት። ዳንኤል 4:35; ራእይ 4፡11

**መቀየር**፡"ቅርፅን መለወጥ፣ ተፈጥሮን, ዝንባሌን, ልብን ወይም የመሳሰሉትን ለመለወጥ፣ መለወጥ"

ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለው የጠበቀ ግንኙነት ስንመላለስ፣ የእርሱን መልክ እና ባህሪ ለማንፀባረቅ ህይወታችንን ይቀይረዋል። ከእርሱ ጋር ወደ ዘላለም ስንገባ ሙሉ ለሙሉ ክብሩን ለማንጸባረቅ እንለወጣለን።

1ኛ ቆሮንቶስ 15፡51—52፤ 2 ቆሮንቶስ 3:18; ፊልጵስዩስ 3:21; 1ኛ ዮሐንስ 3፡2

**በደል(መተላለፍ) ወይ በደለኛ ፡** "ኃጢአት፣ትዕዛዝን, ህግን ወይም ግዴታ መጣስ፣ ህግን የጣሰ ወይም ማንኛውንም የታወቀ የቅንነት፣ የጽድቅ ወይም የትክክለኛነት መርህ የሚጥስ ሰው።

እግዚአብሔር የጽድቅ ደረጃውን በአሥርቱ ትእዛዛት መሰረተ ። ትእዛዙን የሚተላለፉ ሰዎች ሞት ይገባቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ህግን ለመፈጸም፣ የሰውን ልጅ ኃጢአት በመስቀል ላይ ለመሸከም እና በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ መጽደቅ አንዲያገኙ ነው።

ኢሳይያስ 53:12; ማቴዎስ 5:17; ሮሜ 5:18; 7:12; ዕብራውያን 2፡2

**ለደቀ መዝሙሩ የተላከ ደብዳቤ**

**ውድ ደቀመዝሙር፣**

ይህን የደቀመዝሙርነት ራስን የሚያስተምር መጽሐፍ ስንዘጋ፣ እንደ ክርስቲያን በእምነት መኖር ምን ማለት እንደሆነ የተማራችሁትን ሁሉ እንድታንፀባርቁ አበረታታችኋለሁ። ይህ ጥናት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለዎትን ግንኙነትወደ ብስለት እና ወደ ማዳበር እንዲመራዎ እና እንዲረዳዎት እንዲሁም እግዚአብሔር ለደቀመዝሙርነት ላስቀመጠው ንድፍ/እቅድ ዓይኖችዎን እንደከፈተ እጸልያለሁ/አምናለሁ።

ኢየሱስ ሁሉም አማኞች እንዲታዘዙት የጠራቸውን የታላቁን ተልእኮ እይታ/መልእክት ቤተክርስቲያን እያጣች ነው። ታላቁ ተልእኮ ምን እንደሆነ የማያውቁ ክርስቲያኖች እየበዙ ነው። በዓለም ዙሪያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት አባሎቻቸው የኢየሱስን ግልጽ ትዕዛዝ እንዲታዘዙ ሳያስታጥቁ በራሳቸው ውስጣዊ ፕሮግራሞች ወይም ተልእኮዎች ላይ በማተኮር ትኩረታቸውን ይከፋፍላሉ። ነገር ግን አንተ ከአሁን በሀላ ኢየሱስ የሰጠውን ትእዛዝ አውቀሀል እናም ካላወቁት ወገን አደለህም ።

> እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። እስከ ዘመኑ መጨረሻ ድረስ. አሜን። ( ማቴዎስ 28:19—20 )

ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንድትሆኑ ትእዛዙን እንድትታዘዙ እማፀናችሃለሁ ። በእምነታችሁ ስታድጉ እና ስትጎለምሱ፣ ሌላውን በእምነታቸው ማነፅ/መገሰፅ እንድትችሉ ጥበብ እና ማስተዋል እንዲሰጣችሁ በመፀለይ መብቃት ደረጃ ላይ መድረሳችሁን እወቁ ። ዝግጁ ስትሆኑ ዓይኖቻችሁን እግዚአብሔር በህይወታችሁ ላስቀመጣቸው ሰዎች ክፈቱ እና ደቀመዝሙር ልታረጉ የምትችሉትን በንቃት ፈልጉ። ይህ የስራ ደብተር/መፅሄት ለአንተ ታዛዥነት የሚረዳ መሳሪያ ሊሆን ይችላል።

እኔ ያቋቋምኩት የቤተሰብ ደቀ መዝሙርነት አገልግሎት (FDM)በአምላክ ቃል ከሚሰጠው ጥበብና ትምህርት ጋር ለማስማማት ስለ ጋብቻና ስለ ልጅ አስተዳደግ የሚገልጹ ባለብዙ ጥራዝ የሥራ መጽሐፍትን አቅርቧል። *Marriage Is a Ministry series and Parenting Is a*

*Ministry series* ማለትም "ጋብቻ ተክታታይ አገልግሎት ነው" የተባለው እና "ወላጅነት ተክታታይ አገልግሎት ነው" መፅሄቶች  በቤተሰብዎ በኩል ለእግዚአብሔር ክብር ለማምጣት የሚረዳዎት ሁለት ጠቃሚ መሳሪያዎች ናቸው። ሌሎችን ደቀ መዛሙርት ለማድረግም እንዲሁም ሊያገለግሉበትም  ይችላሉ። እነዚህ ቁሳቁሶች በድረ-ገጻችን www.FDM.world ላይ ይገኛሉ።

ጌታ ይባርክህ ይጠብቅህ።

በክርስቶስ ወንድማችሁ

ፓስተር ክሬግ ካስተር

**ስለ ደራሲው**

ሞኝና ማንበብ ፣መፃፍ፣ችግር  ያለበት ተማሪ የነበረ ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በሶስተኛ (C)ደረጃ ውጤት ደካማ ተመራቂ የነበረ ። አላዋቂ ባል እና ጨቃኝ አባት። ከላይ የተገለፀው ሁሉ ፓስተር ክሬግ ካስተር በህይወቱ ውስጥ በአንድ ወቅት ያለፈበት ህይወት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእርሱ የተለየ እቅድ ነበረው። ክሬግ በሕዝብ ፊት ለመናገር ቢፈራም አምላክ በ1994 ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ጠራው። ያለ መደበኛ ትምህርት ወይም የሴሚናሪ ዲግሪ በእምነት ወጣ። በ 1995 የተሾመ ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አራት መጻሕፍትን ጽፏል፣ ብዙ ሰዎችን ደቀ መዝሙር አደረገ፣ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ምክር ሰጥቷል፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ወደ ክርስቶስ መርተዋል፣ እና በሺዎች የሚቆጠሩ በጋብቻ እና በወላጅነት ሴሚናሮች፣ ወንዶች/ባሎች ብቻ የሚሰበሰቡበት ቦታዎች እና በፓስተሮች ጉባኤዎች በመላው ዩናይትድ ስቴትስ እና በአለም አቀፍ ደረጃ አስተምሯል። ሁሉንም በእግዚአብሔር ጸጋ እና ኃይል አከናውኖታል ።

ምንም እንኳን ክሬግ በ1979 ህይወቱን ለኢየሱስ ቢሰጥም/ቢቀበልም፣ ለውጡ የጀመረው በኢየሱስ እና በቃሉ ውስጥ በየቀኑ መኖር ሲጀምር ነው። ኢየሱስ ከእያንዳንዳችን ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደሚፈልግ በእውነት ያምናል። ይህንን ግንኙነት ስለሚከታተል እና ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ ላይ ጥገኛ ስለሆነ ህይወቱ ለዘላለም ተለውጧል።

**ይበረታቱ**

እግዚአብሔር በህይወቶ እንደሚሰራ ለማመን እየታገልክ ከሆነ በፓስተር ክሬግ ታሪክ ተበረታታ። ያለፈው ኃጢአትህ፣ የመማር እክልህ፣ የማስተማር ወይም የመናገር ፍራቻ፣ ወይም የትምህርት እጦትህ በህይወታችሁ ላይ ላለው የእግዚአብሔር ጥሪ ከመታዘዝ እንዲያግድህ አትፍቀድ። እግዚአብሔር አንተን የእርሱ ደቀ መዝሙር ሊያደርግህ ይፈልጋል፣ እና ካገባህ ወይም ልጆች ከወለድክ፣ እርሱን የሚያከብር የትዳር ጓደኛ እና ወላጅ አድርጎ ሊፈጥርህ ይፈልጋል። ጸጋው አስደናቂ እና ገደብ የለሽ ነው። እሱ ይወድሃል እና በአንተ መከበር ይፈልጋል።

**እግዚአብሔር ለአንተ የገባው ቃል ኪዳን**

ተትረፈረፈ የተስፋ ቃሎቹና አቅርቦቶቹ እግዚአብሔር ይመስገን። የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ ከሆነው ***ከስምዖን ጴጥሮስ*** ቃላት በተገኙት የተስፋ ቃሎቹን አሰላስል ።

> እኛ ጋር እኩል የሆነና ክቡር እምነትን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ያገኙ ለእናንተ፤
>
> ጸጋና ሰላም በእግዚአብሔርንና በጌታችንን በኢየሱስን በማወቅ ይብዛላችሁ። በክብርና በምግባር በጠራን በእርሱ እውቀት፣ ለመለኮታዊ ሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልገንን ሁሉ በእርሱ መለኮታዊ ኃይል ሰጥቶናል። በእነዚህም ከዓለም በምኞት ካለው ጥፋት አምልጣችሁ የመለኮት ተካፋዮች ትሆኑ ዘንድ እጅግ ታላላቅና ክቡራን ተስፋዎች ተሰጥተውናል። ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ጨምሩ፤ በበጎነትም ላይ እውቀትን፣ በእውቀትም ላይ ራስን መግዛትን፣ ራስን በመግዛትም ላይ ጽናትን፣ በጽናትም ላይ እግዚአብሔርን መምሰልን፣ እግዚአብሔርን በመምሰልም ላይ የወንድማማች መዋደድን፣ በወንድማማች መዋደድም ላይ ፍቅርን ጨምሩ። እነዚህ ነገሮች በእናንተ ውስጥ ቢበዙና ቢሞሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ፍሬ አልባና የማትጠቅሙ አትሆኑም።(2 ጴጥሮስ 1:1—8)

**ስለ ቤተሰብ ደቀመዝሙርነት አገልግሎት**

በ1994 በመስራች እና በዳይሬክተር ፓስተር ክሬግ ካስተር የተቋቋመው የቤተሰብ ደቀመዝሙርነት ሚኒስቴር (ኤፍዲኤም፣FDM) የክርስቶስን አካል በደቀመዝሙርነት ሞዴል

ቤተሰብን እንዲያገለግል ለመደገፍ፣ ለማስተማር እና ለማሰልጠን ይተጋል። ይህንን ግብ ለማሳካት ኤፍዲኤም ለግል ጥናት፣ ለአነስተኛ ቡድኖች፣ ለቤት-ቡድን ጥናት እና አንድ ለአንድ ደቀመዝሙርነት መጽሃፎችን፣ ደጋፊ ቪዲዮዎችን እና የመስመር ላይ ቁሳቁሶችን ያቀርባል። በደቀመዝሙርነት፣ በጋብቻ እና በወላጅነት ላይ ሴሚናሮችን ያካሂዳሉ።

የኤፍዲኤም /FDM አገልግሎት ግብ የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን ለደቀመዝሙርነት ራዕይ እንዲያዳብሩ እና የቤተክርስቲያናቸውን ቤተሰብ እንዲያገለግሉ ለመርዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽኑ መጽሐፎችን እንዲያቀርቡ መምከር፣ ማሰልጠን እና ማስታጠቅ ነው። ከ 1995 ጀምሮ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የጋብቻ እና የወላጅነት ትምህርቶችን ያጠናቀቁ ሲሆን በመላው ዩናይትድ ስቴትስ እና በውጪ የሚገኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት የኤፍዲኤም ቁሳቁሶችን በመጠቀም ጉባኤያቸውን አገልግለዋል። አገልግሎታቸውም በ www.FDM.world በሚገኙ ድህረገፅ ላይ በነጻ ባሉ ግብዓቶች ብዙ ቤተሰቦችን ይረዳል።

ኤፍዲኤም /FDM እንደ ሩሲያ፣ ዩክሬን፣ ኩባ፣ ሜክሲኮ፣ አፍሪካ፣ ሲንጋፖር፣ ጃፓን እና ቻይና ባሉ አገሮች ውስጥ በንቃት ያገለግላል። ተጨማሪ ድህረገፅ በ www.FDM.world ላይ ያግኙ።